## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ- ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የመደብ ልዩነትና ርዕዮተ ዓለማዊ ተቃርኖ በ*ማዕበል የአብዮት ዋዜማ*፣ በ*ማዕበል የአብዮት መባቻ* እና በ*ማዕበል የአብዮት ማግስት*፤ ከልዋ አልኢዩሴ ማርክሳዊ ንድፈ-ሃሳብ አንጻር

በ

ዳዊት ብርሃኑ

የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሁፍና ፎክሎር መርሀ ግብር የኤም.ኤ ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉ ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት

ሰኔ 2005 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ- ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል


የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የመደብ ልዩነትና ርዕዮተ ዓለማዊ ተቃርኖ በማዕበል የአብዮት ዋዜማ፣ በማዕበል የአብዮት መባቻ እና በማዕበል የአብዮት ማግስት፤ ከልዊ አልኢዩሴ ማርክሳዊ ንድፈ-ሃሳብ አንጻር

በ


ዳዊት ብርሃኑ


የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሁፍና ፎክሎር መርሀ ግብር የኤም.ኤ ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉ ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት


አማካሪ፡- ቴዎድሮስ ገብሬ



ሰኔ 2005 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ- ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## የድኅረ ምረቃ መርሐግብር

# የመደብ ልዩነትና ርዕዮተ ዓለማዊ ተቃርኖ በማዕበል የአብዮት ዋዜማ፣ በማዕበል የአብዮት መባቻ እና በማዕበል የአብዮት ማግስት፤ ከልዊ አልኢዩሴ ማርክሳዊ ንድፈ-ሃሳብ አንጻር

### የፈተና ቦርድ አባላት

| | ፊርማ |
| --- | --- |
| አማካሪ | |
| ፍቅረማርያም ገብሩ | [signature] |
| የውስጥ ፈታኝ | |
| ሀበስፍን [illegible] | [signature] |
| የውጭ ፈታኝ | |
| Daghachew Assefa Desta | Daghachew A. Desta |

# ምስጋና

ይህ ጥናት ለዚህ እንዲበቃ የተቻላቸውን ሁሉ ላደረጉልኝ መምህሬና አማካሪዬ አቶ ቴዎድሮስ ገብሬ (ረ.ፕ.) ምስጋናዬ ላቅ ያለ ነው፡፡ የበኩር ልጄን እንድጠብቅ ላደረግሽኝ የቡሬ ዳሞቷ አስረሴ ለሁሉም ነገር  አመሰግናለሁ (አንድዬ ውለታሽን ይክፈለው)፡፡ የት ላኑርህ እያልሽ ለምጠሪኝ ውዷ እናቴ መስታወት ተመስገን ያላንቺ ብርታትና ጥረት እዚህ አልደርስም ነበርና እጅግ አድርጌ አመሰግንሻለሁ፡፡ እማ በእውነት አንቺ የምር መስታወቴ ነሽ!! አዲስ  ያንቺ ላፕቶፕ ባይኖር ኖሮ የፊደል ግድፈትን እንደምን እዋጋው ነበር? ለማንኛውም ላንቺም ምስጋናዬ ይድረስሽ፡፡

## ማውጫ


ርዕስ ገጽ

ምስጋና ........ i

አጠቃሎ ........ iv

ምዕራፍ አንድ ........ 1

1. መግቢያ ........ 2

1.1. የጥናቱ ዳራ ........ 3

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 4

1.3. የጥናቱ ዓላማ ........ 4

1.3.1. የጥናቱ ዋና ዓላማ ........ 4

1.3.2. የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች ........ 5

1.4.ጥናቱ የሚመልሳቸው የምርምር ጥያቄዎች ........ 5

1.4.1. የጥናቱ ዋና የምርምር ጥያቄ ........ 5

1.4.2. የጥናቱ ዝርዝር የምርምር ጥያቄዎች ........ 6

1.5. የጥናቱ ዘዴ ........ 6

1.6. የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 7

1.7. የጥናቱ መጠነ ርዕይ (ወሰን) ........ 8

ምዕራፍ ሁለት ........ 8

2. ክለሳ ድርሳን ........ 8

2.1. ንድፈ-ሃሳባዊ ዳራ ........ 8

2.1.1. መደብ፣ የመደብ ልዩነት፣ ርዕዮተ ዓለማዊ ተቃርኖና የመደብ ትግል ጽንሰ ሃሳባዊ ትስስር ........ 11

2.1.2. የልዊ አልአ.ዩሴ ማርክሳዊ ንድፈ ሃሳብ ምንነት ........ 12

2.1.2.1. ማህበረሰባዊ ውስብስብ የምክንያትና ውጤት ቁርኝት ምንነት ........ 14

2.1.2.2. የርዕዮተ-ዓለም ምንነት ........ 15

2.1.2.3. ማህበረሰባዊ የግንዛቤና የቁጥጥር ተቋማት ምንነት ........ 17

2.1.2.4. ማንነትን የማፅናትና ማጎልበት ምንነት ........ 18

2.2. የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት

ምዕራፍ ሶስት

3. የመደብ ልዩነትና ርዕዮተ ዓለማዊ ተቃርኖ በማዕበል የአብዮት ዋዜማ፣ በማዕበል የአብዮት መባቻ እና በማዕበል የአብዮት ማግስት፣ ከልዊ አልኢዩሴ ማርክሳዊ ንድፈ ሐሳብ አንፃር .....34

3.1. ርዕዮተ ዓለማዊ መነሻ በ'ባላገሩ'ና በ'መሳፍንቱ' ማሳያነት .....34

3.2. ማንነትን ማጽናትና ማጎልበት እንደ መደብ ልዩነት .....36

3.2.1. የመሳፍንቱና የባላገሩ ወገንተኝነት (በ"ማንነት" መነፅር) .....36

3.2.2. የ"ካሳሁን" አዲስ ማንነት ፍለጋ .....48

3.3. የቁጥጥር ተቋማት ተፅእኖና ጭቆና .....52

3.3.1. አካላዊ ጭቆና .....52

3.3.2. የአመለካከት ጭቆና .....57

3.4. የግንዛቤ ተቋማትና ርዕዮተ-ዓለማዊ ተቃርኖ .....61

3.4.1. የመገናኛ ብዙሃን እንደፕሮፖጋንዳ ማስፈፀሚያ .....61

3.4.2 ትምህርት ቤት እንደ ተቃውሞ ድምፅ .....64

3.5. ማህበረሰባዊ ውስብስብ የምክንያትና ውጤት ቁርኝት .....67

ምዕራፍ አራት

4. መደምደሚያ .....71

ዋቢ ጽሑፎች .....75

## አጠቃሎ

ይህ ጥናት የመደብ ልዩነትና ርዕዮተ ዓለማዊ ተቃርኖ በማዕበል የአብዮት ዋዜማ፣ በማዕበል የአብዮት መባቻ እና በማዕበል የአብዮት ማግስት ክልዋ አልአዩሴ ማርክሳዊ ንድፈ-ሃሳብ አንፃር በሚል ርዕስ የቀረበ ነው፡፡ የጥናቱ ዘዴና ቴክኒክ እንደየቅደምተከተላቸው ነገረ-ፍካሬና የዲስኩር ትንተና ናቸው፡፡ ጥናቱ ቴክስቶቹ ለልዋ አልአዩሴ ማርክሳዊ ንድፈ-ሃሳብ ምቹ ናቸው በሚል ፅኑ እምነት የተደረገ ነው፡፡ የማህበረሰቡ ርዕዮተ ዓለማዊ መነሻ፣ ማንነትን ማጎልበትና ማፅናት፣ የመደብ ልዩነት፣ የግንዛቤና የቁጥጥር ተቋማት ሚና፣ ርዕዮተ ዓለማዊ ተቃርኖና ውስብስብ የምክንያትና ውጤት ቁርኝት የጥናቱ ዋንኛ የትኩረት ነጥቦች ናቸው፡፡ ጥናቱ የማህበረሰቡ ማንነት ማጎልበት ሂደት ለመደብ ልዩነቱ ተጠቃሽ ምክንያት መሆኑን አሳይቷል፡፡ ግለሰቦች በርዕዮተ ዓለም አማካይነት አዲስ ማንነትን መቀዳጀት እንሚችሉ ተጠቅሷል፡፡ የቁጥጥር ተቋማት በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸው ሚና የጭቆና ተግባር እንደሆነም ተብራርቷል፡፡ በድርሰቶቹ ውስጥ የትምህርት ቤት ተቋማት ተግባር ተቃውሞን ማቀጣጠል ሲሆን፣ የመገናኛ ብዙሃኑ ደግሞ የፕሮፓጋንዳ ማስፈጸሚያዎች ናቸው፡፡ የመሰረትና ላዕላይ መዋቅሩ ዝምድና ኢኮኖሚያዊ ብቻ ሳይሆን ውስብስብ ፖለቲካዊ፣ ባህላዊ ወዘተ. ቁርኝትም እንዳላቸው ተዳሷል፡፡ በንድፈ-ሃሳቡ መታገዚያነት ዓመፅ፣ ትግል፣ ለውጥ እንዲሁም አዲስ ማንነትና ወገንተኝነት በጥናቱ ሂደት የተገኙ ውጤቶች ናቸው፡፡ ለዚህ ግኝት ዋንኛ ምክንያት ደግሞ ንድፈ-ሃሳቡና ቴክስቶቹ በአግባቡ ተናበው መቅረባቸው ነው፡፡ በመጨረሻም ከዚህ ውጤት በመነሳት በቴክስቶቹ ውስጥ የማህበረሰቡ አእምሮ የሚገነባው በርዕዮተ ዓለም አማካይነት ነው ብሎ ማጠቃለል ይቻላል፡፡

# ምዕራፍ አንድ

## 1. መግቢያ

የሥነ-ጽሑፍ ስራ ህይወትን መተርጎም ነው፡፡ ይህ ህይወት ደግሞ ከማህበረሰቡ ጋር ይቆራኛል፡፡ ማዕበል የአብዮት ዋዜማ፣ ማዕበል የአብዮት መባቻ እና ማዕበል የአብዮት ማግስት በማህበራዊ እውነታ ላይ የተመሰረቱ ድርሰቶች ናቸው፡፡ በመሆኑም የዘመኑን ታሪክ፣ ባህል፣ ማህበራዊ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ህይወት ሰንዷው ይዘዋል፡፡ መጻሕፍቱ የጥቂቶቹን ገዥነት የብዙሃኑን ተገዥነት የሚያንፀባርቅ መደባዊ ባህርይ ዓላቸው፡፡ ይህ የመደብ ልዩነት ደግሞ ገፀ-ባህርያቱን ለርዕዮተ ዓለማዊ ተቃርኖ ሲያሰናዳቸው ይታያል፡፡ በመሆኑም በመሃከላቸው የታሪክን አቅጣጫ ለመቀየርና ማህበራዊ ለውጥ ለማምጣት የሚደረግ ሽኩቻ አለ፡፡ ስለዚህ በድርሰቶቹ ውስጥ ማህበረሰቡ የራሱ የሆነ ቀለምና አሻራ ዓለው፡፡ ይህ ጥናት ከላይ በጠቀስኳቸው ሶስት የብርሃኑ ዘሪሁን ድርሰቶች ላይ ተመስርቷል፡፡ የመደብ ልዩነትና ርዕዮተ ዓለማዊ ተቃርኖ ከልዊ አልአ.ዩሴ[1] (*Louis Althusser)* ማርክሳዊ ንድፈ-ሃሳብ አንፃር ተፈክሯል፡፡

ማርክሳዊ ንድፈ-ሃሳብ እጅግ ጥንታዊና ሰፊ እንዲሁም በየዘመኑ የተለያዩ አቀንቃኞችን መፍጠር የቻለ ንድፈ-ሃሳብ ነው፡፡ ስለሆነም ይህ ጥናት ማርክሳዊ ፈላስፋ እንዲሁም ማርክሳዊ የሥነ-መዋቅር አቀንቃኝ በሆነው የልዊ አልአ.ዩሴ ማርክሳዊ ንድፈ-ሃሳብ ላይ ተመስርቷል፡፡ ርዕዮተ ዓለም (*ideology*)፣ የማንዛቤና የቁጥጥር ተቋማት (*ideological state apparatus and repressive state apparatus*)፣ ማንነትን ማጎልበትና ማፅናት (*over-interpellation)* እንዲሁም ማህበረሰባዊ ውስብስብ የምክንያትና ውጤት ቁርኝት (*over-determinism)* ንድፈ-ሃሳቡ የተመሰረተባቸው ቁልፍ ነጥቦች ናቸው፡፡ ጥናቱም በዋነኝነት በነዚሁ ላይ ይሽከረከራል፡፡ በቴክስቶቹ ውስጥ ዕንሰ ሃሳቦቹ በተናጥል ይፈተሻሉ፡፡

ጥናቱ አራት ምዕራፎች አሉት፡፡ በምዕራፍ አንድ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ ዓላማ፣ ጥናቱ የሚመልሳቸው የምርምር ጥያቄዎች፣ የጥናቱ ጥቅም፣ የጥናቱ ገደብና የጥናቱ ዘዴ ቀርቧል፡፡ በምዕራፍ ሁለት (ክለሳ ድርሳን) ንድፈ-ሃሳባዊ ዳራና የተዛማጅ

---

[1]ልዊ አልአ.ዩሴ የሚለውን መጠሪያ ከፈረንሳይኛ አፍ አዋቂዎች ጠይቄ ያሰፈርኩት ነው፡፡ በቀጣዩ የጥናቱ ክፍል በአማረኛ ያሰፈርኩትን መጠርያ ብቻ ይገፍ የምዘልቅ ይሆናል፡፡

ፅሁፎች ይቃኛሉ፡፡ በምዕራፍ ሶስት በርዕሱ መነሻነት የመረጃ ትንተና ይቀርባል፡፡ በመጨረሻም ጥናቱ በምዕራፍ አራት መደምደሚያ ይኖረዋል፡፡

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

ይህ ጥናት የመደብ ልዩነትና ርዕዮተ ዓለማዊ ተቃርኖ በማዕበል የአብዮት ዋዜማ፣ በማዕበል የአብዮት መባቻ እና በማዕበል የአብዮት ማግስት፣ ከልዊ አልአ.ዩሴ ማርክሳዊ ንድፈ-ሃሳብ አንጻር በሚል ርዕስ የቀረበ ነው፡፡ ከዚህ ጥናት ጋር ቅርበት ያላቸውን ሁለት መጣጥፎች አግኝቻለሁ፡፡ እነዚህም መጣጥፎች ብርሃኑ ገበየሁ (1992)ና በቀለ ገለታ (1968) ናቸው፡፡

የብርሃኑ ጥናት "ልቦለድ እንደ ርዕዮተ ዓለም መገለጫ" በሚል ርዕስ የቀረበ ነው፡፡ የጥናቱ ትኩረትም በፍቅር እስከመቃብር፣ በወንጀለኛው ዳኛ እና የልምዣት ውስጥ የሚስተዋሉ ማህበራዊ አውዶች ("ትምህርት ቤት"፣ "ጋብቻ"ና "ሽፍትነት")ን መተንተን ነው፡፡ ይህን ለማድረግ የተመሰረተበት ፅንሰ ሃሳብ ርዕዮተ ዓለም ነው፡፡ ብርሃኑ በአውዶቹ ውስጥ ማህበራዊ ባህላዊና ማህበራዊ ፖለቲካዊ ለውጦችን ፈትሿል፡፡

ልቦለዳዊ ትረካዎቹ የተወለዱት ከማህበራዊ ፖለቲካዊ ቀውስ ውስጥ እንደሆነም ጠቁሟል፡፡ የዘመናዊ ትምህርት ጣጣ በፍቅር እስከመቃብር ውስጥ በግልፅ የሚታይ ሳይሆን በትርጓሜ የሚደረስበት መሆኑን አብራርቷል፡፡ በየልምዣት ውስጥ በተሳሉ ወጣቶች ላይ የምናስተውለው የማንነት ቀውስ ከተዛባ የትምህርት ስርዓት የመነጨ መሆኑንም ተንትኗል፡ ፡በየልምዣት ውስጥ የ"ታምራት"ና "ደመቀች" ጋብቻ በታምራት ግንባር ሲታይ ፖለቲካዊ ጋብቻ እንደሆነም ገልጿል፡፡ አመፃና ህጋዊነትም ሰዎች ያሉበትን አስቸጋሪ ሁኔታ ሲረዱ ወይም የተጫነባቸውን ጭነት ለመሸከም ሲሳናቸው የሚፀነስ መሆኑንም ጠቁሟል፡፡

ሌላው በቀለ ገለታ "Political Socialization in Ethiopia" በሚል ርዕስ መጣጥፉን አቅርቧል፡፡ የጥናቱ ትኩረት አንድን ህዝብ በጎሳ፣ በሃይማኖት፣ በቋንቋ፣ ወዘተ. ሳይከፋፍሉ አንድ ወጥ ሃገር መመስርት ይቻላል የሚል ነው፡፡ ይህን ለማድረግ ደግሞ ሆን ተብሎ በሥርዓተ-ትምህርት በተቀነባበረ ርዕዮተ ዓለም ህዝቡን መጥመቅ፣ መስበክ፣ ማሳመን ወዘተ. እንደሚገባ ገልጿል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ትልቅ የሃገር ፍቅር ያለው ትውልድና በጎሳ፣

በቀለም፣ በቋንቋ ወዘተ. ሳይገለል ተከባብሮ መኖር የሚችል ማህበረሰብ መፍጠር እንደሚቻል አስረድቷል፡፡

እነዚህ ሁለት መጣጥፎች ማህበረሰቡን ማዕከል አድርገው የተጠኑ ናቸው፡፡ የብርሃኑ ጥናት ባብዛኛው ማህበረ-ባህሉንና ማህበረ-ፖለቲካውን የዳሰሰ ሲሆን፤ የበቀለ መጣጥፍ ግን ሙሉ ትኩረቱ በሃገር ደረጃ እንዴት ማህበራዊ አንድነትን መፍጠር እንደሚቻል ያብራራ ነው፡፡ በተለይ ባነሷቸው በነዚህ መሰረታዊ ነጥቦች ከኔ ጥናት ጋር ያላቸው ዝምድና ከፍ ያለ ነው፡፡ ነገር ግን ከነሱ በተለየ ሁኔታ የኔ ጥናት ከላይ በተጠቀሱት ሥነ-ፅሑፋዊ ስራዎች ላይ ተመስርቶ የመደብ ልዩነትንና ርዕዮተ ዓለማዊ ተቃርኖን ከልዊ አልኢዩሴ ማርክሳዊ ንድፈ-ሃሳብ አንፃር ፈክሯል፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ይህን ጥናት ለማድረግ ያነሳሱኝ የተለያዩ ምክንያቶች አሉ፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ የተመሰረትኩባቸው ቴክስቶች በቀጥታ ንድፈ-ሃሳቡን ይጠራሉ፡፡ ምክንያቱም በውስጣቸው ታሪክን ከዘመን፣ ማህበረሰቡን ከመንግስት፣ ርዕዮተ ዓለሙን ከተማሪው፣ ተማሪውን ከገበሬው ወዘተ. አንዳቸውን ባንዳቸው ውስጥ የሚያናብቡ ናቸው፡፡ ቴክስቶቹ የመደብ ልዩነትና የርዕዮተ ዓለማዊ ተቃርኖ ማደሪያዎች ናቸው፡፡ በቴክስቶቹ ውስጥ የሚታዩት ማህበረሰቦች በባህሪና ድርጊት ውስብስብ ናቸው፡፡ በአንድ ወይም ሁለት የህይወት ጠገግ (ምሳሌ፤ ፖለቲካና ኢኮኖሚ) ብቻ የሚቃኙ አይደሉም፡፡ በቴክስቶቹ ውስጥ ማህበሩ ከተለያዩ ጉዳዮች ተገምዶ የተሰራ ነው፡፡ ይህ መሆኑ ደግሞ ለአልኢዩሴ ማርክሳዊ ንድፈ-ሃሳብ የተመቸ ያደርገዋል፡፡ ምክንያቱም ንድፈ-ሃሳቡ ከተለያዩ የትምህርት ዘርፎች ጋር ተዋዶና ተቃኝቶ የተወለደ ነው፡፡ ከሥነ-ልቦና *(over determinism)*፣ ከፍልስፍና *(ideology)*፣ ከፖለቲካ (*state power*) ወዘተ. መጥቀስ ይቻላል፡፡ ስለሆነም የንድፈ-ሃሳቡ በይነ-ዲሲፕሊናዊነት[2] ለተመረጡት ቴክስቶች እጅጉን ቅርብ ናቸው፡፡

---

[2] ቴዎድሮስ ገብሬ (2001፣ 259) *በይነ-ዲሲፕሊናዊ የሥነ-ጽሑፍ ንባብ* በተሰኘው መጽሐፉ በይነ-ዲሲፕሊናዊነት ማለት ከአንድ በላይ በሆኑ ‹‹ዲሲፕሊኖች›› ጥምረትና ውህደት የማሰብ፣ የመጠየቅ፣ የማጥናትና የመመርመር ልምድ ነው ይላል፡፡ በኔው ርእይ ልዊ አልኢዩሴ በዚህ አመለካከት ውስጥ መፈረጅ ያለበት ባለሙያ ይመስለኛል፡፡

ሌላው የንድፈ-ሃሳቡ አቀንቃኝ በራሱ አነሳሽ ምክንያት ነው፡፡ ልዊ አልኢዩሴ እስካሁን ኑረው ካለፉት የማርክሳዊ ንድፈ-ሃሳብ አቀንቃኞች አንፃር ተፅእኖ ፈጣሪና የማርክሳዊ ንድፈ-ንድፈ-ሃሳብ ከላሽ (*Marxist revissionist*) ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ስለዚህ ማርክሳዊ ንድፈ-ሃሳቡ የተመሰረተባቸው መሠረታዊ ነጥቦች የንድፈ-ሃሳቡ ጨመቅ ናቸው፡፡ በመሆኑም የንድፈ-ሃሳቡ ምሰሶ የሆኑት ጽንሰ ሀሳቦች (ሐቲቶች) ለቴክስቶቹ ማናበብያነት እጅጉን የተመቹ ሆነው አግኝቻቸዋለሁ፡፡

በኔው ምልከታና ፍተሻ እስካሁን የልዊ  አልኢዩሴን ማርክሳዊ ንድፈ-ሃሳብ ብቻ ይዞ የሃገራችንን የሥነ-ፅሑፍ ስራዎች የመረመረ ባለሙያ አላገኘሁም፡፡ ይህ በመሆኑ ደግሞ ከቴክስቶቹ ጋር በተያያዘ የተከተልኩት ንድፈ-ሃሳብ የተለያዩ ጥያቄዎችን እንድጠይቅ አድርጎኛል፡፡ የግለሰብ፣ ማህበረሰብና ርዕዮተ ዓለም ዝምድና ምንድን ነው? ለሰው ልጅ አመለካከትና ድርጊት መገደብ ምክንያቱ ምንድነው? እና እንዲሁ በዘፈቀደ የሚኖር ማህበረሰብ አለ ወይስ ሁሉም በርዕዮተ ዓለም ተፀንሶ በርዕዮተ ዓለም ሚወለድ ነው? በጥቅሉ የነዚህ ጥያቄዎች አለመመለስ ደግሞ ተጨማሪ አነሳሽ ምክንያቴ ነው፡፡

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ

ይህ ጥናት ከተንደረደረበት ርዕስና ከሚከተለው ንድፈ-ሃሳብ አንፃር የራሱ ዋና ዓላማና ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፡፡

### 1.3.1. የጥናቱ ዋና ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋንኛ ዓላማ የመደብ ልዩነትና ርዕዮተ ዓለማዊ ተቃርኖን በ*ማዕበል የአብዮት ዋዜማ*፣ በ*ማዕበል የአብዮት መባቻ* እና በ*ማዕበል የአብዮት ማግስት*፣ ከልዊ አልኢዩሴ ማርክሳዊ ንድፈ-ሃሳብ አንፃር መፈከር ነው፡፡

### 1.3.2. የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች

የዚህ ጥናት ዝርዝር ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- በ*ማዕበል የአብዮት ዋዜማ*፣ በ*ማዕበል የአብዮት መባቻ* እና በ*ማዕበል የአብዮት ማግስት* ውስጥ የማህበረሰቡን ርዕዮተ ዓለማዊ አመለካከት መተንተን፡፡
- በ*ማዕበል የአብዮት ዋዜማ*፣ በ*ማዕበል የአብዮት መባቻ* እና በ*ማዕበል የአብዮት ማግስት* ውስጥ የመደብ ልዩነት መከሰቻ ምክንያቶችን መመርመር፡፡

- በማዕበል የአብዮት ዋዜማ፣ በማዕበል የአብዮት መባቻ እና በማዕበል የአብዮት ማግስት ውስጥ የማህበረሰቡን የአካልና የአመለካከት ጭቆና በገፀ-ባህርያቱ ማሳያነት መተርጎም፡፡
- በማዕበል የአብዮት ዋዜማ፣ በማዕበል የአብዮት መባቻ እና በማዕበል የአብዮት ማግስት ውስጥ ርዕዮተ ዓለማዊ ተቃርኖን በማህበራዊ ተቋማት አማካይነት መፈተሽ፡፡
- በማዕበል የአብዮት ዋዜማ፣ በማዕበል የአብዮት መባቻ እና በማዕበል የአብዮት ማግስት ውስጥ ማህበረሰቡ ከላዕላይ መዋቅሩ ጋር ያለውን ውስብስብ ዝምድና ማስረዳት ናቸው፡፡

## 1.4.ጥናቱ የሚመልሳቸው የምርምር ጥያቄዎች

ይህ ጥናት የሚመልሳቸው ዋናና ዝርዝር የምርምር ጥያቄዎች አሉት፡፡

### 1.4.1. የጥናቱ ዋና የምርምር ጥያቄ

የዚህ ጥናት ዋንኛ የምርምር ጥያቄ በማዕበል የአብዮት ዋዜማ፣ በማዕበል የአብዮት መባቻ እና በማዕበል የአብዮት ማግስት ውስጥ ማህበረሰቡ እንዴት ተሰራ? የሚል ነው፡፡

### 1.4.2. የጥናቱ ዝርዝር የምርምር ጥያቄዎች

የጥናቱ ዝርዝር የምርምር ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- በማዕበል የአብዮት ዋዜማ፣ በማዕበል የአብዮት መባቻ እና በማዕበል የአብዮት ማግስት ውስጥ የፊውዳሉ ርዕዮተ ዓለም መነሻ ስፍራ የት ነው?
- በማዕበል የአብዮት ዋዜማ፣ በማዕበል የአብዮት መባቻ እና በማዕበል የአብዮት ማግስት ውስጥ ማንነትን ማጎልበትና ማፅናት ከመደብ ልዩነት ጋር ያለው ቁርኝት ምንድነው?
- በማዕበል የአብዮት ዋዜማ፣ በማዕበል የአብዮት መባቻ እና በማዕበል የአብዮት ማግስት ውስጥ የማህበረ-ፖለቲካዊ የቁጥጥር ተቋማት ሚና ምንድነው?
- በማዕበል የአብዮት ዋዜማ፣ በማዕበል የአብዮት መባቻ እና በማዕበል የአብዮት ማግስት ውስጥ የግንዛቤ ተቋማት ርዕዮተ ዓለማዊ ተቃርኖን እንዴት ያስፈፅማሉ?

- ➢ በማዕበል የአብዮት ዋዜማ፣ በማዕበል የአብዮት መባቻ እና በማዕበል የአብዮት ማግስት ውስጥ የማህበረሰቡ የምክንያትና ውጤት ትስስር እንዴት ይገለፃል? የሚሉት ናቸው፡፡

## 1.5. የጥናቱ ዘዴ

ጥናቱ ሙሉ በሙሉ በቤተ-መጻሕፍት ንባብ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ የጥናቱ የምርምር ዘዴ ነገረ-ፍካሬ (*hermeneutics*) ነው፡፡ ይህ ዘዴ ብዙ ጊዜ በስነ-መለኮት፣ በፍልስፍናና በስነ-ፅሑፍ ጥናት ውስጥ ተግባራዊ ይሆናል፡፡ ዘዴው ቀደም ብለው የተፃፉና አሁን እየኖርነው ካለው ህይወት የተለየ አውድና የአኗኗር ይትበሃል የተንፀባረቀባቸውን ቴክስቶች የሚፈልግ በመሆኑ፤ እንዴት አንብበነው ቴክስቱን እንዴት መረዳት እንደሚቻል መፈተሽ የሚያስችል ነው፡፡ ነገረ-ፍካሬ በቀጥተኛና ተራ ንባብ እንዲሁም ከቴክስቱ ያገኘነውን ሃሳብ ይዘን መልሰን ወደ ቴክስቱ በመመለስ ላይ ያተኮረ ዘዴ አይደለም፡፡ ይልቁንም ከቴክስቱ ባሻገር እየተጓዙ መተርጎምን ይሻል፡፡ "*Hermeneutics was not 'reading' or 'return to texts' but, 'an attempt to interpret them*' (Thiselton,1,2009)፡፡ ከዘዴው ባሻገር የዚህ ጥናት ስልት (ቴክኒክ) የዲስኩር ትንተና (*discourse analysis*)[3] ነው፡፡ የዲስኩር ትንተና በአንድ የሥነ-ፅሑፍ ስራ ውስጥ የምናስተውላቸውን የገፀ-ባህርያት ምልልስ፣ ገለፃ፣ የተራኪውን እይታ ሁሉ ይመለከታል፡፡ ስለሆነም እነዚህ ጉዳዮች በጥናቱ የትንተና ክፍል የትኩረት ነጥቦች ናቸው፡፡ በዚህ ሂደት የጥናቱ ዋንኛ የማጠንጠኛ ሃሳብ በቴክስቶቹ ውስጥ የማህበረሰቡ አእምሮ የሚገነባው በርዕዮተ ዓለም አማካይነት ነው የሚል ነው፡፡

## 1.6. የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት ከተመሰረተበት ርዕስ አንፃር የሚከተሉት መሰረታዊ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡

- ➢ ከሥነ-ፅሑፍ መስክ ጋር ተያይዞ የማርክሳዊ ንድፈ ሃሳብን ይዘው ለሚያጠኑ እኔን መሰል አጥኚዎች መነሻ ሃሳብ ሆኖ ያገለግላል፡፡

---

[3] Brian (2006: 2) *Discourse Analysis: An Introduction* በተሰኘው መጽሐፉ የዲስኩር ትንተናን ለመጀመርያ ጊዜ ያስተዋወቀው ሩሲያዊው የሥነ-ልሳን ባለሙያ ዜሊግ ሀሪስ (Zellig Harris) መሆኑን ጠቁሟል፡፡ በጊዜው የዲስኩር ትንተናን በሁለት መንገድ ከፍሎ ለማስረዳት ሞክሯል፡፡ አንደኛው የንግግር ዲስኩር ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ የጽሑፍ ዲስኩር ነው፡፡ ረጅም ልቦለድ፣ አጭር ልቦለድ፣ ግጥም ወዘተ. በጽሑፍ ዲስኩር ስር እንደሚካተቱ አስረድቷል፡፡ ከዲስኩር ነጻ የሆነ ቴክስት የለም ሲልም ሞግቷል፡፡ እንዲሁም ቴክስትን ይዞ የዲስኩር ትንተናን ማቅረብ እንደሚቻልም ጠቁሟል፡፡

- ከተመሰረትኩበት ንድፈ-ሃሳብ ጋር መልካም ትውውቅን ለመፍጠር ያስችላል፡፡
- የስነ-ልቦና፣ ፍልስፍናና ሥነ-ጽሑፍን ቁርኝትና በይነ-ዲሲፕሊናዊነት ያስረዳል፡፡ ስለሆነም የአንባቢን ዘርፈ ብዙ አካዳሚያዊ እይታ ይጨምራል፡፡
- ቀደም ሲል ከነበረው ማህበረሰብ ርዕዮተ ዓለማዊ ፍልስፍና ጋር ያስተዋውቃል፡፡ የጥንቱን ከአሁኑ ዘመን አመለካከቶች ጋር አዋግኖ ለመረዳት ያስችላል፡፡
- ጥናቱ ከተመሰረተበት ንድፈ ሃሳብ ባሻገር ለሌላ አዳዲስ ፅንሰ ሃሳቦች እውቂያ ይጋብዛል፡፡

## 1.7. የጥናቱ መጠነ ርዕይ (ወሰን)

ይህ ጥናት *ማዕበል የአብዮት ዋዜማ፣ ማዕበል የአብዮት መባቻ* እና *ማዕበል የአብዮት ማግስት* በተባሉት የብርሃኑ ዘሪሁን የሶስትዮሽ ድርሰቶች (*trilogy fictions*) ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ከቴክስቶቹ ውስጥም ጥናቱ ትኩረት ያደረገባቸው የልዊ አልአ.ዩሴ ማርክሳዊ ንድፈ-ሃሳብ የተንፀባረቀባቸውን ሃሳቦች ብቻ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ የደራሲውን ሌሎች ልቦለዶችም ይሁን የሌሎች ደራሲያንን ስራ ይህ ጥናት አይመለከትም፡፡ የጥናቱ መታገኒያ ሙሉ በሙሉ የልዊ አልአ.ዩሴ ማርክሳዊ ንድፈ ሃሳብ ብቻ ነው፡፡ ከሌሎች ሥነ-ጽሑፋዊ ስራዎች በተለየ እነዚህን ቴክስቶች ለጥናቴ መነሻ አድርጌ የመረጥኩበት ምክንያት የልዊ አልአ.ዩሴ ማርክሳዊ ንድፈ-ሃሳብ ጋር መናበብ ይችላሉ ብዬ ስላመንኩ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## 2. ክለሳ ድርሳን

በዚህ ስር ጥናቱ የተመሰረተበት ንድፈ ሃሳብ ምንነትና ፋይዳ ይብራራል፡፡ እንዲሁም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከጥናቱ ጋር ግንኙነት ያላቸው የተዛማጅ ጽሑፎች (መጣጥፎች፣ የቢ.ኤ፣ የኤም.ኤና የፒ.ኤች.ዲ የማሟያ ጥናቶች) ይቃኛሉ፡፡

### 2.1. ንድፈ-ሃሳባዊ ዳራ

በዚህ ክፍል የማህበረሰቡ መዋቅራዊ ዝምድና፣ የመደብ ምንነት፣ የመደብ ልዩነት፣ ርዕዮተ ዓለማዊ ተቃርኖና የመደብ ትግል ጽንሰ ሀሳባዊ ትስስር፤ እንዲሁም የልዊ አልአ.ዩሴ ማርክሳዊ ንድፈ ሃሳብ መሰረታዊ ነጥቦች ይቀርባሉ፡፡

#### 2.1.1. መደብ፣ የመደብ ልዩነት፣ ርዕዮተ ዓለማዊ ተቃርኖና የመደብ ትግል ጽንሰ ሃሳባዊ ትስስር[4]

በመደብ፣ በመደብ ልዩነት፣ በርዕዮተ ዓለማዊ ተቃርኖና በመደብ ትግል መካከል ሰፊ የሆነ ፅንሰ ሃሳባዊ ትስስር አለ፡፡ ፅንሰ ሃሳባዊ ትስስሩም በማህበራዊ ባህሉ፣ በማህበራዊ ፖለቲካዉና በማህበራዊ ኢኮኖሚው መስተጋብር ውስጥ ይበልጥ ይጎላል፡፡

ከማርክሳዊ ንድፈ ሃሳብ አኳያ መደብ[5] በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ በሚካሄድ የምርት ሒደት ውስጥ የሚስተዋል ጽንሰ ሃሳብ ነው፡፡ Edgel (1993፡ 17) ሌኒንን ጠቅሶ መደብን በዐራት መሰረታዊ አቅጣጫዎች ያስረዳል፡፡ አንደኛ የማህበረሰቡ መደብ ምርትን መሰረት

---

[4] Lewis (2005፡ 29-35) *Louis Althusser and the Traditions of French Marxism* በተሰኘው መፅሐፍ ውስጥ አልአ.ዩሴን ጠቅሶ መደብ፣ የመደብ ልዩነት፣ ርዕዮተ ዓለማዊ ተቃርኖና የመደብ ትግል ፅንሰ ሃሳባዊ ትስስራቸውን መሰረት ባደረገ መልኩ መብራራት ቢችሉ የተሻለ ግንዛቤን ማግኘት ይቻላል ይላል፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ፅንሰ ሃሳቦች አይቀሬ የሆነ ተዛምዶ በመሀከላቸው እንዳለ ገልጿል፡፡ ለዚህ ነው በተናጥል ከመበየን ይልቅ ‹‹ፅንሰ ሃሳባዊ ትስስራቸው›› ላይ የማተኩሬ ምስጢር፡፡

[5] እንደ Ilitsraya (1978: 361) ገለጻ መደብ (class) የሚለው ቃል የመጣው *classis* ከሚለው የላቲን ቃል ነው፡፡ ትርጉሙም የተከፋፈለ ህዝብ (*a divission of the people*) ማለት ነው፡፡ የመደብን ጥንተ አመጣጥ ስንመለከት ብዙ አፈታሪኮች የሚነገሩለት የሮማው ንጉስ Servius Tullius (578-534 B.C) አብሮ ይነሳል፡፡ ንጉሱ «የሮማ ማህበረሰብ አዲስ ክፍፍል» በሚል ማህበረሰቡን በተለያየ መደብ ወይም ቅደም ተከተል *(class or order)* ለማስቀመጥ ሞክሯል፡፡ በጊዜው ንጉሱ ሀብታቸውን መስፈርት በማድረግ (ባላቸው የፈረስ ብዛት ወይም ጦር መጠን) ወታደሮችን በተለያየ መደብ መከፋፈሉን ጠቁሟል፡፡

ባደረገ መንገድ ይወሰናል፡፡ ሁለተኛ የርስበርስ ግንኙነታቸው በሚያመርቱት መጠን ይቃኛል፡፡ ሶስተኛ በማህበራዊ ተቋማት ውስጥ ባላቸው ሚና ይመሰረታል፡፡ አራተኛ ተካፍለው ባገኙት ማህበራዊ ሀብት እንዲሁም ሀብቱን ባካበቱበት ዘዴ ላይ ይመሰረታል፡፡ በመሆኑም መደብ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና ርዕዮተ ዓለማዊ መዋቅር ድምር ውጤት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ይህ ድምር ውጤት ለመደብ ልዩነቱ ትልቁን ድርሻ ይይዛል፡፡

Giddens (1982፡ 302) ደግሞ የመደብ ልዩነትን የኢኮኖሚ ልዩነት ብቻ አድርጎ ይወስደዋል፡፡ በአንድ ማህበረሰብ ኢኮኖሚው ስለ መደብ ልዩነቱ ተናጋሪ መሳሪያ ነው፡፡ ስለዚህ ሀብት የማካበቱ፣ የማጣቱ ወይም ብዙ የማምረቱና ያለማምረቱ ጉዳይ ለመደብ ልዩነቱ ዋንኛ ምክንያት ነው ይላል፡፡ Feretter (2006፡ 174) አልኢዩሴን ጠቅሶ ኢኮኖሚ ለመደብ ልዩነት አንድ ምክንያት ተደርጎ ሊጠቀስ እንጂ ዋንኛና ብቸኛ ሰበብ ተደርጎ ሊወሰድ እንደማይችል ይሞግታል፡፡ ለመደብ ልዩነቱ ማህበራዊ ኢኮኖሚው የራሱ ድርሻ እንዳለው ሁሉ ማህበራዊ ፖለቲካና ማህበራዊ ባህሉም ያላቸው ሚና ከፍ ያለ ነው፡፡

በመሆኑም ኢኮኖሚ፣ ፖለቲካና ባህል ቁርኝታቸው ከማህበረሰቡ ንቃተ ህሊና ጋር ሲሆን፤ የነዚህ ርዕሰ ጉዳዮች በማህበረሰቡ ውስጥ ተሰባጥሮ መዘርጋት ደግሞ ለመደብ ልዩነቱ ያለው ድርሻ ከፍተኛ እንደሆነ ያስረዳል፡፡ ለምሳሌ በጭሰኛ ና ባላባት መካከል ግልጽ የሆነ የመደብ ልዩነት አለ፡፡ ይህን የመደብ ልዩነት የፈጠረው ደግሞ ኢኮኖሚው ብቻ ነው ብሎ ደፍሮ ለመናገር አይቻልም፡፡ ምክንያቱም ማህበረ ባህሉና ማህበረ ፖለቲካውም በመደብ መዋቅሩ ላይ ልዩነት የመፍጠር አቅማቸው ከፍተኛ ነው፡፡

ስለሆነም በማህበረሰቡ ውስጥ የየራሳቸው ሚና አላቸው፡፡ አንድም በማህበረሰቡ ማንነት ውስጥ ልዩነትን ይተክሉበታል፡፡ አንድም የተከሉትን ልዩነት ያስጠብቁበታል፡፡ በዚህ ወቅት ከመደብ ልዩነቱ ጋር በተያያዘ ሌላው ጽንሰ ሃሳብ ርዕዮተ ዓለማዊ ተቃርኖ (*ideological antagonism*)[6] አብሮ ይጠነሰሳል፡፡

---

[6] Middendrop, C.P (1978) "Progressiveness and Conservatism: The Fundamental Dimensions of Ideological Controversy and Their Relationship to the Social Class" (ገፅ 1-43) በተሰኘው ጥናቱ በማህበራዊ የመደብ ክፍፍል ውስጥ በጊዜ ሂደት ቀደም ሲል በነበረ አስተሳሰብና አዲስ በመጣ እሳቤ መካከል የሚደረግ ፍጭት (*ideological antagonism*) እንዳለ ያስረዳል፡፡ ፍጭቱም አንዳች የጉሮ «ውላጤ» ሊያስከትል እንደሚችልም ጠቁሟል፡፡ ለውጡም ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ ወይም ባህላዊ ሊሆን ይችላል ይላል፡፡

አልአ.ዩሴ አንድ ማህበረሰብ በጊዜው ከነበረው መንግስት ርዕዮተ ዓለማዊ ፍልስፍና ጋር በተያያዘ በተለያየ የመደብ ክፍፍል ውስጥ ያልፋል ብሎ ያምናል፡፡ ይህ ክፍፍል በጊዜ ሂደት በሚያስነሳው ጥያቄ (ለምን? እንዴት?) አማካኝነት ርዕዮተ ዓለማዊ ተቃርኖ እንዲፈጠር ምክንያት ይሆናል፡፡ ርዕዮተ ዓለማዊ ተቃርኖ የራሱ የሆነ መነሻ ምክንያት ዓለው፡፡ ከኢኮኖሚያዊ የምርት አካሄድ ጋር ያለመጣጣም፣ የፖለቲካ ስርዓቱ ፋይዳ ቢስ መሆን ወይም ባህላዊው የአኗኗር ይትበሃል መጣስ ለተቃርኖው መነሻ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

ይህ ሲሆን ማህበረሰቡ ሌላ ያልኖረበትን ህይወት እንዲመኝ ይገደዳል፡፡ የተወሰነው ማህበረሰብ እየተኖረ ያለው ህይወት የተሻለና ትክክለኛው አማራጭ እንደሆነ ያስባል፡፡ ሌላው ደግሞ አዲስ የኑሮ አማራጭን ይመኛል፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ የሚስተዋለውን እንቅስቃሴ ርዕዮተ ዓለማዊ ተቃርኖ ይለዋል፡፡ (አልአ.ዩሴ፣ 2005፣ 100-9)

የርዕዮተ ዓለማዊ ተቃርኖ በጊዜ ሂደት እየበሰለና እየተጠናከረ መምጣት ለመደብ ትግል መፈጠር ምክንያት ይሆናል፡፡ Althusser and others (2006፡ 38) የመደብ ትግል እንደ አንድ ጽንሰ ሃሳብ ሳይሆን መነሳት ያለበት እንደ አንድ ትልቅ ንድፈ ሃሳብ ነው ሲል አልአ.ዩሴ *Philosophy of the Encounter Later Writings,1978-87* በተሰኘው መጽሐፍ መግቢያ ውስጥ ተሟግቷል፡፡ የመደብ ትግል የርእዮተ ዓለምና የመንግስት ራሱን የቻለ አንድ ደረጃ ተደርጎ ሊታይ እንደሚገባም ጠቁሟል፡፡ ስለሆነም የመደብ ትግል ቁርኝት ከኢኮኖሚው መሰረት ጋር ሳይሆን ከመንግስት የተለያዩ ተቋማት ጋር እንደሆነ ያስረዳል፡፡

Ferretter (2006: 16) አልአ.ዩሴን ጠቅሶ ኤንግልስ እ.ኤ.አ በ1874 *The Pesant War in Germany* በሚል ርዕስ በፃፈው መፅሐፍ መቅድም ላይ ሶስት የመደብ ትግል ቅርፆች እንዳሉ መናገሩን ጠቁሟል፡፡ እነዚህም ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ንድፈ ሃሳባዊ የመደብ ትግል ናቸው፡፡ አልአ.ዩሴ እነዚህን የመደብ ትግል ቅርጾች በአንድ የመንግስት ስርዓት መዋቅር ውስጥ እንደ መሰረታዊ ጉዳይ ተደርገው ሊፈቱሹ እንደሚገባ አስረድቷል፡፡

በአጠቃላይ መደብ፣ የመደብ ልዩነት፣ ርዕዮተ-ዓለማዊ ተቃርኖና የመደብ ትግል አንዳቸው ካንዳቸው ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጽንሰ ሃሳቦች ናቸው፡፡ በመሃከላቸው ያለው የመንስኤና የውጤት ተዛምዶም ከፍተኛ ነው፡፡ ምክንያቱም የጽንሰ ሃሳቦቹ ብያኔ ለየግል የሆነ ባህሪ

አይስተዋልበትም፡፡ ይልቁንም አንዱ ጽንሰ ሃሳብ በሌላው ጽንሰ ሃሳብ ውስጥ የመነሳትና የመብራራት አጋጣሚው ሰፊ ነው፡፡

### 2.1.2. የልዊ አልኢዩሴ ማርክሳዊ ንድፈ ሃሳብ ምንነት

አልኢዩሴ የማርክስና ሌኒን ስራዎች ላይ መሰረታዊ የሆነ የመልሶ ማንበብ *(re-reading)* ተግባር በማካሄድ ይታወቃል፡፡ የማርክሳዊ ንድፈ ሃሳብንም ከመነሻው ጀምሮ ለመመርመር ሞክሯል፡፡

አልኢዩሴ (1971፡ 4) በማርክሳዊ ንድፈ ሃሳብ ውስጥ ስለ ሳይንስና ፍልስፍና ተጠይቆ አብራርቷል፡፡ ማርክሳዊ-ንድፈ ሃሳብ የሳይንስና ፍልስፍና ውጤት መሆኑን ገልጿል፡፡ ምክንያቱም ፍልስፍና ሁሌም ከሳይንስ ጋር ቁርኝት አለው፡፡ ከማርክስ በፊት ሁለት የሳይንሳዊ እውቀት አቅጣጫዎች ተፈጥረዋል፡፡ የመጀመርያው በጋሊሊዮ አማካኝነት የተፈጠረው የሂሳብ ሳይንሳዊ እውቀት *(the continent of mathematics)* ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ በግሪካዊው ትሄለስ (Thales) የተፈጠረው የፊዚክስ ሳይንሳዊ እውቀት *(the continent of physics)* ነው፡፡

ሶስተኛው የታሪክ ሳይንሳዊ እውቀትም *(the continent of history)* በማርክስ አማካኝነት መከሰት መቻሉን አስረድቷል፡፡ ይህን የማርክስ ሳይንሳዊ የእውቀት አብዮት *dialectical materialism* ይለዋል፡፡ ከሂሳብ የሳይንሳዊ እውቀት ውልደት ጋር አብሮ ሌላው ሳይንሳዊ እውቀት ፍልስፍና በአፍላጦን (Plato) አማካኝነት ተወልዷል፡፡ ከፊዚክስ ሳይንሳዊ እውቀት ውልደት ጋር በተያያዘ ፍልስፍና በዲስካርተስ (Descartes) አማካኝነት ለውጥ ማሳየቱንም አብራርቷል፡፡

Simpson and Paul (2006፡ 139) ማርክስን ጠቅሰው ኢኮኖሚያዊ ምርት (መሰረት) ፖለቲካዊ ስልቱንም ሆነ ርዕዮተ ዓለሙን (ወይም ላእላይ መዋቅር) እንደሚወስነው ጠቁመዋል፡፡ ለዚህም በካፒታሊዝም አማካኝነት የዲሞክራሲያዊ ፖለቲካ መጠንሰስን እንደ ምክንያት አድርገው ያነሳሉ፡፡ ጥንታዊው የማርክሳዊ አስተሳሰብ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ ነገሮች በሙሉ ቅርፅ የሚይዙት በኢኮኖሚው (በምርት፣ በልውውጡና በስርጭቱ) መሰረት ነው የሚለው እሳቤ ማእከላዊ ጉዳያቸው ነው፡፡

በጊዜው የነበረውን እንዲህ አይነቱን የባህል ግንዛቤ *economic determinism* ይሉታል፡፡ አልኢዩሴ በነዚህ ውስጥ ያለው የምክንያትና ውጤት ተዛምዶ ቀላል አይደለም ሲል ይሞግታል፡፡ ኢኮኖሚ፣ ፖለቲካና ርዕዮተ ዓለም የምንላቸው ሶስት ጽንሰ ሀሳቦች በአንድ ሀገር ውስጥ ሲኖሩ የራሳቸው የሆነ አንፃራዊ ራስ በቅነት *(relative autonomy)* አላቸው፡፡ በመሆኑም ራሳቸውን ችለው በማህበረሰቡ ውስጥ ሊኖሩ ይችላሉ፡፡

ለዚህም አልኢዩሴ ርዕዮተ ዓለማዊ ለውጥ (*ideological shift*)[7]ን እንደ አስረጅ ይጠቅሳል፡፡ ለምሳሌ፤ የሰብአዊነት እሳቤ መነሳት ለካፒታሊዝም መፈጠር እንደ ውጤት ከሚወሰድ ይልቅ እንደ አንድ ሁነት መታየት ይኖርበታል ይላል፡፡ ምክንያቱም በማህበረሰቡ ውስጥ የሚታይ ማንኛውም ክስተት መነሻና መንስኤው ውስብስብ ነው፡፡

የልዊ አልኢዩሴ ማርክሳዊ ንድፈ ሃሳብ በዐራት መሰረታዊ ፍሬ ነገሮች ላይ ይመሰረታል፡፡ እነዚህም ማህበረሰባዊ ውስብስብ የምክንያትና ውጤት ቁርኝት *(over determinism)*[8]፣ ርዕዮተ-ዓለም፣ ማህበረሰባዊ የግንዛቤና የቁጥጥር ተቋማት እና ማንነትን ማጽናትና ማጎልበት ናቸው፡፡ እነዚህ ፅንሰ ሃሳቦች በባህርያቸው እርስ በርስ የሚደጋገፉና ተወራራሽ ናቸው፡፡ ከዚህ በመቀጠል ፅንሰ ሃሳቦቹን በተናጥል እንደሚከተለው አቀርባለሁ፡፡

### 2.1.2.1. ማህበረሰባዊ ውስብስብ የምክንያትና ውጤት ቁርኝት ምንነት

*over-determinism* በአንድ ማህበረሰብ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ርእዮተ ዓለማዊ፣ ባህላዊ ወዘተ. የአኗኗር ሂደት ውስጥ በነጠላ ጉዳይ ላይ ተመስርቶ የአንድ ለአንድ ትስስር መፍጠርያ መንገድ አይደለም፡፡ Ransome አልኢዩሴን ጠቅሶ ፖለቲካዊ፣ ንድፈ ሃሳባዊና ርዕዮተ ዓለማዊ ማስረጃዎች በማህበረሰቡ መዋቅራዊ ግንኙነት ውስጥ ውስብስብ ሚና እንዳላቸው ገልጿል፡፡ በተወሰነ ረገድ ኢኮኖሚው በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የመሪነት ሚና

---

[7] Sara Schatz and Javier Jesus Gutierrez-Rexach (2002) "Conceptual Structure and Social Change: The Ideological Archtecture of Democratization" (ገፅ 10-35) ርዕዮተ ዓለማዊ ለውጥ የሃሳብ፣ የተነሳሽነት፣ የርእዮተ ዓለም፣ የድርጊትና የማህበራዊ ሃይል (*social force*) ቅንብራዊ ውጤት መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ የእውቀት፣ የርእዮተ ዓለምና የእምነት (*belief*) ቁርኝት አጠቃላይ ምስል የሚሰጠን የማህበረ ፖለቲካዊ ሽግግር (*socio-political transitions*)ን እንደሆነም ገልፀዋል፡፡ ስለዚህ በኢኮኖሚ ላይ ብቻ የተንጠለጠለ አስተሳሰብ እነዚህ የተጠቀሱትን ፈርጀ ብዙ ሃሳቦች ሊያዘነጋ እንደሚችል አብራርተዋል፡፡

[8] Bertram and Others (2001፡ 45) *Intentions and Intentionality: Foundation of Social Cognition* በተሰኘው መፅሐፋቸው over-determinism የሚለውን ፅንሰ ሃሳብ ልዊ አልኢዩሴ ከሲግመን ፍሮይድ መዋሱን ጠቁመዋል፡፡ over-determinism ከፍልስፍናና ከስነ-ልቦና እይታዎች አንፃር በሰዎች ድርጊት ውስጥ ሁለት ስረታዊ መዋቅሮች እንዳሉት ያስረዳሉ፡፡ የመጀመርያው አካላዊ (physical) ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ አእምሯዊ (mental) ናቸው፡፡ ከዚህ አንፃር የነዚህ ሁለት መዋቅሮች ምስጢራዊ ጉድኝት በልዊ አልኢዩሴ ማርክሳዊ ንድፈ ሃሳብ ውስጥም ሚናቸው ተመሳሳይ ይመስለኛል፡፡

እንዳለው ጠቁሞ፤ ሁል ጊዜና በየትኛውም ቦታ በአንድ ሃገር ውስጥ ኢኮኖሚው የበላይ ተቆጣጣሪ ነው የሚለው እሳቤ በማርክሳዊ ንድፈ ሃሳብ ውስጥ በስህተት ተግባራዊ እንደሆነም አስረድቷል፡፡ (Ransome, 2010, 230)

Stephen and Richard (2006፡ 131) አልኢዩሴን ጠቅሰው እንደሚበይኑት *over-determinism* በየትኛውም የአኗኗር ይትበሃል ውስጥ ምክንያትና ውጤት አንድ ላይ የሚመጡበት ማህበረሰባዊ ውስብስብ ዘዴ ነው ይላሉ፡፡ ማህበረሰብ ከአኗኗር፣ ከድርጊት፣ ከፍላጎት፣ ከአመለካከት[9] ወዘተ. አንፃር ቶሎ የማይደርስበት ሰፊ ባህር ነው፡፡ ይህን ሰፊ ባህር ደግሞ በኢኮኖሚው የበላይነት ብቻ ማጤን እንደማይቻል አስረድተዋል፡፡ ስለዚህ በየትኛውም አጋጣሚ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚፈጠር ‹‹ውጤት›› የተለያዩ ምክንያቶችና ድርጊቶች አንድ ላይ በመሆን የሚፈጥሩት እንደሆነም ገልፀዋል፡፡ በመሆኑም ይህ ዕንስ ሃሳብ በ"መሰረት" (base) እና በ"ላእላይ መዋቅር" (super structure) መካከል ያለው የአንድ ለአንድ ግንኙነት ነው የሚለውን ከአልኢዩሴ በፊት በማርክሳዊ ንድፈ ሃሳብ ውስጥ የነበረ ግንዛቤን ያስቀየረ መሆኑንም አብራርተዋል፡፡

Lopez አልኢዩሴን ጠቅሶ የመሰረትና የላዕላይ መዋቅር ተዋረዳዊ ዝምድና ዘይቤያዊ *(metaphor)* መሆኑን ገልጿል፡፡ ላዕላይ መዋቅሩ ለብቻው በአየር ላይ ተንሳፎ ያለ ክፍል ሳይሆን መሰረቱን ተጭኖ የሚኖር መሆኑንም አስረድቷል፡፡ ሁለቱም ያላቸው ሚና ሚዛናዊና ተደጋጋፊ ነው፡፡ ያለመሰረቱ የላእላይ መዋቅር ህልውና ትርጉም እንደሌለውም ጠቅሷል፡፡ ምክንያቱም አንዳቸው ከአንዳቸው ተለያይተው መኖር አይችሉም፡፡ (Lopez, 2003, 133)

Berbes (2011፡ 43-44) አልኢዩሴን ጠቅሶ *over-determinism* የአንድ የሥነ-ፅሁፍ ቴክስት "ውጤት" ተያያዥነት ባላቸው የተለያዩ ምክንያቶች የሚዘጋጅ እንጂ ነጠላ ጉዳይ ላይ ብቻ ተመስርቶ (ለምሳሌ፤ economic motive) የሚቀርብ አለመሆኑን ማሳያ እንደሆነም ገልጿል፡፡ ኪነ-ጥበብ (ስነ-ፅሁፍ) በየትኛውም ቦታ አንፃራዊ የሆነ ራስ-በቅነት

---

[9] Valsiner (2011፡ 90) *Cultural Psychology and Psycho analysis: Path Ways to Synthesis* በተባለው መፅሐፉ ፍሮይድን ጠቅሶ የሰው ልጅ አመለካከትና እምነት ከነጠላ ጉዳይ ይልቅ የተለያዩ ምክንያቶችና ድርጊቶች ላይ የተመሰረቱ መሆናቸውን ገልጿል፡፡ ሰብአዊ አእምሮ ለአንድ ርዕሰ ጉዳይ (ችግር) የተለያዩ መባያ ጉዳዮችን ለማጤንና ለመፈለግ መገደዱ ተፈጥሯዊ መሆኑንም ያስረዳል፡፡ ይህን ያመጣኃበት ምክንያት ‹አመለካከት› በማህበረሰብ ደረጃ ሲታይ ደግሞ ምን ያህል ውስብስብ የሆነ የምክንያትና ውጤት ትስስር ሊፈጥር እንደሚችል ለመጠቆም ያህል ነው፡፡

አለው፡፡ በአልአ.ዩሴ ማርክሳዊ ንድፈ ሃሳብ ውስጥ ሥነ-ፅሑፍ እንደ ባህላዊ ቅርጽ ይቆጠራል፡፡

ስለዚህ ሥነ-ጽሁፍ ከኢኮኖሚያዊ መዋቅር ውጪ ሌሎች የሕብረተሰቡን ጉዳዮች በተለያየ መንገድ የማጤን፣ የመረዳትና የመተርጎም እድሉ ሰፊ ነው፡፡ በኢኮኖሚ ገኘሮነት ብቻ የሚንቀሳቀስ ዲሲፕሊን አይደለም፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የመሰረቱና የላዕላይ መዋቅሩ ግንኙነት በኢኮኖሚው መሸጋገሪያነት ብቻ ሊመዘን እንደማይችል አስረድቷል፡፡ ምክንያቱም ባህላዊ፣ ፖለቲካዊና፣ የተለያዩ እምነትና እሳቤዎች ከኢኮኖሚው ባሻገር በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸው ፋይዳ ጥልቅ ነው፡፡

### 2.1.2.2. የርዕዮተ-ዓለም ምንነት

የትኛውም ማህበረሰብ የሚተዳደርበት የራሱ የሆነ ርዕዮተ ዓለም አለው፡፡ ርዕዮተ ዓለም ከማህበራዊ አመለካከት ጋር ይቆራኛል፡፡ Cavallaro ርዕዮተ ዓለም የሚለው ቃል የተፈጠረው በፈረንሳዊው ፈላስፋ ዲስተት ዲ ትሬሲ (*Destutt de tracy)* እንደሆነ ገልፃለች፡፡ ዕንስ ሃሳቡ ሃሳባዊ ሳይንስ ላይ የሚያተኩር ስለመሆኑም ጠቁማለች፡፡ አልአ.ዩሴና ፋኮ(*Foculț*)ን ጠቅሳ የርዕዮተ ዓለም ተቀዳሚ ተግባር ግለሰቦችን ወደ *subject*[10] አሻግሮ መገንባት እንደሆነም አብራርታለች፡፡ (Cavallaro, 2007, 75)
አልአ.ዩሴ (1971፡ 160) ርዕዮተ ዓለም የሚለውን ጽንሰ-ሀሳብ ከታሪክ አንጻር በአዎንታዊና በአሉታዊ ጎን ይመለከተዋል፡፡ በአዎንታዊ መልኩ ርዕዮተ ዓለም የራሱ የሆነ ታሪክ ዓለው፡፡ ይህም በመጨረሻው ማስረጃ ይወሰናል (በመደብ ትግል አማካኝነት)፡፡ በ*communist manifesto* ውስጥ ታሪክ እንደ መደብ ትግል ተወስዶ ተበይኗል፡፡ ስለሆነም ርዕዮተ አለም የማህበራዊ መደብ ታሪክ ተደርጎም ይቆጠራል፡፡ ከዚህ አንፃር ርዕዮተ ዓለም ታሪክ ያለው ተደርጎ ሊታይ እንደሚችል ገልጿል፡፡

በሌላ በኩል ርዕዮተ ዓለም ታሪክ የለውም የሚለውን ሃሳብ ከፍሮይድ የኢ-ንቁ ልቦና *(unconcious)* እሳቤ ጋር አስተሳስሮ ይገልፀዋል፡፡ ለፍሮይድ ኢ-ንቁ ልቦና የአዕምሮ ጨለማው ክፍል ነው፡፡ ታሪክ የለውም፡፡ ስለሆነም ርዕዮተ ዓለም በሂደት የኢ.ንቁ ልቦናችን

---

[10] Robbins (2012: 64) አልአ.ዩሴን ጠቅሶ *French Post War Social Theory* በተባለው መጸሐፍ 'subject' ማለት ማህበረሰቡ ለራሱ ያጸደቀውና ለሌላው የሚሰጠው "ማንነት" ነው ይላል፡፡ ማህበረሰቡ በማንነቱ ማለት ማህበረሰቡ ለራሱ ያጸደቀውና ለሌላው የሚሰጠው ማንነት ... መሰረት ጎራ ለይቶ እንደሚኖርም ገልጿል፡፡ ግለሰቦች በመደብ ደረጃ እንዲዋቀሩና በራሳቸው ማንነት ውስጥ እንዲኖሩ ትልቁን ሚና የሚጫወቱት የግንዛቤ ተቋማት እንደሆኑም ጠቁሟል፡፡

አካል ሊሆን ስለሚችል የራሱ የሆነ ታሪክ የለውም ሲል ሃሳቡን ያፀናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አልአ.ዩሴ ርዕዮተ ዓለምን በሁለት መንገድ ያስረዳል፡፡ (አልአ.ዩሴ፣ 1971፣ 12)

የመጀመርያው አብዛኛው ንፅረተ ዓለም ከእውነታ ጋር የሚቆራኝና ምናባዊ ነው ይላል፡፡ ስለዚህ ርዕዮተ ዓለም የሰው ልጅ ከሚኖርበት ዓለም ጋር ታርቆ ለመዝለቅ ሲል የፈጠረው ምናባዊ ፅንሰሃሳብ ነው፡፡ ለምሳሌ፤ ልእለ ተፈጥሯዊ ሀይልን በማንሳት ምናባዊ መሆኑን ጠቅሷል፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ርዕዮተ ዓለም በእውናዊው አለም በምንኖርበት ጊዜ ከተለያዩ ነገሮች ጋር ያለንን ትስስር ማሳያ ነው፡፡ ለምሳሌ፤ አንድ በእግዚአብሔር መኖር የሚያምን ሰው ለመፀለይ፣ ለመስገድ፣ ለመፅደቅ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይሄዳል፡፡ ንስሃ መግባቱንም እንደ ተፈጥሯዊ ስርዓት አድርጎ ይወስደዋል፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው ደግሞ ርዕዮተ ዓለም እጅጉን ቁሳዊ ነው ይላል፡፡

የርዕዮተ ዓለምን ምናባዊነት አስመልክቶ Goldstien አልአ.ዩሴን ጠቅሶ የተናገረውን ሃሳብ እንደሚከተለው አቅርቤዋለሁ፡፡

> *ርዕዮተ ዓለም ከምናባችን ወልደን በምናባችን የምናሳድገው ውስብስብ የሆነ የአመክንዮ ውጤት ነው፡፡ በሰዎች ውስጥ የሚስተዋል ምናባዊ ተዛምዶውም ከፍተኛ ነው፡፡ ይህ ርዕዮተ ዓለም የምንለው ጉዳይ አንድ ራሱን የቻለ ስልት ነው፡፡ ስልቱም እንደ አስፈላጊነቱ በአንድ ማህበር ውስጥ በምስል፣ በሚት፣ በሃሳብ ወይም ፅንሰሃሳብ የሚፈጠር አስተማስሎ ነው፡፡* (Goldstien, *23, 1990)*

የሰው ልጅ በተፈጥሮው ርዕዮተ ዓለማዊ እንስሳ ነው፡፡ በህግና ስርዓት መተዳደርን ይሻል፡፡ የራሱን ህይወት የሚመራበትንም ስርዓት ይነድፋል፡፡ በዚህ ሂደትም የሚኖርበትን ዓለም ይተረጉማል፡፡ በመሆኑም ርእዮተ ዓለም በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ሲሰርፅ በጊዜ ሂደት ያልተዛባ ማህበራዊ እውነታ ይሆናል፡፡ እንደ Simpson and Paul (2006: 145) ገለፃ ለአልአ.ዩሴ ርዕዮተ ዓለም ኤንግልስ እንደሚለው የሃሰት ንቃተህሊና አይደለም፡፡ ለአልአ.ዩሴ ርዕዮተ ዓለም ከገቢር ጋር ከፊል ተዛምዶ ያለው ፅንሰ ሃሳብ ነው፡፡ ስለዚህ ርዕዮተ ዓለም የሃሰት ንቃተ ህሊናም ምናባዊ ብቻም አይደለም፡፡ ርዕዮተ ዓለም ለሰው አእምሮ በአዲስ ርዕይ በሂደት የሚዳብርበት መንገድ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በአጠቃላይ ለአልአ.ዩሴ ርዕዮተ ዓለም ከማህበረሰቡ እውነታ ጋር ተዛምዶ የሌለው ምናብ ሰራሽ ብቻ የሆነ ፅንሰ ሃሳብ አይደለም፡፡ ይልቁንም ርዕዮተ ዓለም ለአልአ.ዩሴ ከምናባዊ እሳቤና እውነታ ተገምዶ የተሰራ ፅንሰሃሳብ ነው፡፡

### 2.1.2.3. ማህበረሰባዊ የግንዛቤና የቁጥጥር ተቋማት ምንነት

በአንድ ሀገር ውስጥ (በየትኛውም የፖለቲካ ስልት) የሚኖር ማህበረሰብ በግንዛቤና የቁጥጥር ተቋማት ስርዓት ውስጥ ማለፉ የግድ ነው፡፡ እነዚህ ተቋማት ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ባህላዊ ግንኙነቶችን ማስጠበቂያዎች ናቸው፡፡ በመሆኑም ከርዕዮተ ዓለም ጋር ያላቸው ዝምድና ከፍተኛ ነው፡፡ እንዲያውም የመጠንሰሻ፣ የማደጊያና የመተግበሪያ መንገዳቸው ርዕዮተ ዓለም ነው፡፡

ነገርግን የጽንሰ ሃሳቡን ጅማሬ በተመለከተ Levine የግንዛቤና የቁጥጥር ተቋማት የሚባሉትን ጉዳዮች አልአ.ዩሴ በጥልቀት ይግለፃቸው እንጂ ለመጀመሪያ ጊዜ ሃሳቡን ያመነጨው አንቶኒዮ ግራምሺ (*Antonio Gramsci*) መሆኑን ገልጿል፡፡ እነዚህ ተቋማት እጅጉን ከርዕዮተ ዓለም ጋር የተቆራኙ መሆናቸውንም የጠቆመው ግራምሺ መሆኑን አስረድቷል፡፡ (Levine, 2003, 115)

Eagelton (1991: 18) አልአ.ዩሴን ጠቅሶ ርዕዮተ ዓለም የተወሰኑ ተቋማት የሰው ልጅን ወደ ማህበራዊ Subjectነት የማሻገር ተግባራዊ ተልዕኮን ያዘለ ፅንሰ ሃሳብ ነው ይላል፡፡ ርዕዮተ ዓለም ሃሳብን ከተግባር ጋር የማዛመድ ስርዓት ነው፡፡ በዚህ ስርዓት ውስጥ ማህበረሰቡ እየኖረው ባለው ህይወት እንዲያምን ማድረጊያ እንደሆነ ያብራራል፡፡

አልአ.ዩሴ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ መንግስት የበላይነቱን የሚያውጀው በሁለት መንገድ መሆኑን እንደ መስረታዊ ነጥብ ያነሳዋል፡፡ አንድም በተለያዩ የቁጥጥር ተቋማት ለምሳሌ፣ ፍርድ ቤት፣ የፖሊስና መከላከያ ሃይል፣ ማረሚያ ቤት ወዘተ. በማለት ይዘረዝራቸዋል፡፡ ይህንንም መንግስት እንደ ውጫዊ ሃይል አድርጎ እንደሚያስባቸው ጠቁሟል፡፡ ውጫዊ ሃይል ተደርገው የሚታሰቡበት ምክንያት አመፀኛን ማስታገሻ፣ ወንጀለኛን መቅጫ፣ የመንግስት ሃይል መጠቆሚያ፣ ከፍ ሲል ደግሞ መጨቆኛም (በተለይ ይሄ በአካልም በአመለካከትም ሊሆን ይችላል) ወዘተ. ሆነው የማገልገል ተግባር ያላቸው በመሆኑ እንደሆነ አብራርቷል፡፡

ሌላው በሁለተኛ ደረጃ የሚነሱት የዜጎችን ውስጣዊ ትኩረት ይይዛሉ ተብለው የሚታሰቡ የግንዛቤ ተቋማት ናቸው፡፡ በዚህ ስር የፖለቲካ ፓርቲዎችን፣ ትምህርት ቤቶችን፣ ቤተ-አምልኮዎችን፣ ቤተሰብን፣ የመገናኛ ብዙሃንን (ጋዜጣ፣ ሬዲዮና ቴሌቪዥን)፣ የባህል ግንዛቤ መፍጠርያዎችን (ኪነ-ጥበብ (ስነ-ፅሑፍ)፣ ስፖርት ወዘተ.) ይጠቅሳቸዋል፡፡ እነዚህን ውስጣዊ ሃይል ይላቸዋል፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸው ሚናም ርዕዮተ ዓለሙን የመስበክ፣ የመንግስት ስርዓትን (ህገ መንግስቱንም ሊሆን ይችላል) የማስገንዘብ፣ ከአመለካከት ጋር የተሳሰሩ ሃሳቦችን በሰው አእምሮ ውስጥ የመትከል ወዘተ. መሆኑን ጠቁሟል፡፡ (አልአ.ዩሴ፣ 1971፣ 143)

አልአ.ዩሴ (2005፡156) ለካፒታሊስቶች የበላይ የሆኑት የግንዛቤ ተቋማት የትምህርት ተቋማት እንደሆኑ ያስረዳል፡፡ በተጨማሪም ርዕዮተ ዓለም የቁጥጥርና የግንዛቤ ተቋማት ጥገኛ ሳይሆን፤ የመንቀሳቀሻና የሃሳብ ማስፈፀምያ ማዕከላዊ ምሰሷቸው መሆኑንም ገልጿል፡፡በቁጥጥር ተቋማትና በግንዛቤ ተቋማት መኃል ያለው መሰረታዊ ልዩነት የቁጥጥር ተቋማት የአመፅ ማስቆሚያ ሲሆኑ፤ የግንዛቤ ተቋማት ደግሞ ርዕዮተ ዓለምን የማስገንዘብና የማስፈፀም ተግባር እንዳላቸው አስረድቷል፡፡

በአጠቃላይ የግንዛቤና የቁጥጥር ተቋማት በአንድ ስርወ መንግስት ውስጥ አይቀሬ ማኅበራዊ መዋቅሮች ናቸው፡፡ ምክንያቱም ህግና ደንብ ያስከብራሉ፤ ርዕዮተ ዓለሙን በማህበረሰቡ ውስጥ ይተክላሉ፤ ወዘተ.፡፡ ስለዚህ ተቋማቱ የመንግስት ፈቃድና ፍላጎት ዋንኛ የማስፈፀሚያ መሳሪያዎች ናቸው፡፡

### 2.1.2.4. ማንነትን የማፅናትና ማጎልበት ምንነት

*Interpellation* በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ግለሰቦች በተተከለው ርእዮተ ዓለም አማካኝነት ማንነታቸውን የሚገነቡበት መንገድ ነው፡፡ አልአ.ዩሴ (1971፡ 74-83) ርዕዮተ ዓለም ግለሰቦችን ወደ subject የመለወጥ ተግባር እንዳለው ገልጿል፡፡ ለውጡም በግለሰብ ላይ ብቻ አነጣጥሮ የሚቆም ሳይሆን ሁሉንም ወደ አንድ ጎራ የማምጣት ሂደት ነው፡፡ ግለሰቦች ሁልጊዜ በርዕዮተ ዓለም አማካኝነት ወደ *subject* ይቀየራሉ፡፡ እንዲያውም ግለሰቦች ሁልጊዜ *subject* ናቸው ብሎ ማመን እንደሚቻል ሁሉ ያስረዳል፡፡ ለዚህ የክርስትና ርዕዮተ ዓለምን እንደ ጥሩ ምሳሌ አድርጎ ይጠቅሰዋል፡፡

ለምሳሌ፤ ሰዎች ቤተ-ክርስቲያን ሂደው ይፀልያሉ፣ ይሰግዳሉ፣ ይጠመቃሉ፣ ንስሃ ይገባሉ ወዘተ.፡፡ ይህ ሁሉ ወደ *subject* ለመሸጋገር የሚደረግ ጥረት ነው፡፡ በዚህ ርዕዮተ ዓለም ውስጥ ትልቁ (ፍፁም የሆነው) *subject* ልዕለ ተፈጥሯዊው ሃይል ነው፡፡ ቀጥሎ ልጁ ክርስቶስ ይቀመጣል፡፡ ሰማዕታቱ፣ ቅዱሳኑ፣ መላዕክቱ ወዘተ. ሌላው የትልቁን *subject* መንበረ መንግስት ማዕኛ መንገዶች ናቸው፡፡ የነዚህን መብዛት (*dupilication*) *'The subject in to Subjects and of the Subject itself in to a subject-Subject* መዋቅራዊ አካሄድ እንደሆነ ያስረዳል፡፡ ስለዚህ በዚህ መዋቅር የሚያምኑ ግለሰቦች ራሳቸውን የልዕለ ተፈጥሯዊው ሀይል *subject* አድርገው ስለሚያስቡ ድኅነት (*salivation*) እናገኛለን ብለው ያምናሉ፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የመንግስት ርዕዮተ ዓለማዊ የ*Interpellation* ጣጣ ብዙም ከዚህ መዋቅራዊ አካሄድ የተለየ እንዳልሆነ ያስረዳል፡፡ (አልኢዩሴ፣ 1971፣ 74-83)

Weedon (2004፡ 168-71) አልአይዩሴን ጠቅሶ *Interpellation* በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ግለሰቦች በተተከለው ርዕዮተ ዓለም ተማርከው ወደ *subject* የሚቀየሩበት ሂደት ነው ይላል፡፡ ስለሆነም የበላይ ለሆነው ርዕዮተ ዓለም በሂደት የመሸነፍ፣ በሱ ብቻ ለመተዳደር መቋመጥና ለመገዛት መፍቀድ የ*Interpellation* ጉዳይ መሆኑን አስረድቷል፡፡ *Interpellation* ሰዎች በርዕዮተ ዓለም አማካኝነት ራሳቸውን በተወሰነ ማንነት ውስጥ ከተው «እኔ እንዲህ ነኝ» ብለው የሚያስቡበት ስልት እንደሆነም አስገንዝቧል፡፡ በተጨማሪም ግለሰቦችን በፖለቲካዊ ርዕዮተ ዓለም ውስጥ ሰብኮ የማስገባት ሂደት መሆኑንም ገልጿል፡፡ ማህበራዊ ግንኙነት የሚገነባው በቋንቋ አማካይነት መሆኑን ጠቅሶ፤ በተለያዩ ወገኖች (የፖለቲካ ፓርቲዎችም ሊሆኑ ይችላሉ) መካከል በቋንቋ አማካይነት የሚደረገው ተግባቦት ያላቸውን ልዩነትና ስፍራ ሊጠቁም እንደሚችል አስረድቷል፡፡

በጥቅሉ *Interpellation* በየትኛውም ማህበራዊ ህይወት ውስጥ ሰዎች ማንነታቸውን የሚገነቡበት፣ ጎራ የሚለዩበት (በዘር፣ በሀይማኖት፣ በአመለካከት ወዘተ.) በዚህ ሂደትም ወደ *subject* የሚሸጋገሩበት እሳቤ ነው፡፡

## 2.2. የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት[11]

በዚህ ስር ከጥናቴ ጋር ግንኙነት ያላቸው በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል እንዲሁም በውጭ ቋንቋዎችና ሥነ-ፅሑፍ ትምህርት ክፍል የተሰሩ የቢ.ኤ. ዲግሪ[12]፣ የኤም. ኤ ዲግሪና የፒ.ኤች. ዲ ማሚያ ጥናቶች ይቃኛሉ፡፡ በተጨማሪም የተለያዩ መጣጥፎች ይዳሰሳሉ፡፡ በቢ.ኤ.ዲግሪ ደረጃ ካገኘዋቸው ጥናቶች ውስጥ በይበልጥ ከኔ ጥናት ጋር ይዛመዳሉ ብዬ ያሰብኳቸው በአርጋው ቦጋለ (1974) እና በአብርሃም ታደሰ (1978) የቀረቡት ጥናቶች ናቸው፡፡

አርጋው ቦጋለ (1974) ‹‹የደራሲው ሚና በሶሻሊስት አብዮት ወቅት›› በሚል ርዕስ ጥናቱን አቅርቧል፡፡ የጥናቱ ዋንኛ ዓላማ በሶሻሊስት አብዮት ወቅት የደራሲውን ሚና መግለፅ ነው፡፡ የማጠንጠኛ ሃሳቡ የሶሻሊስት አብዮትን አስፈላጊነት ማግዘፍ ሲሆን፤ የተመሰረተበት ንድፈ ሃሳብ ደግሞ የማህበረሰባዊነት ንድፈ ሃሳብ ነው፡፡ ምክንያቱም ፀናን የሆኑ ማህበረሰብ ተኮር ሃሳቦችን ከደራሲው ጋር አገናኝቶ ሲያስረዳ በብዛት አስተውያለሁ፡፡ በተጨማሪም የሶሻሊስት አብዮት ዓላማና ሙያ አርጅቶ ያፈጀውን የካፒታሊዝም ህብረተሰብ፣ ኢኮኖሚና የፖለቲካ ስርአት ደምስሶ አዲስና ተራማጅ በሆነው ህብረተሰባዊ ስርአት መተካት እንደሆነ በተደጋጋሚ ገልጿል፡፡

አርጋው የሶሻሊስት አብዮትና ኪነ-ጥበባዊ አመለካከቱ፣ ማህበረሰባዊ እውነታ፣ አብዮታዊ ደራሲና የደራሲውን የቀድሞ ማንነትና ምርጫዎች አስመልክቶ ትንተናውን አቅርቧል፡፡ ኪነ-ጥበብ የሚገልፀው ሰውን፣ ባህሪውን፣ አስቦት የሚገኘውን ህይወት ግምትና ዝንባሌ፣ ህሊናዊ ህይወቱን፣ የሚያደርጋቸውን እንቅስቃሴዎችና በዚህም ጊዜ የሚፈጥራቸውን

---

[11] በተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝቱ ስር ካቀረብኳቸው ጥናቶች ውስጥ በውጭ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል የተገኙት ጥናቶች የዘመን አቆጣጠራቸው የአውሮፓ ነው፡፡ ሁለቱ መጣጥፎችና በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል የቀረቡት ዲማጾች ደግሞ የዘመን አቆጣጠራቸው የአበሻ መሆኑ ይተኮርበት፡፡

[12] በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል የተጠኑ ሰባት የመጀመርያ ዲግሪ ዲማፆችን አግኝቻለሁ፡፡ ይልማ ደምሰው (1986) የ‹አደፍርስ›፣ ‹የጉዱ ካሳ› ና ‹የካሳሁን›ን ማህበራዊ እይታ በተመለከተ፡፡ ጥሩዬ ዓለሙ (1979) የማዕበል የገፀ-ባህርያትን አቀራረፅ በተመለከተ፡፡ አፀደ ተፈራ (1979) የማዕበል የብርሃኑ ዘሪሁን ልቦለዶችን ለውጥ በተመለከተ፡፡ ደጀኔ ተሰማ (1982) የ ‹‹ዘግሬፕስ አቭራዝ›› እና የማዕበል የአብዮት ዋዜማና መባቻ የአብዮት ዋዜማ ላይ ያተኮረ ንፅፅራዊ ጥናት፡፡ ገነት ለማ (1975) የማዕበል የአብዮት ዋዜማና መባቻ የአብዮት ዋዜማ ላይ ያተኮረ ንፅፅራዊ ጥናት፡፡ አርጋው ቦጋለ (1974) እና አብረሃም ታደሰ (1978) የሶሻሊስት አብዮትና የቋንቋ ይዞታን በተመለከተ፡፡ አርጋው ቦጋለ (1974) እና አብረሃም ታደሰ (1978) የሶሻሊስት እውነታዊነት ላይ በማተኮር አጥንተዋል (እነዚህ የመጨረሻዎቹ ሁለት ጥናቶች ከሌሎች በተሻለ ለኔ ጥናት ይቀርባሉ)፡፡

አስተሳሰቦችና ስሜቶች እንደሆነ አስረድቷል፡፡ ከዚህም ጋር አያይዞ የሶሻሊስት ሥነ-ጽሑፍ የሚመዘነው በኪነት ጥራቱ፣ ደራሲው ሁኔታዎችን በሚመለከትበት አንፃር (በርዕዮተ አለም) ና በውክልናው የሰፊው ህዝብ ሆኖ ሲገኝ እንደሆነም ገልጿል፡፡ በህብረተሰባዊ እምነት ላይ ለተመሰረተው ሥነ-ጽሑፍ የወዛደሩን ህይወት በትክክል በስራዎቹ ከማሳየቱ አንጻር ማክሲም ጎርኪ ተጠቃሽ ደራሲ መሆኑን ጠቁሟል፡፡

በተጨማሪም ‹‹አብዮታዊ ደራሲ›› በህብረተሰቡ ውስጥ ጎልተው የሚታዩት ችግሮች መንስኤ ምን ምን እንደሆኑ፣ ለምን እንደመጣ፣ እንዴትና በምን እንደሚወገድ በዝርዝር መግለጽ የሚችል እንደሆነም አብራርቷል፡፡ በመጨረሻ አርጋው ሥነ-ጽሑፍ የከበርቴውን ርዕዮተ አለም ዘመቻ ለመቋቋም ከሚያስፈልጉት አንዱ ስለሆነ፤ በሶሻሊስት አብዮት ወቅት ደራሲ የተሟላ አሰራርና ስርዓት እንደሚያስፈልገው በመጠቆም ጥናቱን ቋጭቷል፡፡

የአርጋው ጥናት በአብዛኛው አብዮታዊውን ማህበረሰብ የሚመለከትና በተወሰነ ደረጃ የፊውዳሉን ርዕዮተ አለም የሚሞግት በመሆኑ ከኔ ጥናት ጋር ይመሳሰላል፡፡ በተረፈ ግን አጥኚው ከተመሰረተበት አላማና ግብ አንጻር ከኔ ጥናት ፈጽሞ ይለያል፡፡

አብረሃም ታደሰ (1978) ‹‹የሶሻሊስት እውነታዊነት ፍንጮች በድህረ-አብዮት የአማርኛ ልቦለዶች ውስጥ›› በሚል ርዕስ ጥናቱን አቅርቧል፡፡ የጥናቱ ዋንኛ አላማ ከሥነ ጽሑፍ ዘርፎች ውስጥ አንዱ የሆነው ረጅም ልቦለድ ከድህረ አብዮት በኋላ የሶሻሊስት እውነታዊነት ፍንጮችን በማሳየት ረገድ ያመጣውን ውጤት መመልከት ነው፡፡ ለጥናት የመረጣቸው ረዥም ልቦለዶች *የቀይ ኮከብ ጥሪ፣ ማዕበልና ጣምራጦር* ናቸው፡፡ ጥናቱ ከርዕሱ መለየት እንደሚቻለው በሶሻሊስት እውነታዊነት ጽንሰ ሀሳብ ላይ የተመሰረተ ነው፡ ፡የጥናቱ ማጠንጠኛ ሃሳብ በተመረጡት ሥነ-ጽሑፋዊ ስራዎች ውስጥ የሶሻሊስት እውነታዊነት ፍንጮችን ማረጋገጥ ነው፡፡ አብርሃም የሶሻሊስት አብዮትን ምንነትና ጠባይ በይኗል፡፡

የሶሻሊስት እውነታዊነት አይነተኛ ጠባይ ያለፈውንና ያለውን እውነታ ማንፀባረቅ ሳይሆን የወደፊቱን የህብረተሰብ ብሩህ ተስፋ ማሳየትም እንደሆነ አብራርቷል፡፡ ሶሻሊስት እውነታዊነት ከሌሎች እውነታዊ የጥበብ እንቅስቃሴዎች (‹‹ኪነ-ጥበብ ለኪነ-ጥበብነቱ››፣ ‹‹ተፈጥሯዊነት›› ና ‹‹ሂሳዊ እውነታዊነት››) የሚለይበት ጠባይንም ለመጠቆም ሞክሯል፡፡ በትንተናው ውስጥም ማዕበል *የአብዮት ዋዜማ*፣ *ማዕበል የአብዮት መባቻ* እና ማዕበል

የአብዮት ማግስትን በተወሰነ ደረጃ በተናጥል ለመመልከት ሞክሯል፡፡ ‹‹ማዕበል›› (አብርሃም አንዳንዴ በጥቅሉ ማዕበል እያለ፣ አንዳንዴ ደግሞ ‹‹በቅጽ›› ለይቶ ይጠራቸዋል) ጭቁን ገበሬዎች ብዝበዛ ካለበት ስርዓተ ማህበር ‹‹ነፃነት›› ወዳለበት አዲስ ስርዓተ ማህበር ሲሸጋገሩ የሚያሳይ ልቦለድ መሆኑን ጠቁሟል (ገፅ፣ 39)፡፡

ስራዎቹ ባብዛኛው የማህበረሰቡን የህይወት ገጠመኝ በመግለፅ ላይ ያተኮሩ መሆናቸውንም አስረድቷል፡፡ *ማዕበል የአብዮት ዋዜማ* በሚለው ልቦለድ ውስጥ ገገርው መደብ ከጭቁን ህዝብ ጋር ያለው የመደብ ቅራኔ እንደታየበት ገልጿል፡፡ በ*ማዕበል የአብዮት ዋዜማ* የፊውዳሉ ቡርዥዋ ስርዓተ ማህበር ውስጥ የገበሬዎች ህይወት ጨለማና የከፋ እንደሆነ ጠቁሟል (ገፅ፣ 52)፡፡ ከዚህ የተነሳም በ*ማዕበል የአብዮት መባቻ* ላይ የሰፊው ህዝብ አመፅ ከፍተኛ ደረጃ ላይ መድረሱን አብራርቷል፡፡ በ*ማዕበል የአብዮት መባቻ* ውስጥ የመጀመርያው የመከፋፈል ሁኔታ የተጀመረው የእድገት በህብረት ዘመቻን ለመካፈል ፍቃደኝነታቸውን በገለፁና ባልገለፁ ተማሪዎች መካከል መሆኑንም ጠቁሟል (ገፅ፣ 54)፡፡ በ*ማዕበል የአብዮት ማግስት* ደራሲው «ያንፀባረቀው» አብዮቱ ከፀረ-አብዮት ቡድኖች የተነሳበትን ጥቃቶች ለመቋቋም ያረገውን ትግልና በትግሉም የተቀዳጃቸውን ድሎች መሆኑን ተንትኗል፡፡ አብርሃም ‹‹ሙሄ›› የተባለው ገፀ-ባህርይ በሶሻሊስት ሥነ-ፅሑፍ ውስጥ የሚሳሉት ጀግኖች የሚያደርጉትን ትግል አይነት መፈፀሙን አብራርቷል፡፡ በዝባገሮች ዳግመኛ የብዝበዛ ስርዓታቸውን እንዳያሰፍኑ መታገሉን፣ በመጨረሻም *ማዕበል* የሶሻሊስት እውነታዊነት ፍንጮች የተስተዋሉበት ስራ መሆኑን በመጠቆም ሃሳቡን ጠቅልሏል፡፡

በማርክሳዊ ንድፈ ሃሳብ ውስጥ ማህበራዊ እውነታ አይቀሬ ነው፡፡ በመሆኑም አብርሃም የ*ማዕበል የአብዮት ዋዜማ* ፣ የ*ማዕበል የአብዮት መባቻ* ና የ*ማእበል የአብዮት ማግስት*ን መሰረት አድርጎ ስለማህበረሰቡ ገፅታ ገለፃ ለመስጠት መሞከሩ ከእኔ ጥናት ጋር በቀጥታ ያዛምደዋል፡፡ አንድም ጥናቱን የመሰረተባቸው ሥነ-ጽሑፋዊ ስራዎች የኔም ጉዳይ በመሆናቸው፡፡ አንድም ማህበረሰቡን ይዞ ከገፀ-ባህሪያቱ ጋር በማዛመድ መግለፁ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ አብርሃም ዋንኛ የትኩረት ነጥቡ ድርሰቶቹን ይዞ የሶሻሊስት እውነታዊነትን መፈተሽ በመሆኑ ከኔ ጥናት ይለያል፡፡

በአጠቃላይ አርጋውና አብርሃም በጥናታቸው መጀመሪያ ላይ ይዘው የተነሱትን አላማ ማሳካታቸው፣ የማጠንጠኛ ሃሳባቸውን ያለመዘንጋታቸውና ያለምንም መደናቀፍ

ተያያዥነት ያለው ሃሳብ በጥናታቸው ለማቅረብ መሞከራቸው እንደ ጠንካራ ጎን ሊጠቀስላቸው ይገባል ብዬ አምናለሁ፡፡ ነገር ግን በጥናታቸው ውስጥ ለዘመን መንፈስ የማድላትና ከትምህርታዊ ጥናት ይልቅ የፖለቲካ ጥናት የመምሰል ባህሪይ ይስተዋላል (ድንገት በጊዜው የነበረው ተፅእኖ ይሆን?)፡፡ ለምሳሌ፤ በአርጋው ጥናት ውስጥ መፈክር የሚመስሉ ወገንተኝነት የታጨቀባቸው ሃሳቦች ይታያሉ፡፡

"አዋቂ ደራሲ አብዮታዊ ደራሲ ነው" (ገፅ 21)፡፡ "የሶሻሊዝምን የማይቀር አሸናፊነት፣ የማይካድ ጠቃሚነትና የአድሃሪ ስርአቶችን የማይሸፈን ውድቀት በተግባራዊ መረጃዎች አማካኝነት ማረጋገጥ ይገባል" (ገፅ 22)፡፡ "ከአብዮታችን ፍንዳታ ወዲህ የሥነ-ጽሑፍ ስራ ምን ያህል ሰፊ ድርሻ እንደተሰጠው የሚያጠያይቅ አይደለም" (ገፅ24)፡፡ "በአብዮታዊ ቲዎሪ የተደራጀና፣ የታጠቀ ህዝብ በኪነትም አማካኝነት የነቃ፣ የተደራጀና የታጠቀ እንዲሆን ያስፈልጋል" (ገፅ 30) ወዘተ. የሚሉት ከብዙ ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ እንደ አርጋው የጎላ ባይሆንም የአብርሃም ጥናትም የዚህ አይነቱ ተመሳሳይ ባህሪ ይስተዋልበታል፡፡ ለምሳሌ፤ «ከኪያኒው የሚጠበቀው ሃቅን እንዲያሳይ ሲሆን ዋና ተግባሩ ደግሞ ህብረተሰቡን በሶሻሊስታዊ አስተሳሰብ ማነፅ ነው» (ገፅ 31)፡፡ ይህን እንደ ድክመት ያነሳሁበት ዋንኛ ምክንያት አንድ አጥኚ በየትኛውም መስክ ውስጥ ገለልተኛ በመሆን ያለውን ጉዳይ ያለ ወገንተኝነት ማጥናት ይኖርበታል ብዬ ስለማምን ነው፡፡

የአርጋውና የአብርሃም ጥናቶች የተወሰነ ክፍተትም ይስተዋልባቸዋል፡፡ የአርጋው «የደራሲው ሚና በሶሻሊስት አብዮት ወቅት» የሚለው ጥናት ሃገራዊ ድርሰቶችን ያላናበበና በንድፈ ሃሳብ ብቻ የተሞላ ነው፡፡ በቀረበው ንድፈ ሃሳብ ውስጥ የመደብ ልዩነትን ከደራሲያን ስራ ጋር አያይዞ ለማጤን አልሞከረም፡፡ አብረሃምም በጥናቱ በ"ማዕበል" ውስጥ ያለውን ማህበረሰባዊ መዋቅር በጥልቀት አልፈተሸም፡፡ በስራዎቹ ውስጥ የርዕዮተ አለምን ጣጣ አልቃኘም፡፡ በድርሰቶቹ ውስጥ ማህበረ-ባህሉና ማህበረ-ፖለቲካው ያላቸውን ሚና አላሳየም፡፡ በመሆኑም እነዚህ ክፍተቶች በኔ ጥናት ውስጥ የሚሸፈኑ ይሆናል፡፡

ከጥናቴ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ሁለት መጣጥፎችንም አግኝቻለሁ፡፡ እነሱም ብርሃኑ ገበየሁ (1992) እና በቀለ ገለታ (1968) ናቸው፡፡ ከሁለቱ የበቀለ መጣጥፍ በፖለቲካ ሳይንስ ትምህርት ክፍል ውስጥ የቀረበ መጣጥፍ ነው፡፡

ብርሃኑ ገበየሁ (1992) «ልቦለድ እንደ ርዕዮተ ዓለም መገለጫ» በሚል ርእስ በክቡር ዶክተር ሃዲስ አለማየሁ የ90ኛ ዓመት ክብረ በዓል ላይ መጣጥፉን አቅርቧል፡፡ ጥናቱ የሚያተኩረው *በፍቅር እስከመቃብር*፣ *በወንጀለኛው ዳኛ*ና *የልምዣት* ላይ ነው፡፡ ብርሃኑ እነዚህን ስራዎች መሰረት በማድረግ የማህበራዊ ባህላዊ ተሃድሶንና ማህበራዊ ታሪክን ከርዕዮተ ዓለም ጋር አዛምዶ ገልጿቸዋል፡፡

እነዚህን ጽንሰ ሃሳቦች ያብራራው በደራሲው ስራዎች ውስጥ ተመርጠው በቀረቡ ማህበራዊ አውዶች ነው፡፡ እነዚህ አውዶችም «ትምህርት ቤት»፣ «ጋብቻ» ና «ሽፍትነት» ናቸው፡፡ ብርሃኑ በአውዶቹ ውስጥ ማህበራዊ ባህላዊና ማህበራዊ ፖለቲካዊ ለውጦችን ፈትሿል፡፡ ብርሃኑ መጣጥፉን በርዕዮተ ዓለም ፅንሰ ሀሳብ ላይ መስርቶ ነው ያቀረበው፡፡ የጥናቱ ማጠንጠኛ ሃሳብም "ሃዲስ" ልቦለዶቻቸውን እንደ ርዕዮተ ዓለም መገለጫና እንደ መንፈሳዊ መሳሪያ ተጠቅመውበታል የሚል ነው፡፡

ደራሲው *በፍቅር እስከመቃብር*፣ *በየልምዣት* ና *በወንጀለኛው ዳኛ* ውስጥ ዘመናዊውን የኢትዮጵያ ትምህርት አስመልክተው ያቀረቧቸው ልቦለዳዊ እውነታዎች ከጥናታዊ ዘገባዎች ጋር መጣጣማቸውን ገልጾ፣ ሥነ-ጽሑፋዊ ስራዎቹ የዘመኑን እውነታ በመግለጥ ረገድ የተወጡት ሚና ከፍተኛ መሆኑን ጠቁሟል፡፡ *በፍቅር እስከመቃብር* ውስጥ የዘመናዊ ትምህርት ጣጣ በግላጭ ሳይሆን በትርጓሜ የሚደረስበት መሆኑንም ገልጿል፡፡ የማህበራዊ ዲሞክራሲያዊ ፍልስፍና እምብርት ማህበራዊ ለውጥ፣ ነፃነትና እኩልነት እስከሆኑ ድረስ፤ የለውጡ ተጠቃሚዎች ብቻ ሳይሆኑ ለውጡን የሚያንቀሳቅሱት ማህበራዊ ተቋማት መሆናቸውን አስረድቷል፡፡

ልቦለዳዊ ትረካዎቹ የተወለዱት ከማህበራዊ ፖለቲካዊ ቀውስ ውስጥ ሲሆን፤ የእያንዳንዳቸው ማህበራዊ ታሪካዊ መቼት ደግሞ ቅራኔዎች የተካረሩባቸውና ውዥንብሮች የነገሱባቸው የታሪክ ዘመናት እንደሆኑም አሳይቷል፡፡ *በፍቅር እስከመቃብር* ውስጥ በቀጥታ የማናስተውለው የዘመናዊ ትምህርት ጉዳይ፤ *በየልምዣት* ውስጥ በስርአት ተተክሎ እንደምናገኘውም አስረድቷል፡፡ *ወንጀለኛው ዳኛ*ም በበኩሉ መቼት ካደረገው የታሪክ ዘመን ጀምሮ እስካለንበት የሃያ አንደኛው ምእተ ዓመት መባቻ ድረስ ፖለቲከኞች የሚወዛገቡበትን የትምህርት ስርዓት ጉዳይ ማንሳቱን ጠቁሟል፡፡ በመሆኑም በልቦለዱ

ውስጥ ትምህርት ቤቶች የማህበራዊ ለውጥ ‹‹መቸገኛ (የችግኝ መብቀያ)›› መደቦች መሆናቸውን ገልጿል፡፡

በየልምዣት ውስጥ በተሳሉ ወጣቶች ላይ የምናስተውለው የማንነት ቀውስ ከተዛባ የትምህርት ስርዓት የመነጨ መሆኑንም ተንትኗል፡፡ ብርሃኑ በ"ሃዲስ" ልቦለዶች ውስጥ ያስተዋለው ጋብቻ የፖለቲካ (የመደብ) ቅራኔዎች ወይም ትስስሮች መገለጫ ነው፡፡ በተለይ *በፍቅር እስከመቃብር* ውስጥ ጋብቻ የልቦለዱ መሰረታዊ ፍልስፍና ስግው የሆነበት መዋቅራዊ ቅንብር መሆኑን ተንትኗል፡፡ ጋብቻ ባህላዊ፣ ስነ-ምግባራዊና ማህበራዊ መሰረት ያለው የግለሰቦች ጥምረት መገለጫ ሲሆን፤ ግቡም የህብረተሰብ መዋቅር መሰረታዊ አሃድ የሆነውን ቤተሰብን መመስረት እንደሆነም ዘርዝሯል፡፡

ብርሀኑ በ*ፍቅር እስከ መቃብር* ውስጥ የ‹‹ሰብለወንጌል›› ና የ‹‹በዛብህ›› ፍቅር፤ እንዲሁም የ‹‹ሰብለ››ና የ‹‹ፊታውራሪ አሰጌ›› ጋብቻ በሰብለ ወላጆች ‹‹ከንቱነት›› መገታቱ በማህበረሰቡ ውስጥ ባህል፣ ወግና ልማድ በግለሰቦች ሰብአዊ መብት ላይ የሚያሳድሩትን ልክ የለሽ ተጽእኖ ያመለክታል ይላል፡፡ የ‹‹ካሳ ዳምጤን›› ና የ‹‹አፈረ ጠላቱ›› (የእንቆጳዝዮን)ን ጋብቻ ማህበሩ ሳይባርከው የቀረበት (ሊባርከውም የማይችልበት) ዋንኛ ምክንያት ይህ ገናና እና ስር-ሰደድ ርዕዮተ ዓለም የገገሮውን መደብ ማህበራዊ ቦታና ማንነት፤ የተገኘውን ግዴታና የበታችነት ደንግጎ በማስቀመጡ እንደሆነም ጠቁሟል፡፡ በየልምዣት ውስጥ የ‹‹ታምራት›› ና የ‹‹ደመቀች›› ጋብቻ በ‹‹ታምራት›› ግንባር ሲታይ ፖለቲካዊ ጋብቻ እንደሆነም አሳይቷል፡፡

ምክንያቱም ‹‹ታምራት›› የ‹‹ባሻ ፀሀይ››ን የጋብቻ ዝምድና በፅኑ የሻው፤ ‹‹ባለ ማዕረግ ሰው›› በቤተሰቡ በማስገባት የሚፈራውን ሽሙጥና ሀሜት ለመሸሽ በሚል እንደሆነ ተንትኗል፡፡ *በወንጀለኛው ዳኛም* ውስጥ አባቱ በኮንትሮባንድ ንግድ ባካበተው ገንዘብና በዘመናዊ ትምህርቱ ለመንግስት ስልጣን የበቃው ‹‹ወንድይራድ›› በቤተሰቦቹ በኩል ሊያገኝ ያልቻለውን ‹‹መሰረተ ጌትነት›› የቀኝ አዝማች "ሙላት አራጌ"ን ልጅ (ሶፍያ) ን ለማግባት መጣጣሩ ጋብቻ ፖለቲካዊ አንድምታ እንዳለው ማሳያ መሆኑንም አስረድቷል፡፡

ብርሃኑ ‹‹አመጽና ህጋዊነት››ንም በተመለከተ በ‹‹ሃዲስ›› ስራዎች ውስጥ ያላቸውን መልክ ለማሳየት ሞክሯል፡፡ በልቦለዶቹ ውስጥ የማህበሩ ‹‹ደንበኛ›› አባላት የባህል ተንከባካቢዎች ብቻ ሳይሆኑ፤ ራሳቸው ባህልን የሚወክሉ የወል ንቃተ ህሊና መከሰቻ መልኮች

መሆናቸውን ጠቁሟል፡፡ በተጨማሪም አመጸኞችና ህገወጦች ተደርገው የሚቆጠሩት የለውጥ ሃዋርያት ደግሞ የግለሰባዊ ንቃተ ህሊና ነፀብራቆች እንደሆኑ ገልጿል፡፡ ማህበራዊ ታሪክ፣ የርሱም መከሰቻ የሆኑት ማህበራዊ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ባህላዊ ለውጦች፤ በእነዚህ ሁለት የህብረተሰብ ክፍሎች መካከል የሚፈጠሩ ቅራኔዎች ውጤቶች መሆናቸውንም ተንትኗል፡፡

ማንኛውም አይነት የለውጥ ፍላጎት፣ ሰዎች ያሉበትን አስቸጋሪ ሁኔታ ሲረዱ ወይም የተጫነባቸውን ጭነት ለመሸከም ሲሳናቸው የሚፀነስ መሆኑንም አብራርቷል፡፡ እንደ ብርሃኑ ገለፃ ‹‹ሰብለወንጌል››፣ ‹‹በዛብህ››፣ ‹‹ካሳ ዳምጤ››፣ ‹‹አበጀ በለው›› ፣ ‹‹ደመቀች፣ ‹‹በሻህ››፣ ‹‹አዝማሪው ውቤ››፣ ‹‹ጥላሁን›› እና ‹‹ሶፍያ›› የመሳሰሉት በለውጥ ፈላጊነታቸው ሰብአዊና ግለሰባዊ ነፃነታቸውን የተገፈፉ ሰዎች ናቸው፡፡ በጥቅሉ ሽፍትነት በልቦለዶቹ ውስጥ ለውጥ በሰላም ወይም ‹‹በደም›› የሚመጣ ተደርጎ ቀርቧል፡፡

የብርሃኑ ጥናት ጥልቅ ከሆነ ንድፈ ሃሳብ ተቃኝቶ የቀረበ ነው፡፡ በትንተናው ውስጥም ርዕዮተ ዓለም፣ የወል ንቃተ ህሊናና ግለሰባዊ ንቃተ ህሊና ከማህበረሰቡ ጋር ተቆራኝተው የቀረቡበት መንገድ ግልጽና ፍሰቱን የጠበቀ ነው፡፡ በዚህ መጣጥፍ ውስጥ በማርክሳዊ ንድፈ ሃሳብ መታገጊያነት ሊነሱ የሚገባቸው ፅንሰ ሀሳቦች በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ ተብራርተዋል፡፡ የመደብ ልዩነት፣ የመደብ ትግልና ርዕዮተ ዓለማዊ ተቃርኖ፣ የማህበረሰቡ ማህበረ-ባህልና ማህበረ-ፖለቲካዊ ፋይዳ፣ የነፃነት ጥያቄ፣ የሰብአዊነት እጦት፣ የትምህርት ቤቶች የለውጥ ስፍራ መሆን ወዘተ. ከተነሱት መሰረታዊ ነጥቦች ከብዙ ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ እነዚህ ሃሳቦች በመጣጥፉ ውስጥ መነሳታቸውም ከኔ ጥናት ጋር በቀጥታ ያመሳስለዋል፡፡ በአንጻሩ ደግሞ ከተመሰረተባቸው ድርሰቶች፣ አላማና ግብ አንፃር ከኔ ጥናት ይለያል፡፡ በመሆኑም የኔ ጥናት የማንነት ግንባታን (አመሰራረትን)፣ በማንነት ውስጥ ጎራ ለይቶ የመሳተፍ ጣጣንና የአመለካከትና የድርጊት ቁጥብነትን በማህበረሰቡ ውስጥ የሚፈትሽ ይሆናል፡፡

የብርሃኑ መጣጥፍ ማጠቃለያ ከማጠቃለያነት ይልቅ የ‹‹መደምደምያ›› ባህሪን የያዘ ነው፡፡ ምክንያቱም ሃሳቡን ሚጠቀልለው ቀደም ሲል ያብራራቸውን ጉዳዮች ገፅ በገፅ በመድገም ሳይሆን አንባቢን ለአዲስ ጥናት ሊጋብዙ በሚችሉ ሃሳቦች ነው፡፡ ለምሳሌ፤ ርዕዮተ አለም ከትረካ፣ ካቀራረብ ስልትና ቅርጽ ጋር ያለውን ቁርኝት ለመጠቆም ሞክሯል (ገፅ 69)፡፡

በ"ህዲስ" ስራዎች ውስጥ ገፀ ባህሪያት እንደ አፈ-ታሪካዊ ጀግና *(Legendary Hero)* የተሳሉበትን መንገድ ፍንጭ ሰጥቷል፡፡

እንዲሁም የህዲስ ልቦለዶች ማህል ሽሽ *(Centrifugal)* እና ማዕከለ ብዙ መዋቅሮች *(polycentric)* እንደሆኑ ጠቅሷል (ገፅ70)፡፡ በተለይም *ወንጀለኛው ዳኛ* ከሥነ ኅሳዊ *(ethnographic)* እሳቤ፣ ከነገረ-ስያሜ *(Onomastics)* እና ከባህላዊ ስርዓቶች *(rituals)* አንፃር ሊጠና እንደሚችልም ጥቆማ አድርጓል (ገፅ 73)፡፡ በአጠቃላይ ይዞት የተነሳውን አላማ ማሳካት የቻለና በርእዮተ አለም መነሻነት ከተለያዩ ማርክሳዊ እሳቤዎች በጥልቀት የተቃኘ መጣጥፍ ነው፡፡

ሌላው በቀለ ገለታ (1968) "political socialization in Ethiopia" በሚል ርእስ ያቀረበው መጣጥፍ በተዛማጅ ፅሁፍነት ይጠቀሳል፡፡ የመጣጥፉ ትኩረት አዲስ ርዕዮተ ዓለምን በማህበረሰቡ ውስጥ ለማስረፅ በትክክል በተቀረፀ ካሪኩለም (በትምህርት፣ በመገናኛ ብዙሃን፣ በወጣቶች ማህበር ወዘተ.) አማካኝነት በመዘርጋት ጥንታዊውን መቆጣጠር እንደሚቻል ማስረዳት ነው፡፡ የመጣጥፉ ማጠንጠኛ ሃሳብ ለኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት የማህበረሰባዊነት *(socialism)* ፖለቲካዊ ስርአት ነው የሚል ነው፡፡ መጣጥፉ በማህበረሰባዊነት ንድፈ ሀሳብ ላይ ተመስርቶ የተፃፈ ነው፡፡

በቀለ ፖለቲካዊ ማህበራዊነትን በሁለት አይነት መንገድ ወደ ማህበረሰቡ ማስረፅ እንደሚቻል አስረድቷል፡፡ አንድ በኢ-ንቁ ልቦና አማካኝነት ሳይጠበቅና ሳይታወቀን የምንረዳበትና የምንሳተፍበት አጋጣሚ ነው፡፡ ይህ በማህበረሰቡ ውስጥ የሰው ልጅ የሚያድግበት መንገድ የሚያስከትለው ተፅእኖ መሆኑን አስረድቷል፡፡ በመሆኑም ፖለቲካዊ ማህበራዊነትን ከርዕዮተ አለም ጋር አስተሳስሮ ይመለከተዋል፡፡

ስለዚህ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚያድጉ ልጆች ለተተከለው ርዕዮተ ዓለም ሳይታወቃቸው ተገዥ የመሆን ባህሪን ያዳብራሉ ብሎ ያምናል፡፡ ሁለት ደግሞ ዓላማና ቅርፅ ተነድፎለት ሆን ተብሎ ፖለቲካዊ እምነቱን በሰው አእምሮ ውስጥ መትከል ነው፡፡ እንደ በቀለ እይታ ይሄኛው አካሄድ ብዙ ጊዜ ወጣቶችን ይመለከታል፡፡ አንድም የማህበረሰቡን ትኩስ ሃይል ለመያዝ ስለሚረዳ፡፡ አንድም እንደ ትምህርት ቤት፣ መገናኛ ብዙሃን፣ የተለያዩ ማህበራት ይህን የማስፈፀም ግዴታ ስላለባቸው ነው፡፡ በቀለ የማህበራዊነት (*Socialization*) ተቀዳሚ

ተግባርና ዓላማ (አዲስ በሚቋቋም መንግስት ውስጥ) የተለያየ ጎሳና የተለያየ ቋንቋ ተናጋሪ የሆነውን ማህበረሰብ ወደ አንድ ብሄራዊ ስሜት ማምጣት እንደሆነ ተንትኗል፡፡

በዚህ ውስጥም ያብሮነት ስሜት እንዴት እንደሚዳብር፣ ያለ ቋንቋ ልዩነት እንዴት አንድ መሆን እንደሚቻል አሳይቷል፡፡ በቀለ መጣጥፉን ያጠናው በወለጋና በአሶሳ ማህበረሰብ ናሙናነት (ምልከታ በማድረግ) ነው፡፡ በመጨረሻም ማህበረሰቡ በቀላሉ የሚግባባበት አማራጭና የመንገድ መጓጓዣ እጥረት የባህላዊ ግንኙነትና ትስስራቸውን እንዲቀዘቅዝ እንዳደረገው ገልፆ፤ ሊሻሻል እንደሚገባ በመጠቆም መጣጥፉን ቋጭቷል፡፡ በቀለ በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን የተቋማት ሚና ከርዕዮት ዓለም ጋር አስተሳስሮ መግለፁ ከኔ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል፡፡ ነገር ግን መጣጥፉ ያተኮረው በገሃዱ ማህበረሰብ ላይ በመሆኑና ለፖለቲካ ስርዓቱ ማስፈፀሚያነት ሆን ተብሎ የተሰራ በመሆኑ ከኔ ጥናት ይለያል፡፡

የበቀለ መጣጥፍ የዘመኑን መንፈስ ከፖለቲካዊ ማህበራዊነት ጋር አስተሳስሮ ማቅረቡ፣ በፖለቲካዊ ማህበራዊነት ውስጥ የሚዘረጋው ርዕዮተ ዓለም ያለውን ፋይዳ ማስፈሩና በመጣጥፉ መደምደሚያ ላይ የመፍትሔ ሀሳብ መጠቆሙ እንደ ጠንካራ ጎን ሊታይ ይገባል ብዬ አምናለሁ፡፡ ምክንያቱም መጣጥፉ አንዳች ውጤትን በመሻት የተፃፈ ለመሆኑ አስረጂዎች ናቸው፡፡ ከዚህ ውጭ መጣጥፉ ውስጥ ተጀምረው በጥልቀትና በስፋት መገለፅ ሲገባቸው በንጥልጥል የቀሩ ሀሳቦችንም አስተውያለሁ፡፡ ለምሳሌ፤ "ማህበራዊነት አናሳ ጎሳዎችን የኢትዮጵያዊ ስሜት እንዲያድርባቸው ያደርጋል" (ገፅ 25) ይላል፡፡ ነገር ግን እንዴትና በምን አይነት መልኩ ለዚህ ስሜት እንደሚያበቃቸው አልገለፀም፡፡ ይህ ደግሞ የጥናቱን ተጠየቅ ችግር ውስጥ የሚከት በመሆኑ ድክመት ነው፡፡

ከጥናቴ ጋር ተዛማጅ የሆኑ ለውጭ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል የቀረቡ የኤም.ኤ ማሟያ ፅሁፎችም ይገኛሉ፡፡ እነዚህም የሚካኤል ፍቅረ ማርያም (2008)ና ምስራቅ ታረቀኝ (2002) ናቸው፡፡

ሚካኤል (2008) "The Study of the Influence of Marxism on Bealu Girma's Three Novels: *Haddis, Yekey Kokeb Tiri and Derasiw*" በሚል ርዕስ ጥናቱን አቅርቧል፡፡ የጥናቱ ዋና ዓላማ የበዓሉ ግርማ ስራዎች በማርክሳዊ ንድፈ-ሃሳብ ተፅዕኖ ውስጥ መሆናቸውን ማሳየት ነው፡፡ የጥናቱ ማጠንጠኛ ሃሳብ ደራሲው (በዓሉ) የማርክሳዊ እሳቤ አቀንቃኝ ነው የሚል ነው፡፡ ጥናቱ የተመሰረተበት ንድፈ ሃሳብ ደግሞ ማርክሳዊ ንድፈ-

ሃሳብ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡ የሚካኤል ንድፈ-ሃሳባዊ ዳራ ያለ ቅጥ የተለጠጠና የተመሰረተበትን ንድፈ-ሃሳባዊ አቅጣጫ የዘነጋ ነው፡፡ የተለያዩ ማርክሳዊ ንድፈ-ሃሳብ አቀንቃኞች ስለ ስነ-ፅሁፍ የተናገሩትን በመቃኘት ብቻ ብዙ ገፅ አባክኗል፡፡

ማርክስና ኤንግልስ ስለ ሥነ -ጽሑፍ ያላቸው እይታ (ገፅ 14)፣ ሚሪንግና ፐሌካኖቭ ስለ ሥነ ጽሑፍ ያላቸው እሳቤ (ገፅ 16-17) ወዘተ.፡፡ ይህ ደግሞ የተመሰረተበትን የማርክስ ፍልስፍና በተወሰነ ደረጃ እንዲዘነጋ አድርጎታል፡፡ ሚካኤል "ህዲስ"ን ጠቅሶ የፊውዳሉ ስርዓት በባላገሩ ላይ ያሳደረውን ጭቆናና ብዝበዛ ተንትኗል፡፡ የመደብ ክፍፍሉና ክርስቲያናዊነቱ ለገዥው መደብ ያበረከቱትን ሃይልና ሚዛን አብራርቷል፡፡

የደራሲውን ማርክሳዊ እይታ በገፀ ባህርይው (ህዲስ) ውስጥ ፈትሿል፡፡ ከአብዮቱ በኋላ ኢትዮጵያ የነበራትን ማህበረ-ፖለቲካዊ ሁኔታ ደራሲው በ*የቀይ ኮከብ ጥሪ* ውስጥ ማንፀባረቅ መቻሉን አስፍሯል፡፡ *የቀይ ኮከብ ጥሪ* የገዥ መደቡን ርዕዮተ ዓለማዊ ፍልስፍና ደግፎ የቀረበ ድርሰት መሆኑንም አሳይቷል፡፡ ዋና ገፀ-ባህሪው ሲራክ የበዓሉ አምሳያ መሆኑንም ተንትኗል፡፡ በመረጣቸው ድርሰቶች ውስጥ የደራሲውን አስተሳሰብ ከዋና ገፀ-ባህርያቱ ጋር እያዋሀደ መመልከቱ፣ የዘመኑን መንፈስ በገፀ-ባህሪያቱ አማካይነት መግለፁና የበዝባዥና ተበዝባዥ ስርዓቱን ከርዕዮተ ዓለም አኳያ ማጤኑ የጥናቱ ጠንካራ ጎኖች ናቸው፡፡ በተዛማጅ ፅሁፍ ቅኝቱ ውስጥ ያሰፈራቸውን ጥናቶች ጉድለትና ጥንካሬያቸውን ነቅሶ መቃኘት አለመቻሉ፣ ከመተንተኑ ይልቅ ባብዛኛው ከምንባቡ መጥቀሱ (ይህም የትንተና ሂደቱን ፍዝ አድርጎታል) እና ከፍካሬ ይልቅ በገለፃ ላይ ማተኮሩ የጥናቱ መሰረታዊ ድክመቶች ናቸው፡፡

ሚካኤል የበዝባዥና የተበዝባዥ መስተጋብሩን ማንሳቱ፣ የማህበረሰባዊነት እሳቤን ከርዕዮተ ዓለም ጋር ማቆራኘቱና ከአብዮቱ በኋላ ያለውን ማህበረ-ፖለቲካዊ ግንኙነት መተንተኑ ከኔ ጥናት ጋር በቀጥታ ያመሳስለዋል፡፡ ነገር ግን አጥኚው ከተመሰረተባቸው ሥነ-ጽሑፋዊ ስራዎች እንዲሁም ከነደፈው አላማና ግብ አንፃር እንለያያለን፡፡

ምስራቅ ታረቀኝ (2002) "Alienation in three Amharic Novels: *Fekir Iskemekabir*, *Adafris* and *Kadmas Bashager*" በሚል ርዕስ አጥንታለች፡፡ የጥናቷ ዋንኛ ዓላማ በተመረጡት ድርሰቶች መሰረት እንዴት የሰው ልጅ በተለያዩ ተቋማት ውስጥ እንደሚስተናገድ መግለፅ ነው፡፡ ጥናቷ በማርክስ የባይተዋርነት (*alienation*) ፅንሰ ሃሳብ

ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ የጥናቷ የማጠንጠኛ ሃሳብ *ፍቅር እስከመቃብር፣ አደፍርስና ከአድማስ ባሻገር* የባይተዋርነት ፅንሰ ሃሳብ ማደርያዎች ናቸው የሚል ነው፡፡ ንድፈ-ሃሳባዊ ዳራዋ በርዕሷ ላይ ያሰፈረችውን ፅንሰ ሃሳብ በተመለከተ ብቻ በጥልቀት ከማርክስ አስተሳሰብ አኳያ ተዳሶ የቀረበ ነው፡፡ የመንዛዛትና ከርዕሷ ውጭ የሆኑ ሃሳቦች አይስተዋሉበትም፡፡ ይህን በማድረጓም ለመረጃ ትንተናዋ ግልፅነትና ተያያዥነት ራሱን የቻለ አስተዋፆ አበርክቶላታል፡፡

በመረጃ ትንተናዋ ውስጥ ለራስ ባይተዋር መሆን (*alienation from the self*)፣ ለሰው ባይተዋር መሆን (*alienation of man from man*) ትምህርትና ባይተዋርነት (*education and alienation*)፣ የምሁራን ባይተዋርነት (*intellectual alienation*) በማለት በሶስቱም መጽሀፎች ውስጥ አስገብታ ከፋፍላ ተንትናለች፡፡ በ*ፍቅር እስከመቃብር* ውስጥ የ"ሰብለወንጌል"ንና "የበዛብህ"ን ሃሳቦች በመጥቀስ እንዴት ለራሳቸው ባይተዋር እንደሆኑ ገልፃለች፡፡ ለምሳሌ፤ በዛብህን ጠቅሳ "ጉዋደኞቼ የሚያደርጉትን ለማድረግ እንዳልችል የገዛ እናቴ ፈርዳ ያሳሰረችኝ እስረኛ መሆኔን ተረዳሁና ጠላኋት" (ገፅ 33)፡፡ ምስራቅ በዚህ ውስጥ የበዛብህን የተወሳሰበ ህይወትና ለራስ ባይተዋር መሆን ያመጣውን ጣጣ በጥልቀት ተንትናለች፡፡ በ"ፊታውራሪ መሸሻ" ለምሳሌ ያህል "አባቴ ሰው አይደለም ገበሬ ነው" (ገፅ 41) የሚሉ አመለካከቶች ለሰው ባይተዋር ከመሆን የመነጩ እንደሆኑ አስረድታለች፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በ*አደፍርስ* ውስጥ የሚታየው የ "ወይዘሮ አሰጋሽ" አስተሳሰብ እንዲሁም በ*ከአድማስ ባሻገር* ውስጥ የ"አቶ አባተ ወርቂ" አመለካከት ለሰው ባይተዋር ከመሆን የመነጨ እንደሆነ ተንትናለች፡፡ የገፀ- ባህሪው "አደፍርስ" አመለካከትን በትምህርትና ባይተዋርነት ርዕስ ስር አስረድታለች፡፡

ለምሳሌ፤ "የትምህርታችን ይዞታ እንዲህ እንዲያ ያርገን አይታወቅምኮ....?" (ገፅ74) በሚለው ሀሳቡ አማካይነት የባይተዋርነቱን ደረጃ ለመጠቆም ሞክራለች፡፡ በ*ከአድማስ ባሻገር* ውስጥ "ሃይለማርያም" የተባለው ገፀ-ባህሪ የምሁራኑ ባይተዋርነት ማሳያ እንደሆነም ተብራርቷል፡፡ ለምሳሌ፤ "የተቀጣጠለ ሲጃራ፣ የተዘረጋ መጽሐፍና እንድ ብርጭቆ ውስኪ የልብ ጓደኞቹ ናቸው፤ ከነሱ ጋር ስሆን እዝናናለሁ ይላል አዘውትሮ" (ገፅ 87) የሚለውን ሃሳብ ጠቅሳ የገፀ-ባህሪውን ምሁራዊ ባይተዋረነት በጥልቀት መርምራለች፡፡

የምስራቅ ትንተና ፍሰቱን የጠበቀና በአግባቡ ከተመረጡ ቴክስቶች አንፃር የተቃኘ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡ በጥናቷ ውስጥ የሃሳብ መቆራረጥ አይስተዋልም፡፡ ትንተናዋ በጥልቀትና

በስፋት የቀረበ ነው:: በንድፈ-ሃሳብዋ ውስጥ የተነሳው ፅንሰ ሃሳብና የመረጃ ትንተናዋ በቀጥታ የሚናበቡ ናቸው:: በመሆኑም እንደ ጠንካራ ጎን ሊጠቀስላት ይገባል ብዬ አምናለሁ:: ጥናቷ የድህረ-አብዮቱንና የቅድመ-አብዮቱን ዘመን የሚመለከት መሆኑ፣ የገፀ-ባህሪያቱን አመለካከት ከማህበራዊ መደባቸው እንደሚመነጭ መግለጿ፣ በገፀ- ባህሪያቱ አስተሳሰብ ውስጥ ጥናቷ የተመሰረተበትን ፅንሰ ሃሳብ ለማሳየት መሞከሯ ከኔ ጥናት ጋር ያመሳስላታል::

ከዚህ ውጪ በተመሰረተችበት ፅንሰ ሃሳብ፣ ዘዴ፣ ዓላማ እንዲሁም ሥነ-ጽሑፋዊ ስራዎች አንፃር ጥናቷ ፈፅሞ ከኔ ይለያል:: ጥናቷ በተወሰነ መልኩ የድርስቶቹን ማህበረ-ፖለቲካዊ ህይወት ችላ ማለቱን እንደ ክፍተት አድርጌ ወስጄዋለሁ:: ምክንያቱም በጥናቷ ውስጥ አብዛኛው ትኩረቷ ማህበረ ባህሉ ነበር ብዬ አስባለሁ:: ስለሆነም ይህ ክፍተት በእኔ ጥናት ይሸፈናል::

ሌላው ከጥናቴ ጋር በተዛማጅነት የማነሳው ፍቅሬ ቶሎሳ (1983) ጀርመን ፣ብሬመን ዩኒቨርስቲ ያቀረበውን የፒ.ኤች.ዲ ማሟያ ፅሁፍ ነው::

ፍቅሬ ቶሎሳ (1983) "*Realism and Amharic Literature (1908-1981)*" በሚል ርዕስ ጥናቱን አቅርቧል:: የጥናቱ ዋንኛ ዓላማ በአማርኛ ድርስቶች ውስጥ ገፀ-ባህርያትን፣ ቋንቋንና ትልምን መሰረት በማድረግ የ '*Realism*'ን ፅንሰ ሃሳብ ማሳየት ነው:: ጥናቱ ከሬኒዌሌክ (*Rene Wellek*)፣ ከፍሬደሪክ ኢንግልስ (*Frederick Engels*) እና ከጆርጅ ሉካሽ (*Georg Lukacs*) የእውነታ ፅንሰ ሃሳብ አኳያ የተሰራ ነው::

ፍቅሬ በንድፈ-ሃሳባዊ ቅኝቱ ከፑሽኪን እስከ ጎሪኪ ያለውን የሩሲያ እውነታ እድገት ምን እንደሚመስል አብራርቷል:: የማህበረሰባዊ እውነታንና የሮማንቲሲዝምን እሳቤ አስረድቷል:: ፍቅሬ ብርሃኑ ዘሪሁን የጋዜጠኝነት ባለሙያ እንደነበር፣ የራዲዮ ቴክኒሽያን ትምህርት መቅሰሙን፤ እንዲሁም ወደ ሥነ-ጽሑፍ ዓለም የገባው እ.ኢ.አ በ1960ዓ.ም "የእንባ ደብዳቤዎች" በተባለው የአጭር ልቦለዱ አንደነበርም ገልጿል::

ፍቅሬ የማህበረሰባዊ እውነታ ፅንሰ ሃሳብ በአማርኛ ሥነ-ጽሑፍ ውስጥ የተጀመረው ከ1974ቱ አብዩት በኋላ እንደሆነ ያስረዳል:: የሁለተኛው ቅድመ-ኢትዮ ጣሊያን ጦርነት ዘመን (1908-1935)፣ ከጦርነቱ በኋላ (1941-1956)፣ ዘመናዊው ዘመን (1957-1973) እና ከ1974ቱ አብዮት በኋላ (1979-1981) በማለት የአማርኛ ሥነ-ጽሑፍን በአራት ዘመን

ከፍሎ ለማስረዳት ሞክሯል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ የኔ ጥናት የተመሰረተባቸውን የሥነ-ጽሑፍ ስራዎች በሶስተኛው ዘመን ውስጥ አካቷቸዋል፡፡

ፍቅሬ (በጥናቱ ገፅ 271) *ማዕበል የአብዮት ዋዜማ፣ ማዕበል የአብዮት መባቻ* እና *ማዕበል የአብዮት ማግስት* «መጥፎ» የሚባሉ ስራዎች እንዳልሆኑ ገልፆ፤ በተወሰነ ደረጃ በእውነታ ላይ ተመስርተው እንደተፃፉ ጠቁሟል፡፡ በ*ማዕበል የአብዮት ማግስት* ውስጥ "ካሳሁን" የተባለውን ገፀ-ባህርይ የገጨችውን መኪና "ቦጋለ" ና ጓደኞቹ በተለያዩ ስፍራዎች እየዞሩ መፈለጋቸው በዘመኑ አይን ሲታይ ከእውነታ የራቀ ነው ሲል ተንትኗል (ገፅ 168)፡፡ የቋንቋ አጠቃቀማቸውን በተመለከተ ድርሰቶቹ በአካባቢያዊ ዘዬ የተሞሉ መሆናቸውን አሳይቷል፡፡ ገፀ-ባህርያቱንም ተንተርሶ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል የፊውዳሉ ስርዓት ወኪል ሊሆኑ እንደሚችሉ ጠቁሟል፡፡ የማስረሻ ስነ-ልቦናዊ ስቃይ ምን እንደሚመስል፤ እንዲሁም ደራሲው በ "ሙሄ አየለ" ውስጥ ሙሉ በሙሉ የገበሬውን ገፅታ እውነታን መሰረት ባደረገ መልኩ እንደሳለውም ተንትኗል፡፡

ፍቅሬ በአማርኛ ሥነ-ጽሑፍ ውስጥ ያሳየው የዘመን አከፋፈሉ፣ ሥነ-ጽሑፋዊ ስራዎቹንና ደራሲዎቻቸውን አስተሳስሮ ቅኝት ማድረጉ እንዲሁም የቋንቋ ደረጃቸውን ድክመትና ጥንካሬያቸውን መገምገሙ እንደ መልካም ጎን ሊጠቀስለት ይገባል ብዬ አምናለሁ፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ የሃገራችንን ሥነ-ጽሑፍ በዘመንና በባህል ከሚለያየው ከሩሲያ ሥነ-ጽሑፍ ጋር ለማነፃፀር መሞከሩ የጥናቱ አንድ ድክመት ነው፡፡ በተጨማሪ (በጥናቱ ገፅ 4) "የብርሃኑ ዘሪሁን *ማእበል የአብዮት ዋዜማ፣ መባቻና ማግስት* *Party organization and party literature* በሚለው የሌንን ስራ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ነገር ግን ደራሲው በአንድ ወቅት ቃለ መጠይቅ ተደርጎለት ይህን ጉዳይ አልገለፀውም" ሲል አስፍሯል፡፡

ፍቅሬ በዚህ ሃሳቡ ውስጥ ደራሲው ተጠይቆ ላለመመለሱ ያስፈረልን ምክንያት የለም፡፡ ወይም በጠቀሰው የሌኒን ስራ ውስጥ የተነሱ ሃሳቦችን ገፅ በገፅ ከደራሲው ስራ ጋር አናቦ አላስረዳም፡፡ እንዲሁ በስሚ ስሚ ያስፈረው ሃሳብ ይመስለኛል፡፡ ፍቅሬ ሃሳቡን ካነሳው ላይቀር ቢያንስ ከጠቀሰው ስራ ውስጥ የተወሰነ ሃሳብ መዞ አዋግኖ በመተንተን በአመክንዮ ላይ የተመሰረተ ማጠቃለያ ላይ ሊደርስ በተገባ ነበር፡፡ ይህንን ባለማድረጉ በጥናቱ ውስጥ ያነሳው ሃሳብ ያልተቋጨ (በጅምር የቀረ) እንዲሆን አድርጎታል፡፡ ስለሆነም ለጥናቱ ድክመት ተጨማሪ ማስረጃ ሆኗል፡፡ ፍቅሬ *ማዕበል የአብዮት ዋዜማ፣ ማዕበል የአብዮት መባቻ* እና *ማዕበል የአብዮት ማግስትን* በመደብ ደረጃ ለማጤን መሞከሩ ከኔ ጥናት ጋር

ያመሳስለዋል፡፡ ጥናቱ ከተመሰረተበት ዓላማና ግብ አንፃር፣ መታገጊያ ካደረገው ንድፈ ሃሳብና ከስፋቱ አኳያ ከኔ ጥናት ይለያል፡፡

ቀደም ሲል በጠቀስኳቸው ተዛማጅ ፅሁፎች ውስጥ በቅኝቴ ወቅት የጥናት ዘዴያቸውን ያላሰፈርኩት፤ አጥኚዎቹ የተገለገሉበት «ዘዴ» የምር ዘዴ ነው ወይ? የሚል ጥያቄ ስላለኝ ነው፡፡ ብርሃኑ፣ በቀለ፣ አርጋውና ቦጋለ የጥናት ዘዴያቸው "ገለጻ" ነው፡፡ ሚካኤል "ፍካሬ"ን፤ ምስራቅ ደግሞ "ገለፃና ፍካሬ"ን አንድ ላይ በማዋገን እንደ ዘዴ ተጠቅማለች፡፡ ፍቅሬ ምንም እንኳን ቃል በቃል ያሰፈረው የጥናት ዘዴ በስራው ውስጥ ባላስተውልም፤ ከጥናቱ አጠቃላይ ባህሪ በመነሳት ግን "ገለፃ"ን እንደ ዘዴ አድርጎ የተጠቀመ ይመስለኛል፡፡ ይሁን እንጂ በአንድ ጥናት ውስጥ "ገለፃ"፣ "ትንተና"፣ "ፍካሬ" ወዘተ. የሚባሉት ጉዳዮች ያላቸው የዘዴነት ሚና አይደለም፡፡ ይልቁንም በጥናቱ ውስጥ ለማስረዳት የተፈለገውን ርዕሰ ጉዳይ በሂደት የማዳበርያና የማጎልበቻ መንገዶች ናቸው፡፡ ሚናቸው የጥናት ስልት (*Technique*)[13] መሆን ነው፡፡

ለአንድ ጥናት ዘዴ አጋዥ ሆነው ማገልገል የሚችሉ መሳሪያዎች ናቸው፡፡ ነገር ግን በራሳቸው የዘዴን ተግባር መሸፈን አይችሉም፡፡ በጥናት ውስጥ አንድን ርዕሰ ጉዳይ በገለፅን ቁጥር መተንተናችን፤ በተነተን ቁጥር መፈከራችን፤ በፈከርን ቁጥር ደግሞ መግለፃችን ሊያጋጥም ይችላል፡፡ ስለሆነም ተግባራቸው ከንድፈ ሃሳቡ ጋር ተናቦ የመጣውን ዘዴ ማጉላት ነው፡፡ ነገር ግን እነዚህን እንደ ዘዴ አድርጎ መጠቀም፤ አንድም የተመረጠውን ንድፈ-ሃሳብ ሃይልና ደረጃ ያሰንፈዋል፡፡ አንድም የትኛውም ሰው ሊያውቀው የሚችለውን ጉዳይ በጥሬው ማቅረብ ይሆናል፡፡ በጥቅሉ ጥናቶቹ ስልት እንጂ ዘዴ የላቸውም ብሎ ማጠቃለል ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ጥናቱን ለመሰረቱበት ንድፈ-ሃሳብ

---

[13] Taylor (2005: 256-59) *Integrating Quantitative and Qualitative Methods in Research* በተባለው መፅሐፉ "ፍካሬ"፣ "ገለፃና" "ትንትና"ን አንድን ርዕሰ ጉዳይ መናገርያ ወይም ማስረጃ ስልቶች እንደሆኑ ገልፆ፤ በተለይም ደግሞ በነገረ-ሰብዕ (*Humanities*) የሙያ መስክ ውስጥ ያላቸው ሚና ስልት ሆኖ ማገልገል እንደሆነ ጠቁሟል፡፡ በተጨማሪም በአንድ ጥናት ውስጥ ዘዴ ከንድፈ-ሃሳቡ ጋር በቀጥታ መናበብ (አንድም በባህሪ፣ አንድምበተግባር) የሚችል እንዲሁም አጥኚው በጥናቱ ውስጥ የሚንሸራሸርበትን ስፍራ የሚያበጅ መሆኑንም አስፍሯል፡፡

የተጨነቁትን ያህል ለጥናት ዘዴያቸው ባለመጠበባቸው በስራቸው ላይ ብዥታ ፈጥሯል ብዬ አምናለሁ፡፡

በአጠቃላይ የጥናታቸው "መደምደሚያ"ም በተመሳሳይ መልኩ ድክመት ይታይበታል፡፡ መደምደሚያቸው እንደ ማጠቃለያ ሆኖ የቀረበ ነው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ቀደም ሲል በትንተናታቸው ያነሱትን ርዕሰ ጉዳይ አሳጥሮ በማቅረብ ባህሪይ ተጠምደዋል፡፡ ለምሳሌ፣ በምስራቅ ጥናት መደምደሚያ ውስጥ (ገፅ 93-94) ጭምቅ ሃሳቡ የዘመናዊ ትምህርት አሳቤና አመለካከት ከፍቅር እስከ መቃብር በተሻለ መልኩ በአደፍርስና በክአድማስ ባሻገር ውስጥ መነሳቱን ጥቅል በሆነ መልኩ የሚያነሱ ናቸው፡፡ፍቅሬ ቶሎሳም እንደዚሁ (ገፅ 285) ስለ አማርኛ ስነ-ፅሑፍ የግል አስተያየት ነው ሚሰነዝረው (ለምሳሌ፣ ስነ-ፅሁፉ እንዲያድግ ፎክሎሩ ማደግ አለበት)፡፡

ሚካኤልም በዓሉና ስራዎቹ የሶሻሊስት ርዕዮተ ዓለም ማሳያ መሆናቸውን ጠቅሶ ነው ሚቋጨው፡፡ ስለሆነም የአንባቢን አይን ሊከፍት የሚችል አዲስ ሃሳብ አይስተዋልባቸውም፡፡ በአንድ ጥናት መደምደሚያ ውስጥ አንባቢን ለሌላ ተጓዳኝ አዲስ ርዕስ የሚጋብዝ ሃሳብ መስጠት (መጠቆም) ተገቢም አስፈላጊም ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ ነገር ግን አንዳቸውም ይህን አላደረጉም፡፡ በመሆኑም የጥናታቸውን "መደምደሚያ" ደካማ አድርጎታል፡፡ ይሁን እንጂ በጥናታቸው መጀመሪያ ይዘው የተነሱትን ዓላማ በጥናታቸው መጨረሻ ማሳካታቸው ዋንኛ የጥንካሬያቸው መለያ ነው፡፡

## ምዕራፍ ሶስት

# 3. የመደብ ልዩነትና ርዕዮተ ዓለማዊ ተቃርኖ በማዕበል የአብዮት ዋዜማ፣ በማዕበል የአብዮት መባቻ እና በማዕበል የአብዮት ማግስት፣ ከልዊ አልአይዩሴ ማርክሳዊ ንድፈ ሐሳብ አንፃር

## 3.1. ርዕዮተ ዓለማዊ መነሻ በ'ባላገሩ'ና በ'መሳፍንቱ' ማሳያነት

ርዕዮተ ዓለም የሰውን ልጅ አእምሮ ለመገንባት ይረዳል፡፡ በድርሰቶቹ ውስጥ የባላገሩና የመሳፍንቱ መደብ የተገነባበት ርዕዮተ ዓለም አለ፡፡ ይህ ርዕዮተ ዓለም ሁለቱንም ወገኖች በአመለካከትና በእምነት ደረጃ በአግባቡ ቅርፅ ያስያዘ ይመስለኛል፡፡ ስለሆነም ከሁለቱም ወገን ወካይ ገፀ-ባህርያትን በመውሰድ ርዕዮተ ዓለማዊ መነሻቸውንና ያላቸውን የጋራ እሳቤ አስረዳለሁ፡፡ ከባላገሩ ወገን 'ካሳሁን'ን ከመሳፍንቱ ጎራ ደግሞ 'ወይዘሮ ዘርፈሽዋል' ለዚህ ሃሳብ ተገቢ አስረጅ ይሆናሉ ብዬ አምናለሁ፡፡

“ካሳሁን … የሚያውቀው የግፍ ዘመን መሆኑን ብቻ ነው፡፡ እሱ ያመጣውን እሱ እስኪመልሰው አለ” (*ዋዜማ*፣ 192)፡፡ በዚህ ጥቅስ ውስጥ የሚነበበው የካሳሁን ግላዊ አመለካከት ሳይሆን መላው የባላገሩ ስሜት ነው፡፡ 'እሱ' የተባለው ጉዳይ ሰማይና ምድርን የፈጠረው ልዕለ ተፈጥሯዊው ሃይል ነው፡፡ ይህ ሃይል የህልውናቸው ባለቤት ነው፡፡ በመሆኑም ካሳሁን የሚያውቀው «የግፍ ዘመን» መሆኑን ብቻ ነው፡፡ 'ግፍ' በልዕለ ተፈጥሯዊው ሃይል ትዕዛዝ ብቻ እየተፈፀመ እንዳለ አድርጎ ያስባል፡፡ አንድም 'እሱ' የፍጡሩ ሁሉ የበላይ በመሆኑ ነው፡፡

አንድም የሚሾምና የሚሽር 'እሱ' ብቻ ነው፡፡ አንድም በ'እሱ' ስራ ውስጥ ጣልቃ ገብቶ መዶለት ሀጥያት ነው፡፡ “እሱ ያመጣውን እሱ እስኪመልሰው” የባላገሩ የኑሮ ፍልስፍና አጠቃላይ ውጤት ነው፡፡ የመኖራቸው ምስጢር 'እሱ' ነው፡፡ ያስተዳድራችሁ ሲል መርጦ የሾመላቸውም 'እሱ' ነው፡፡ አርሰው እንዳይበሉ የስደትና የርሃብ ምርኮኛ ያደረጋቸውም እንደዚሁ 'እሱ' ነው፡፡ በሚኖሩበት ስርዓት ውስጥ 'እሱ' የርዕዮተ ዓላማዊ ፅንሰ ሃሳቡ መነሻ ስፍራ ነው፡፡ ለሁለቱም ማህበር ስርዓታቸው በግለሰብ አመለካከት የተገነባ አይደለም፡፡ ይልቁንም 'እሱ' መርጦ ቀብቶ የሾመው፣ በእርሱ መሪነትና ቀያሽነት ወዘተ. የተመሰረተ

ነው፡፡ በህይወታቸው ውስጥ 'እሱ' ትልቅ ስፍራ ዓለው፡፡ ለዚህ ማሳያ የሚሆነን ከብዙ እልቂት በኋላ ዝናብ ሲዘንብ አንዱ ባላገር የተናገረው ጉዳይ ነው፡፡

"ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ አሉ፡፡ ከአለቅን በኋላ አሁን ቸርኩ ማለቱ ነው ፈጣሪ?" "ተው በእሱ ላይ ክፉ አትናገር! ሲል አንዱ ኮስተር ብሎ ይገስፃል" (*መባቻ*፡ 89)፡፡ በዚህ ውስጥ የምንረዳው ሁለት ለየቅል የመሰሉ ሃሳቦች አሉ፡፡ የመጀመሪያው ነባሩን አመለካከት የሚሸር ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ቀደም ሲል የነበረውን የባላገሩን ግንዛቤ መልሶ የሚያፀና ነው፡፡ 'ካለቅን በኋላ አሁን ቸርኩ ማለቱ ነው ፈጣሪ?' የሚለው የፈጣሪን ህልውና ጥያቄ ውስጥ የሚከት ሃሳብ ነው፡፡

አንድም አለ? ወይስ የለም? የሚል ሃሳብ ያጭራል፡፡ ስለሆነም የመኖር ህልውናውን ይፈታተናል፡፡ አንድም ጥርጣሬውን የለም! ወደሚል ድምዳሜ የሚያሳድግ ሃሳብ ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ሃሳብ 'ተው በእሱ ላይ ክፉ አትናገር!' በሚል ተጓዳኝ ሃሳብ ወዲያው ይሻራል፡፡ ምክንያቱም 'እሱ' በህይወታቸው ውስጥ ትልቅ ትርጉም ዓለው፡፡ አንድም 'ተው' የሚለው ግሳፄ 'እሱ' በገነባውና ማህበሩ ባጸደቀው ሚቶሎጂ ውስጥ ከቶ ለሌሎች ማስተማሪያ እንዳያደርግህ ማለቱ ነው፡፡ አንድም አንድዬን አትፈታተነው የሚል ነው፡፡ አንድም ይክሰናል ነው፡፡ ስለዚህ በ'እሱ' ስራ ውስጥ ማንም ጣልቃ ሊገባ አይችልም፡፡ የሚሰጥ የሚነሳ፤ የሚሾም የሚሽር 'እሱ' ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም እየኖሩበት ያለው ርዕዮተ ዓለም የሚመዘዘው ከ'እሱ' ነው፡፡ 'እሱ' በመሳፍንቱ ወገንም ቢሆን በተቀራራቢ መልኩ የሚታይ ነው፡፡

"...ቀብቶ የፈጠራቸው ስለሆነ ቁም ነገሩ ተፈጥረው ወደ ዓለም የመጡበት ጊዜ ነው፡፡" (*ማግስት*፡ 57)፡፡ ቀብቶ በመፍጠር ውስጥ የምናገኘው 'እሱ'ን ነው፡ ለዚህ ማህበረሰብ መርጦ ቀብቶ የሚሾመው ልዕለ ተፈጥሯዊው ሃይል ነው፡፡ ከዚህ አንፃር በባላገሩም ሆነ በመሳፍንቱ ወገን እየኖሩበት ያለው ርዕዮተ ዓለም መነሻው 'እሱ' ነው፡፡ ንጉሱ ሁል ጊዜ የሚታዩት በ'እሱ' መነጽር ነው፡፡ ምክንያቱም በዓላማ የተፈጠሩ ናቸው፡፡ አፈጣጠራቸውም እንደማንኛውም ሰው ይኖሩ ዘንድ ብቻ ሳይሆን ሊመሩም ነው፡፡ ስለዚህ 'ቁም ነገሩ ተፈጥረው ወደ ዓለም የመጡበት ጊዜ ነው፡፡' አመጣጣቸው እንዲሁ በዘፈቀደ አይደለም፡፡ በተልዕኮ ነው፡፡ አንድም ከላይ ውክልና ያላቸው በመሆኑ በ'እሱ' ምርጫ የጸኑ ናቸው፡፡

አንድም የፈለጉትን ያደርጉ ዘንድ ባለሙሉ መብት ያላቸው መሆኑን ማሳያ ነው፡፡ አንድም በመሳፍንቱና በባላገሩ መሃከል የተዘረጉ ንድፈ-ሃሳብ የመሆናቸው ምስጢር ነው፡፡ በንጉሱ መነሻነት መሳፍንቱ የፈለጉትን ያደርጋሉ፡፡ በንጉሱ መነሻነት ባላገሩ የተባለውን ሁሉ ይቀበላል፡፡ ይህ በዚህ ርዕዮተ ዓለም አማካይነት የተዘረጋ የማይሻር የህይወት ዑደት ነው፡፡ እምቢ ባይ አይኖርም፡፡ በ'እሱ' መነፅር የሚታይ በንድፈ-ሃሳብ የገዘፈ አካል አለ፡፡ ባላገሩም ሆነ የመሳፍንቱ ወገን በተዘረጋው ርዕዮተ ዓለም ቅርፅ እንዲይዙ ተደርጓል፡፡ ርዕዮተ ዓለም ተግባሩ መጨቆን አይደለም፡፡ ተግባሩ አዕምሮን መገንባት (ቅርፅ ማስያዝ) ነው፡፡ ባላገሩ አርሶ፣ ለፍቶ፣ አርብቶ ወዘተ. ለመኳንንቱ፣ ለመሳፍንቱና ለባላባቱ መገበር እንዳለበት አምኖ እንዲቀበል የሚያደርገው ርዕዮተ ዓለሙ ነው፡፡ መሳፍንቱም ከባላገሩ ግብር መቀበል እንዳለበት ልቡናውና አእምሮው የሚያምነው በርዕዮተ ዓለሙ አማካኝነት ነው (ይህ ማለት ግን ርዕዮተ ዓለሙ ሁሌም ትክክል ሁኖ ይዘልቃል ማለት አይደለም)፡፡

በአጠቃላይ በድርሰቶቹ ውስጥ ባላገሩና መሳፍንቱ የኖሩበት ርዕዮተ ዓለም መነሻ 'እሱ' (ልዕለ ተፈጥሯዊው ሃይል) ነው፡፡ የርዕዮተ ዓለሙ መነሻ የማህበረሰቡን አመለካከትና እምነት ከግምት ውስጥ በመክተት (የሃይማኖቱ ተፅእኖ ሳይዘነጋ) የተዘረጋ ነው፡፡

## 3.2. ማንነትን ማጽናትና ማጎልበት እንደ መደብ ልዩነት

በዚህ ስር መሳፍንቱና ባላገሩ በማንነታቸው መሰረት ያላቸው ወገንተኝነት ይፈተሻል፡፡ በዚህ አማካኝነትም እንዴት የመደብ ልዩነት እንደሚጎላ ይተነተናል፡፡ እንዲሁም በግለሰብ ደረጃ የሰው ልጅ በርዕዮተ ዓለም አማካኝነት ወደ አዲስ ማንነት የሚሻገርበትም መንገድ በ"ካሳሁን" ማሳያነት ይብራራል፡፡

### 3.2.1. የመሳፍንቱና የባላገሩ ወገንተኝነት (በ"ማንነት" መነፅር)

ጎራ ለይቶ መቆምን ከመደብ ልዩነት ጋር አያይዞ ማየት ይቻላል፡፡ የመደብ ልዩነት በሆነ ጉዳይ ላይ ተመስርቶ ራስን ወደ አንድ ወገን *subject* ከማድረግ ጋር በቀጥታ ይያያዛል፡፡ ይህ ጉዳይ በመሳፍንቱ አስተሳሰብና በባላገሩ አመለካከት ውስጥ እንዴት እንደተስተዋለ አስረዳለሁ፡፡

"እንደ አይነቱ ነው! ሰው የተባለው ሁሉ አንድ አይደለም፡፡ እንደዘሩ እንደ አይነቱ ነው፡፡ አሉ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ተኮፍሰው" (*መባቻ፣* 139)፡፡ በዚህ ጥቅስ ውስጥ 'አይነት' እና 'ዘር'

የተባሉት መሰረታዊ ጉዳዮች ናቸው፡፡ የሁሉቱም የመጨረሻ ግብ ልዩነት መፍጠር ነው፡፡ ፊፅሞ ሌላው ካንዱ ወገን ጋር አንድ ሊሆን አይችልም፡፡ ወይዘሮ ዘርፊሸዋል በዚህ ልዩነት የሚያምኑ ሰው ናቸው፡፡ ከሰው ልጅ የአፈጣጠር ሂደትና ደንብ በመውጣት ለሰው ዓይነት ያበጁለታል፡፡ በወይዘሮ ዘርፊሸዋል አመለካከት የሰው ልጅ አንድም እኩል አይደለም፡፡ አንድም እንደየፈርጁ ይመደባል፡፡ አንድም የሰው ትርጓሜ ለሳቸው 'ልዩነት' ነው፡፡ በሳቸው ርዕይ የሰው ልጅ በልዩነት ውስጥ ኑሮ በልዩነት ውስጥ የሚያልፍ እንስሳ ነው፡፡ ዘርና ዓይነቱ በውስጥ ታዋቂነት የመደብ ጣጣ አለበት፡፡ በልዩነት ውስጥ መደብን፣ በመደብ ውስጥ ልዩነትን መረዳት የግድ ነው፡፡ የህይወት ፍልስፍናቸውም ከዚህ ውጭ አይደለም፡፡ አንድም ልዩ ሆነው መኖርን ይሻሉ፡፡ አንድም የተለዩትን ይንቃሉ፡፡

ዘር ጥሩ፣ ሚረባ፣ ማይረባ ወዘተ. እየተባለ ስም ሊወጣለት የሚችል ባህሪ ዓለው፡፡ በዘር ውስጥ አይነት፣ በአይነት ውስጥ ዘር አለ፡፡ ወይዘሮ ዘርፊሸዋል ሙሉ ህይወታቸው የሚቀጥለው በዚህ የማያቋርጥ ሰንሰለት ውስጥ ነው፡፡ ከሰንሰለቱ ውጪ የሆነ ሰው ለሳቸው 'ትንሽ' ነው፡፡ ቢጮህ የማይሰማ፣ ቢናገር የማያሳምን ተራ ነው፡፡ ተራነቱና ትንሽነቱ የሚመነጨው ከወይዘሮ ዘርፊሸዋል የ'አይነትና' የ'ዘር' እሳቤ ነው፡፡

"...እሱማ ስለ ጋብቻም ያወራል፡፡ እኔ ፊት አልሰጠሁትም እንጂ..." "እረ ዘሩስ ምንድን ነው?... ማዕረጉስ ምንድን ነው?" (*መባቻ*፣ 201)፡፡ ይህ ከልጃቸው (ዘለቃ) ጋር ያደረጉት ምልልስ ነው፡፡ የወይዘሮ ዘርፊሸዋል ዋንኛ ጥያቄ 'ዘር' ነው፡፡ በሳቸው አእምሮ የሁለቱ መፈቃቀድ ተዘንግቷል፡፡ ከትንሽ ሰው (በመጠን ሳይሆን በዘርና ደረጃ) ሄዳ እንዳታዋርዳቸው ነው ስጋታቸው፡፡ በዘርና ማዕረግ ጥያቄያቸው ውስጥ ዋንኛ ግባቸው የሰውየውን 'ቅርበት'ና መደብ ማረጋገጥ ነው፡፡ ቅርበት ካለው 'እረ የኛው ነው' ሊባል፣ አልያም በሳቸው እሳቤ 'ወፍ ዘራሽነቱ'ን ለማወቅ ነው፡፡ ያለመደባቸው መዋልን አእምሯቸው አይፈቅድም፡፡ የኑሯቸው ግብ ራሳቸውን ከላይኛው መደብ (ከመኳንንቱ፣ መሳፍንቱና ባላባቱ) ጋር አስተካክሎ ማስቀመጥ ነው፡፡ የታችኛው መደብ ለሳቸው ሁሌም አገልጋይና ታዛዥ ብቻ ነው፡፡ እንደታዘዘው ብቻ የሚገኝ፡፡ ስለሆነም የራሳቸውን ወገን መካብ፣ ማድነቅና ማሞካሸት የዘውትር ተግባራቸው ነው፡፡ በዚህም ያላቸውን ማህበራዊ ግዝፈት ለማሳየት ይጥራሉ፡፡

"እረግ አብ ሲነካ ወልድ ይከፋ እንዲሉ ለካ አንተም ከዚያው ነህና! ጥብቅና መቆምህ ነው? ስለኔ ትውልድ ግን ዝግባና ብሳና ለየቅል ተብሏል" (*መባቻ*፣ 140)፡፡ ለወይዘሮ ዘርፊሸዋል

ከራስ ባለፈ በትውልድ ቅብብሎሽ የመጣው የዘር ሀረጋቸው እንደ ገዘፈ ደሪና ዘላቂ ነው፡፡ በመሆኑም በሳቸውና በሌላው መካከል ያለውን 'ልዩነት' ለመግለፅ ዝግባና ብሳናን ያነፃፅራሉ፡፡ በ'ዝግባና' 'ብሳና' ንጽጽር ውስጥ የሚገኘው ትልቁ ቁም ነገር መደብና ጎራን መለየት ነው፡፡ አንድም ዝግባና ብሳና የማንነት ጥያቄ በውስጣቸው ያዘሉ ናቸው፡፡ አንድም ዝግባና ብሳና የግዝፈት ልዩነት አላቸው፡፡ አንድም ዝግባና ብሳና መደብ ናቸው፡፡ አንድም ዝግባና ብሳና ዘር ናቸው፡፡ አንድም ዝግባና ብሳና የጠንካራና ደካማ ምሳሌ ናቸው፡፡ በዚህ ውስጥ ወይዘሮ ዘርፈሸዋል ወገንተኝነት ይስተዋልባቸዋል፡፡

ዝግባ በጥንካሬም ሆነ በአገልግሎት ዘመን ከብሳና የተሻለ ነው፡፡ ዝግባ በግዝፈትም ቢሆን ከብሳና ይሻላል፡፡ ለዝግባና ብሳና ማህበረ ባህሉ ያለው ግምት እኩል አይደለም፡፡ ወይዘሮ ዘርፈሸዋል ዝግባ ናቸው፡፡ የመሳፍንቱ፣ የመኳንንቱ፣ የባላባቱ ነገድ ውስጥ ገብተው እንደ አንድ ሰበዝ የሚቆጠሩ ሰው ናቸው፡፡ ስለዚህ ብሳና መሆንን አይሹም፡፡ ሁሌ ጊዜ *subject* መሆን የሚፈልጉትም ሆነ የሚጥሩት ለላይኛው መደባዊ መዋቅር ነው፡፡ የታችኛው መደብ (የባላገሩና ጭሰኛው) ዘርና የኑሮ ዘይቤ ፈፅሞ አይመለከታቸውም፡፡ የታችኛው መደብ ብሳና ነው፡፡ ልጠንክር ቢል ተሰባሪ፤ ላምፅ ቢል ሚች ነው፡፡ አቅሙና ጥንካሬው በብሳና ባህርይ ተቀምሮ የተሰራ ማህበረሰብ ነው፡፡ ፈፅሞ የታችኛው መደብ አካል ሊሆኑ አይችሉም፡፡ 'ዝግባና ብሳና' እንጨት ቢሆኑም፤ በወይዘሮ ዘርፈሽዋል የሰው ባህሪይ ተሰጥቷቸዋል ('ሰው አይነትና ዘር ዓለው')፡፡

አስተሳሰባቸው በዚህ ውስጥ የተቃኘ ስለሆነ ዝግባና ብሳና የሰው ወኪሎች ናቸው፡፡ 'ዝግባ' ቅርስነቱና ወኪልነቱ ለላይኛው መደብ ነው፡፡ በዝግባና በብሳና መካከል የመደብ ልዩነት አለ፡፡ ልዩነቱ ሚመነጨው ከሳቸው ባህሪና ተግባር ነው፡፡ በመሀከላቸው ያለው የጥንካሬ፣ የአገልግሎትና የግዝፈት ልዩነት መደብ አመልካች ነው፡፡ ዝግባና ብሳና የላይኛው (መኳንንት፣ መሳፍንት ወዘተ.) እና የታችኛው (ባላገሩና ጭሰኛው) መደብ ማደሪያ ናቸው፡፡ በባህሪና በተግባር ይመስሏቸዋል፡፡

> *እስቲ ማን ይሙት የጨዋ የመሳፍንት የመኳንንት ዘር መሆን የሚያስድብ ነው? ኦሆሆ! የእህል ዘርን እንውሰድ ምርጥ የስንዴ ዘር፣ የአጃ ዘር፣ የማኛ ጤፍ ዘር፤ ሙሬ፣ ሙጃ፣ አራሙቻ፣ ስሚዝ፣ እንክርዳድ ካልሆነ ተብሎ ይሰደባል? (ማግስት፣ 59)*

ወይዘሮ ዘርፌሽዋል በዚህ ውስጥ የሚበላውን ከማይበላው፣ ጠቃሚውን ከማይጠቅመው ያዋግናሉ:: ዓላማቸው የራሳቸውን ወገን ከፍ አርጎ ማሳየት ነው:: የተሻለውን በመቅረብ የማይረባው እንደማይመለከታቸው ያሳያሉ:: 'ምርጥ የስንዴ ዘር'፣ 'የአጃ ዘር'፣ 'የማኛ ጤፍ ዘር' በሙሉ የእህል ዘር ናቸው:: ውክልናቸውም ለመኳንንቱና ለመሳፍንቱ ዘር ነው:: አይነታቸውም በውል ከመለየቱ ባሻገር ቢዘሩ በቃይ ናቸው::

ስለዚህ ዘርፌሽዋል ጎራ ለይተው የቆሙ ሰው ናቸው:: ራሳቸውን የመኳንንቱና የመሳፍንቱ subject አድርገዋል:: በእህል ዘር የመወከላቸው ምስጢር አንድም የተፈላጊነት ደረጃቸውን ከፍ ለማድረግ ነው:: አንድም እንደማይከስሙ ለመጠቆም ነው:: አንድም የዘረ ብዙነት ምሳሌ ነው:: መኳንንቱና መሳፍንቱ ዘሩ የተለየና የታወቀ አካል ናቸው:: ከየት መጤነቱ የማያደናግር መደብ ነው:: በሌላው ወገን ደግሞ *subject* የሚያደርጓቸው የ'ሙሬ'፣ የ'ሙጃ'፣የ'አራሙቻ'፣ የ'ስሚዝ'ና የ'እንክርዳድ' ወኪል የሆኑትን የታችኛው መደቦችን ነው:: አንድም ዘራቸው በውል የተለየ አይደለም:: ትርፍ ናቸው:: ተለይተው የሚጣሉ እንክርዳዶች ናቸው:: ትርጉማቸው ሰው ከሚለው ፅንሰ ሃሳብ እጅጉን የራቀ ነው:: ለምግብነት ቢውሉ እንኳ ለእንስሳት ነው:: ለወይዘሮ ዘርፌሽዋል የታችኛው መደብ ቅርበቱ ለእንስሳ ነው:: *subject* መሆን የሚችለውም ከእንስሳው ጋር ነው:: የወይዘሮ ዘርፌሽዋል ጎራና የታችኛው መደብ ጎራ ፅንፍ ለፅንፍ የቆመ ነው:: በመሆኑም የሙሬ፣ የሙጃ፣ የአራሙቻ፣ የስሚዝና የእንክርዳድ ወገን (subject) ሊሆኑ አይችሉም:: "... የመኳንንት ዘር መሆን የሚያሰድብ ነው?" በወይዘሮ ዘርፌሽዋል አመለካከት ለስድብ ቅርብ እንክርዳዱ ነው:: የ "አጃ ዘር"፣ "ምርጥ የስንዴ ዘር"ማ ተለይቶ ይታወቃል:: አራሙቻው ግብስብስ ነው:: መነሻና መድረሻው አይታወቅም::

አንድም በተቀደደለት ቦይ የሚፈስ ጎርፍ የሚያንገላታው፣ ተራ ነው:: አንድም በሳቸው ልኬት የታችኛው መደብ 'ትንሽነት' የተየለሌ ነው:: አንድም ትንሽነቱ ከሚኖርበት ህይወት ይመነጫል:: አንድም በርቀቱ ይለካል:: አንድ ነገር ከላይ ወደ ታች ሲታይ ትንሽ ነው:: በርቀቱ ውስጥ የሚነበበው 'ልዩነት' ነው:: ለወይዘሮ ዘርፌሽዋል ከላይ ወደታች ይታያል እንጂ ከታች ወደ ላይ የሚታይ አይመስላቸውም (ከታች ወደ ላይ ሲታይም አንድ ነገር ትንሽ ነው):: የ'ትንሽነት'ና የ'ትልቅነት' ብያኔው ሚመነጨው በመደብ የተፈረጀው ማህበረሰብ አእምሮው ከተሰራበት ርዕዮተ ዓለም ነው:: የሆነው ሆኖ ስድብ፣ ትችት ወዘተ. እሳቸው የሚመደቡበትን ጎራ የሚመለከት አይመስላቸውም::

ለሳቸው ተሳዳቢው ተገኘውና ታዛዡ ክፍል የታችኛው መደብ ብቻ ነው፡፡ በዚህ የአስተሳሰብ እንቆቅልሽ ውስጥ ነው እስከመጨረሻው የሚያልፉት፡፡

ጎራ ለይቶ መደብን ለማረጋገጥ የሚደረግ እሩጫ በወይዘሮ ዘርፈሽዋል ብቻ የሚስተዋል ሳይሆን፤ የኔ ወገን ናቸው በሚሏቸው ላይም ይታያል፡፡

> *ዘለቄታቸውን ያሳምርላቸው እንጂ ደህና ሙሽሮች ናቸው፡፡ ያንችን ልጅማ አውቃታለሁ፡፡ እየቆነጀች እያማረባት ሔዷል፡፡ ለመሆኑ እንዲያው የዘመኑ ፍቅር ብቻ የቤተሰብም ቁም ነገር አለበት? ልዕልት ሁለቱን ሙሽሮች አሁንም ቃኘዋቸው የማን ሀረግ ነው ወላጆቹን እናውቃቸዋለን? (ዋዜማ፣ 221)፡፡*

በዚህ ውስጥ ትልቁ ቁም ነገር ያለው ሁለት መሰረታዊ ጥያቄዎች ላይ ነው፡፡ የመጀመሪያው "የቤተሰብ ቁም ነገር አለበት?" የሚለው ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ "የማን ሃረግ ነው ወላጆቹን እናውቃቸዋለን?" የሚለው ነው፡፡ በጥያቄዎቹ ውስጥ የመደብና የ*subject* ጣጣ አለ፡፡ ከማይፈለግ ቡድን ጋር እንዳትቀላቀለን የሚል አንድምታ አለው፡፡ የመሳፍንቱ ወገን የመሳፍንት ዘር የሆነውን ብቻ ነው ወደ ራሱ መቀላቀል ሚፈልገው፡፡ ከራስ ተወልደው ወደ ራስ *subject* የሚሆኑት ይተኮርባቸዋል፡፡ ለዚህ ደግሞ "ሃረግ" እና "ቤተሰብ" ወሳኝ ጉዳዮች ናቸው፡፡ አንድም ሃረግ በባህሪው ቅጥልጥል ነው፡፡ አንድም ሃረግ ማሰርያ ነው፡፡ አንድም ሃረግ የመዋቅር አምሳያ ነው፡፡ የመሳፍንቱና የመኳንንቱ ጎጆ ሚቀለሰው በዚህ ውስጥ ነው፡፡ ከ'ወፍ ዘራሹ' የታችኛው መደብ ቢቀላቀሉ ለነሱ ሞት ነው፡፡ ከፍ ካለው መቆራኘት የግድ ነው፡፡ ከዚህ ዝንፍ ያለ እነሱን አይወክልም፡፡ ደረጃውን የመፈለግ ግዴታ ይጫነዋል፡፡ በመፈለግ ውስጥ አለመፈለግ በግልፅ ይታያል፡፡ ከመፈለግ በስተጀርባ ገፅ በገፅ ይነበባል፡፡

'ቤተሰባዊ' እንዲሆንም ይፈለጋል፡፡ ቁም ነገር የታከለበት እንዲያሰኝ ይጠበቃል፡፡ ቤተሰብ ማኅበራዊ ተቋም ነው፡፡ የመሳፍንቱና የመኳንንቱ ህይወት በተቋም ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ *subject* በማድረግ ሰበብ የሚገነባው ተቋም ነው፡፡ ተቋሙ ተጋብቶ ልጅ የመውለድ ጉዳይ ብቻ አይደለም፡፡ የፖለቲካዊ ጉዟቸው ዋስትናም ነው፡፡ በመተሳሰር አቅምን መገንባት ዋንኛ ግባቸው ነው፡፡ አንድም በቤተሰብ ይዛመዳሉ፡፡ አንድም በቤተሰብ ያስተዳድራሉ፡፡ አንድም በቤተሰብ ይሾማሉ፡፡ በጋብቻ ሂደት ውስጥ የ'ቤተሰብ ቁም ነገር' የሚፈለግበት ምክንያት፤ ከዘር ሃረግ ማረጋገጫነት ባለፈ ተቋማዊ ምስጢር አለው፡፡

ተቋሙ የፖለቲካ የበላይነታቸውንም ማስጠበቂያ ነው፡፡ የዘር ሃረግን ሰበብ አድርጎ ወደ ራስ ማቅረቢያ "ቴክኒክ" ነው፡፡ መደብን መሰረት ያላደረገ ጋብቻ ለነሱ ውድቀት ነው፡፡ በጋብቻ ደረጃ የታችኛውን መደብ ፊፅሞ ሊቀርቡት አይከጅሉም፡፡ ተለይቶ እንዲኖር ተፈርዶበታል፡፡ በመካከላቸው ያለው እርቀት ተጠብቆ እንዲዘልቅ ይፈለጋል፡፡ ካለበለዚያማ እንዴት መኳንንት መሳፍንት እየተባሉ መግዘፍ ይኖራል? መሳፍንትና መኳንንት በሚለው ስያሜ ውስጥ ያለው ፅንስ ሃሳብ ትርጉሙ ጥልቅ ነው፡፡

መኳንንት ለገበሬ ልጁን ቢድር የተገነባው ንድፍ-ሃሳባዊ ደረጃ ይናዳል፡፡ ስያሜውም ፍሬ ፈርስኪ ይሆናል፡፡ ስለዚህ በመደብ ልዩነቱ ውስጥ ቤተሰብና የዘር ሃረግን ምክንያት አድርጎ ተፈላጊውን ሰው ወደራስ *subject* ማድረግ የትኩረት ነጥባቸው ነው፡፡ ወይዘሮ ዘርፈሽዋልም የዚሁ ተመሳሳይ ህይወት አንድ አካል ናቸው፡፡ ከኑሮ እኩዮቻቸው ውጪ ማን ሊቀርባቸው ይችላል?

> *ወይዘሮ ዘርፈሽዋልና ማናዬ በምግብ አዳራሽ ውስጥ ተቀምጠው፤ መጀመሪያ ለጥም ማብረጃ አምቦሃ ቀጥሎ ውስኪ ቀርቦላቸው ሲዝናኑ ዘይኔ የምታደርገው ጠፍቷት ከበሩ ጥግ ቆማ ቆየች፡፡ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል እንደ እርሳቸው ድብልብል የሆነውን ሰራተኛ "ወደዚያ ጥግ አስቀምጣት የምትጠጣውም ውሃ ስጣት" ብለው ያዘዙት ውስኪውን ሁለት ጊዜ ተጎንጭተው ጫን ከተነፈሱ በኋላ ነበር፡፡ ...ዝነኛው የጭራ ሜዳ የዶሮ ጥብስ ትልልቅ ጉልቻ መስሎ በሁለት ሳህን ቀረበላቸው፡፡ ተያያዙት፡፡ ምንችፍ፡፡ ቁርጥም፤ ቁርጥምጥም፡፡ ምንችፍ፡፡ ቁርጥም፡፡ ቁርጥምጥም፡፡ ግንጥል-ጋጥ-ጋጥ- ቁርጥም ጉንጭት፡፡ (መባቻ፣ 45)*

'ዘይኔ' ተወልዳ ያደገችበት ማህበረሰብ የታችኛው መደብ በመሆኑ፤ አብሮ ለመቀመጥ እንኳን አልታደለችም፡፡ የቤቱ መሃል፣ ፊት-ለፊትና በግላጭ የሚታዩት የማረፊያ ወንበሮች ተነፍገዋታል፡፡ ለሷ አይገቧትም፡፡ የሚሆናት "ጥጉ" ነው፡፡ ከእይታ ነፃ የሆነ ማረፊያ ይሰጧታል፡፡ ከጅምሩ የዘይኔ ምርጫ "ጥጉ" ነው፡፡ ያለቦታዋ ሂዳ አላረፈችም፡፡ "ከበሩ ጥግ ቆማ ቆየች" እንጂ በፈቃዷ ወደ ውስጥ አልዘለቀችም፡፡ ቦታዋን ታውቀዋለች፡፡ የታችኛው መደብ ፍሬ ናት፡፡ ያለ ቦታዋ እንዴት ልታርፍ ትችላለች? የኖረችበት ማኅበር ያላፀደቀላትን ከየት ታመጣዋለች? ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ቦታ ይወዳሉ፡፡ የእርሻ ቦታ፣ የአክብሮት ቦታ ወዘተ. የእሳቸው ብቻ እንዲሆን ይሻሉ፡፡ ስለዚህ እንደምርጫዋ ሁሉ ለዘይኔ የሚሆናት 'ጥጉ' ነው፡፡ "ጥግ" አንድም ማህበራዊ ደረጃዋ ነው፡፡ አንድም የአዲስ ህይወት መታዘቢያዋ ነው፡፡ አንድም የልዩነት ልኳ ነው፡፡ አንድም መሸሸጊያዋ ነው፡፡ አንድም የታችኛው መደብን መረሳት ማሳያ ነው፡፡ የወይዘሮ ዘርፈሽዋል ማህበራዊ መደብ

ለሷ ሩቅ ነው፡፡ ብትመኘው የማይሰጣት፤ ብትንጠራራ የማትደርስበት፡፡ እጅግ በጣም ከእሷ ማህበራዊ ህይወት ይለያል፡፡ የመደብ ልዩነታቸው በዚህ ብቻ አያበቃም፡፡ ለዘይኔ 'ውሃ' ለወይዘሮ ዘርፈሽዋል ደግሞ 'ውስኪ' መቅረቡ ሌላው የመደብ ልዩነታቸው ማሳያ ነው፡፡ እንደዘይኔ ላለችው የታችኛው መደብ አባል ለሆነች ሴት ውሃ እንጂ ውስኪ አይሆናትም፡፡ በወይዘሮ ዘርፈሽዋል እምነት ለውስኪ የታደለች አይደለችም፡፡ ውስኪው ለመኳንንቱ ለመሳፍንቱና እንደ ማናዬ ላለው የመንግስት ሹም ብቻ የቀረበ የላይኛው መደብ መጠጥ ነው፡፡ ተፈጥሯዊው ውሃ ግን ለዘይኔ ይገባታል፡፡ አንድም ወንዝ ወርዳ ቀድታዋለች፡፡ አንድም የ'እሱ' ስጦታ ነው፡፡ ውስኪ ግን ከኖረችበት ማህበር እጅጉን ይርቃል፡፡

ከወይዘሮ ዘርፈሽዋል ጋር አብሮ ለመመገብና ለመጠጣት የመኳንንቱ፣ የመሳፍንቱና የሹማምንቱ ወገን መሆን ያስፈልጋል፡፡ ማናዬ አብሯቸው ለመመገብ የታደለው የሹማምንቱ *subject* በመሆኑ ነው (የፍቅር ጨዋታው እንዳለ ሆኖ)፡፡ ከዚሁ በተጓዳኝ ዘይኔ በራሷ 'ጥግ'ን መምረጧ የታችኛው መደብ *subject* መሆኗን ማፅናቷ ነው፡፡ ካልኖረችበት ህይወት ይልቅ፤ የነበረችበትን ትመርጣለች፡፡ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ባዘሉት የዶሮ ጥብስ የአመጋገብ ሂደት ውስጥ የምንረዳው ሌላ ጉዳይ የበዝባዥና የተበዝባዥን መስተጋብር ነው፡፡ ይህም የመደብ ልዩነቱ ያመጣው ጣጣ ነው፡፡

"ምንችፍ" ፣ "ቁርጥም"፣ "ቁርጥምጥም"፣ "ግንጥል-ጋጥ-ጋጥ" የሚሉት ቃላት የአመጋገብ ስርዓት ማሳያዎች ብቻ አይደሉም፡፡ ይልቁንም የላይኛውን መደብ በዝባዥነት ጠቋሚዎች ናቸው፡፡ "ዶሮው" ደግሞ በታችኛው መደብ የጭሰኛ ማህበረሰብ ይወከላል፡፡ የሚመነቸፈው፣ የሚጋጠውና የሚቆረጠመው ባላገሩ ነው፡፡ አንድም ባላገሩ እንዲገብር የሚገደደው የስጋና የላቡን ውጤት ነው፡፡ አንድም ባላገሩ መስዋእት ነው፡፡ በተጓዳኝ የመኳንንቱና የመሳፍንቱ ወገን ደግሞ በጭሰኛው ላብ ይወፍራሉ፡፡ በጭሰኛው ምስሶነት ይኖራሉ፡፡ የጭሰኛውን ልጆች ተስፋ ያጨልማሉ፡፡ ጭሰኛው በዘመኑ ሁሉ ለነሱ የ'ዶሮ ጥብስ' ነው፡፡ ለላይኛው መደብ *subject* መሆን የቻሉ ግለሰቦች የሚቋደሱት ማዕድ ነው፡፡ ሊያገለግል እንጂ ሊገለገል ያልታደለው ማህበር ጭሰኛው ነው፡፡

የጭሰኛው ወዝ ውጤት የሱ ሳይሆን በመመንቸፍና በመጋጥ የሚያምኑት የመሳፍንቱ ዘሮች ነው፡፡ በዶሮ ጥብሱና በሚግጠው መሃል የመደብ ልዩነት አለ፡፡ የላይኛው መደብ *subject* መሆን የቻለ በሙሉ ይግጣል፡፡ ይመነችፋል፡፡ የታችኛው መደብ *subject* የሆነው ደግሞ

ይጋጣል። ይመነቸፋል። ዘይኔ የታችኛው መደብ ውስጥ የምትካተት በመሆኗ፣ ለመጋጥ የታደለች አይደለችም። የተበዝባዥ ማህበር ፍሬ በዝባዥ ሊሆን አይቻለውም። እጣ ፈንታዋ ሲግጡ ማየት ነው። ከነሱ ጋር መሳተፍ ካለ ቦታ እንደመገኘት ይቆጠራል። ጭሰኛው ተገዶ ሚገብረው እያየ እያስተዋለ ነው። በልቶ ጠግቦ ወስፋቱን ገሎ አይደለም። እየጎመዠ እየሳሳ ለመሳፍንቱ እህል ይጭናል። በዘይኔና በዶሮ ጥብሱ ውስጥ የጭሰኛው ህይወት፣ በወይዘሮ ዘርፈሽዋል ውስጥ ደግሞ የመሳፍንቱ ተግባር ታይቷል። ወይዘሮ ዘርፈሽዋል በርዕዮተ ዓለሙ አማካኝነት የተጎናፀፉት የላይኛው መደብ አባል መሆንን ብቻ ሳይሆን፣ አካላዊ ግዝፈትንም ጭምር ነው።

> *. . . ወይዘሮ ዘርፈሽዋል ወንበሮቹን በንቀት አይን ቃኙዋቸው እንዱ ደረቅ የእንጨት ወንበር ነው። ሲቀመጡበት ሁለቱ ጭናቸው ከጎን ተርፎ እንደሚንጠለጠል ያውቁታል። ከጎንና ከጎን ድጋፍ ያለው አሮጌ ትንሽ የመንደር ፎቴ ደግሞ ጭናቸውን አያስገባም። ቢያስገባም አጣብቆ ያስጨንቃቸዋል። . . . ወዲያ ወዲህ ተመልክተው ራቅ ብሎ ወደሚገኘው ትልቅ ፎቴ ላይ ዘርፈጥ ሲሉ ዳሌያቸውና ጭናቸው ለሶስት ሰው ከተመደበው ወለል ከግማሽ የሚበልጠውን ሞላው ... (ዋዜማ፣ 18)*

ወይዘሮ ዘርፈሽዋል የላይኛው መደብ አባል ከመሆናቸው ባሻገር በአካልም ግዙፍ ናቸው። "ወንበሮቹን በንቀት አይን ቃኝዋቸው" ንቀቱ ሚመነጨው ልካቸውን ከማጣት ነው። ከመጠናቸው ውጪ በሆነ ወንበር መቀመጥ አይችሉም። የዚህ ሁሉ መንስኤው ግዝፈታቸው ነው። ግዝፈታቸው አካላዊ መገለጫቸው ብቻ አይደለም። ይልቁንም የማህበራዊ መደብ አምሳያቸው ነው። የላይኛው መደብ ግዙፍ ነው። ግዝፈቱ በንድፈ-ሃሳብም በተግባርም ነው።

በተግባር፣ በአቅምና በጉልበት ያሻውን መፈፀም የታደለው የላይኛው መደብ ነው። የታችኛው የተባለውን ተቀባይ ነው። ለወይዘሮ ዘርፈሽዋል የ"እንጨት ወንበር" አይሆናቸውም። "አሮጌ ትንሽ የመንደር ፎቴም" አይመጥናቸውም። ያውም 'ትንሽ' የተባለ ተቀፅላ የወጣለት ወንበር እንደምን ከሳቸው አስተሳሰብና ግዝፈት ጋር አብሮ ይሄዳል? በትንሽ ውስጥ የሚነበበው ሌላ ፅንሰ ሃሳብ ነው (የጭሰኛው ህይወት)። ወይዘሮ ዘረፈሽዋል ደግሞ ይህ ህይወት አይመለከታቸውም። የሳቸው አኗኗር ከትልቅ የተቀዳ ነው።

ከመኳንንትና ከመሳፍንት የተወለደ ትንሽ ነገርንም ሆነ ትንሽ መባልን አይሻም፡፡ ሁል ጊዜ ከትልቅ መጎዳኘትን ይመርጣሉ፡፡ 'ትልቅ'ና የላይኛው መደብ (ወይዘሮ ዘርፌሽዋል) ገፅ በገፅ ይናበባሉ፡፡ ቀደም ሲል ያደጉበትና የተሰሩበት ርዕዮተ ዓለም ያስተማራቸው ትልቅነትን ነው፡፡ 'ትንሽ' ለአእምሯቸውም ሆነ ለልቦናቸው ሩቅ ነው፡፡ ትንሽ አንድም ለአይን አይሞላም፡፡ ትንሽ አንድም የባላገሩ ገላጭ ነው፡፡ ትንሽ አንድም አያስፈራም፡፡ በወይዘሮ ዘርፌሽዋል ህይወት ውስጥ 'ትንሽ' ትርጉምና ብያኔ የለውም፡፡ ጎራቸው ከትልቆቹ (ከመሳፍንቱና ከመኳንንቱ) በመሆኑ፤ ትርጉም ያለው "ትልቅ" በሚለው ቃል ውስጥ የተሰገሰገው ማንነታቸው ነው፡፡ ስለሆነም የሚመጥናቸው "ትልቅ ፎቴ" ነው፡፡ "ፎቴው" የገዢው መደብ ወካይ ነው፡፡ የገዢው መደብ አካል መሆናቸው በ"ትልቅ ፎቴ" ምርጫቸው ውስጥ ይታያል፡፡

ወይዘሮ ዘርፌሽዋል ከትልቁ ፎቴ ላይ ቢቀመጡም "ዳሌያቸውና ጭናቸው ለሶስት ሰው ከተመደበው ወለል ከግማሽ የሚበልጠውን ሞላው" ይላል፡፡ ወይዘሮ ዘርፌሽዋል ሰው ሚማርኩት በጠመንጃና በዱላ አይደለም ( በተለይ ለላይኛው መደብና ለስልጣን ቅርበት ያላቸው ሰዎች ሆነው ሲገኙ)፤ ይልቁንም በጭንና ዳሌያቸው ነው፡፡ የጭንና ዳሌያቸው ግዝፈት የማህበራዊ ደረጃቸው ወኪል ነው፡፡ አንድም ጭንና ዳሌ ስጋ ነው፡፡ አንድም ስጋ የሚያሳስበው የላይኛውን መደብ ነው (የዶሮ ጥብሱን ይመለከቷል)፡፡ ስለዚህ ወይዘሮ ዘርፌሽዋል የላይኛው መደብ አንድ አካል መሆናቸው የሚገለፀው በአመለካከታቸው ብቻ ሳይሆን በግዝፈታቸው ጭምር ነው፡፡

በወይዘሮ ዘርፌሽዋል ህይወት ውስጥ የላይኛው መደብ አመለካከትና ፍልስፍና በግልፅ ይታያል፡፡ ወይዘሮ ዘርፌሽዋል በተለያየ መንገድ የላይኛው መደብ ወገን መሆናቸውን እንደገለፁ ሁሉ፤ ባላገሩም የታችኛው መደብ *subject* መሆኑን ያፀናል፡፡

"ማ-ይሙት ደሃ ገበሬ በሁለት ሶስት ቀን ዕድሜ ሹመት ያገኛል? የጓሮ እሸት መሸምጠጥ ሆነ እንዴ! ኧረ ዕድቄ ቀርቶ በውል በኮነነኝ! ገበሬን ካፈር እንጂ ከሹመት ካባ ምን አገባው!" (*ዎዜማ*፡ 182)፡፡ በዚህ ሃሳብ ውስጥ ባላገሩ ጎራ ለይቶ ሲቆም ይስተዋላል፡፡ ገበሬ ዝምድናው "ካፈር" ጋር ነው፡፡ አንድም በአፈር አማካይነት ይመገባል፡፡ አንድም በአፈር ጥገኝነት ይኖራል፡፡ አንድም አፈር ዝቅ ብለው ያዩታል እንጂ ቀና ብለው አይመለከቱትም፡፡ ገበሬው ምድሪቱን ቆፍሮ በዘራው እህል ያገኘውን አዝመራ አጭዶ ከመኖር ባለፈ ሌላ ህይወት የለውም፡፡ ስለዚህ ባላገሩ ራሱን የሚያጎዳኘው "ከአፈር" ጋር

ነው፡፡ በዚህ ውስጥ ተነጥሎ የቆመበትን ስፍራ መለየት ይቻላል፡፡ ባላገሩ ማንነቱን ካፈር ለይቶ ሊመለከተው አይችልም፡፡ እንዴት ያልኖረበትን ህይወት ሊመኘው ይችላል? በመሆኑም በአፈሩ ውስጥ ባላገሩ፣ በባላገሩ ውስጥ ደግሞ የታችኛው መደብ ህይወት በግልፅ ይነበባል፡፡

ራሱን *subject* ሚያደርገው ከአፈር ጋር ነው፡፡ ማንነቱ ከአፈር ጋር ተገምዶ የኖረ ነው፡፡ አፈር የባላገሩ ሙያ (እርሻ) ወኪል ነው፡፡ "አፈር (እርሻ)"ና የ"ሹመት ካባ" ፅንፍ ለፅንፍ የቆሙ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ማንነታቸውም ለየቅል ነው፡፡ "ሹመትና ካባ" የመሳፍንትና የመኳንንት ህይወት ምሳሌ ነው፡፡ የመሸም መሻር ጣጣ የላይኛው መደብ ማህበረሰብ ጉዳይ ነው፡፡ በሃሳብም ሆነ በተግባር ይመለከታቸዋል፡፡ ለባላገሩ ግን ባዕድ ነው፡፡ ምክንያቱም አንዳቸው በአንዳቸው ውስጥ ተዛምዶ መኖርን አለመዱም፡፡ የባላገሩንና የመሳፍንቱን አእምሮ የሰራው ርዕዮተ ዓለም፣ በተመሳሳይ መንገድ አስበው በተመሳሳይ መንገድ እንዲኖሩ የሚያስችል አይደለም፡፡

በገበሬውና በመኳንንቱ ልቡና ውስጥ ሁለት የተለያየ ዓለም አለ፡፡ ይኸውም ባላገሩን እንደ ባላገርነቱ (ገባሪና አፈር ገፊ) ብቻ ማሰብ እንዲችል የሚያደርግ፣ መኳንንቱንም እንደ መኳንንትነቱ (አስገባሪና ሹም) እንዲኖር ማድረግ የሚያስችል ነው፡፡ አንዳቸው ያንዳቸውን ተግባር ልፈፅም እንኳን ቢሉ አይቻላቸውም፡፡ ባላገሩን ከ'ሹመት' መኳንንቱን 'ካፈር' ማቆራኘት የኖሩበትን ርዕዮተ ዓለምና ልማድ እንደማፍረስ ይቆጠራል፡፡ ስለሆነም ባላገሩ ለአፈር *subject* ሲሆን መኳንንትና መሳፍንቱ ደግሞ ለሹመት *subject* ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ በ'አፈር' እንዲሁም በ'ሹመትና ካባ' ውስጥ በስተጀርባ የሚገኙትን ማህበረሰቦች ማየት ይቻላል፡፡ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚስተዋለው ፍሬ ነገርም የማንነት ልዩነት ነው፡፡ በአፈሩ ውስጥ የታችኛው መደብ (የባላገሩ) ማንነት፣ በተጓዳኝ ደግሞ በ"ሹመትና ካባ" ውስጥ የላይኛው መደብ (የመሳፍንቱና የመኳንንቱ) ማንነት ይፀናል፡፡ የባላገሩ ማንነትና ከመሬት (ከአፈር) ጋር ያለው ጥብቅ ዝምድና ዘመንና ትውልድ ተሻጋሪ ነው፡፡ ስለሆነም በመሬትና በባላገሩ ቁርኝት ውስጥ ዘር ረቂቅ ትርጉም ዓለው፡፡

*ይህ የአባቶቻችን፣ የአያቶቻችን የስንት ዘር አገራችን ነው፡፡ ከእትብታችን የተሳሰረ ነው፡፡ አባቴ ለኔ አስረከበኝ፡፡ እኔ ለእናንተ፣ እናንተ ደግሞ ለልጆቻችሁ ማስተላለፍ አለባችሁ፡፡ ካለበለዚያማ እትብት ዘር የሌለን ፍልሶች ሆነን እንቀራለን፡፡ እኔ እናንተን ከተካሁ ሀረጉ ተያይዟል፡፡ ዛሬ ዛሬ እየደከመ እኛም በጉልተኛው እየተዳከምን ሄድን እንጂ መልካም መሬት ነው ኣባቶቻችሁ ያቆዩዋችሁ፡፡ የሰጡትን የሚያፈራ… (ዋዜማ፣ 10)*

በባላገሩ ህይወት ውስጥ የትውልድ ቅብብሎሹ የትኩረት ነጥብ "መሬት" ነው፡፡ አንድም መሬት የማንነታቸው ምስጢር ነው፡፡ አንድም መሬት ማረፊያ ነው፡፡ አንድም መሬት የትውልድ ማደሪያ ነው፡፡ አንድም መሬት ዘር አብቃይ ነው፡፡ የመሬት ህልውና በእህል ዘር ብቻ የሚቋጭ አይደለም፡፡ ይልቁንም የሰውን ልጅ ሽግግር ማሳያ ነው፡፡ ባላገሩ በመሬት ኑሮ፣ በመሬት ለምቶ በመሬት የሚያልፍ ማህበረሰብ ነው፡፡ የባላገሩ የትውልድ ዘር (ሐረግ) ከመሬቱ ውጭ ህልውና የለውም፡፡

ገበሬው ከመሬት ጋር የተጎዳኘ ፀናን ሃሳብ ዓለው፡፡ ለባላገሩ መሬት "እትብት" ተቀብሮ "እትብት" የሚተካበት ራሱን የቻለ የህይወት-ዑደት ነው፡፡ በመሬቱ ውስጥ ባላገሩ በባላገሩ ውስጥ መሬቱ ሚዛናዊና ትይዩ ናቸው፡፡ ባላገሩ የመሬቱ ማደሪያ ነው፡፡ መሬቱም የባላገሩ መለያ ነው፡፡ "እትብት"ና "ዘር" በባላገሩ ዘንድ ያለመሬት ፍሬ ፈርስኪ ናቸው፡፡ ዘር አንድም የእህል ነው፡፡ ዘር አንድም የሰው ነው፡፡ ዘር አንድም ሽግግር ነው፡፡ መሬቱ የእህል ዘር የማብቀል ብቻ ሳይሆን ትውልድ የማስቀጠልም ሚና ዓለው፡፡ የባላገሩን ህይወት ከዚህ ውጪ ማሰብ አይቻልም፡፡ ኑሮው ሁሉ ከሚያርሰው መሬት ውጪ ባዶ ነው፡፡ መሬቱን አርሶ፣ መሬት የሰጠችውን በልቶ፣ መሬት ተኝቶ የህይወት ዘመኑን ሁሉ ከመሬት ተጋብቶ የሚኖረው ባላገሩ ነው፡፡

ማንነቱ ፈፅሞ ከመሬት ውጪ አይደለም፡፡ መሬት መገኛ ስፍራው ከእግር በታች ነው፡፡ መሬት መራመጃና መረገጫ ነው፡፡ መሬት ይታረሳል፡፡ መሬት የብዙ አንጡረ ሃብት መገኛ ነው፡፡ ተጨባጭ የሆነው ይህ የመሬት በህሪና የባላገሩ ህይወት ተመሳሳይ ነው፡፡ መሬት የባላገሩን ኑሮ በቀጥታ ይገልፀዋል፡፡ አንድም ባላገሩ የታችኛው መደብ አካል ነው፡፡ አንድም ባላገሩ በመሳፍንቱና በመኳንንቱ ይጨቆናል፤ ይረገጣል፡፡ አንድም ባላገሩ የመሳፍንቱ መሰረት ነው፡፡ በመሆኑም ባላገሩና መሬቱ ረቂቅ በሆነ መንገድ በባህሪ ደረጃ ይወራረሳሉ፡፡ የባላገሩ ጎራና ጉድኝት ከመሬት ጋር ነው፡፡ ከመሬት ውጪ አስቦ ከመሬት ውጪ የሚተገብረው አንዳችም ልምድ የለውም፡፡ባላገሩ የዘር ሃረግ ቅብብሎሹን

የሚገልፀው በመሬት ማንፀሪያነት ነው፡፡ “መልካም መሬት ነው አባቶቻችሁ ያቆዩዋችሁ” በማለት፡፡ ባላገሩ በትውልድ ሒደት ውስጥ ለልጅ ልጅ የሚያቀብለው “መሬት”ን ነው፡፡ ከመሬት ውጭ ለልጅ ለጆቹ የሚያሳድረው እርስት የለውም፡፡ ለታችኛው መደብ (ለባላገሩ) መሬት በፅንስ ሃሳብም ሆነ በገቢር ይወክላቸዋል፡፡ መሬት የፍልስፍናቸው መሰረት ነው፡፡ ህይወታቸውን በመሬት ይመስላሉ፤ ህይወታቸውን በመሬት ይተረጉማሉ፡፡

የላይኛው መደብ እርሶ መገበር የባላገሩ ብቸኛ መክሊት አድረጎ እንደሚያስበው ሁሉ፤ መሬትና እርሻ የባላገሩ ብቻ እንደሆነ አድርጎ የሚያስበው ራሱ ባላገሩም ጭምር ነው፡፡ ባላገሩ መሬት ማረስን የራሳቸው እንደሆነ አድርገው በማሰብ፤ ከዚህ የማንነታቸው መገለጫ ውስጥ የላይኛው መደባዊ መዋቅር አባላት ሊሳተፉ እንደማይችሉ ያፀናሉ፡፡

“አሁን ማ-ይሙት የራስ ወሌ ቅምጥሎች ናቸው በሬ ጠምደው እርፍ ጨብጠው አፈር የሚገምሱት!? የት ሆኖላቸው፡፡ የት አውቀውበት” *(ዋዜማ፣* 198)፡፡ የባላገሩ ድርሻ የሆነው መሬትን ገምሶ የማደሩ ተግባር የላይኛውን መደብ አይመለከተውም፡፡ ይህ ህይወት የሚገልፀው ባላገሩን ነው፡፡ ስለዚህ የላይኛውን መደብ አባላት ከዚህ ተግባር ያርቁታል፡፡ አንድም የማንነታቸውን “ሌላነት” ይገልፁበታል፡፡ አንድም እንደ ባለሙያ ይኩራሩበታል፡፡ ለባላገሩ የላይኛው መደብ እርሶ ለማደር አይችልም (ባይሆን ያረሱትን ይነጥቃል እንጂ)፡፡ ለመሬቱና ለርሻው *subject* ሚሆነው ባላገሩ ነው፡፡ የላይኛው መደብ ጎራ እጅጉን ከነሱ ይርቃል፡፡ “የት አውቀውበት” የሚለው ሃሳብ የመኳንንቱና የመሳፍንቱን ህይወት “ሌላነት” ማሳያ ነው፡፡ “እርፍ መጨበጥ” የገበሬው ማንነት ነው፡፡ ባላገሩ የራሱን መገለጫ ባህሪ ለላይኛዎቹ፤ የላይኛውንም መደብ ባህሪ ለራሱ ማድረግን አይመኘውም፤ አያገኘውም፡፡ እየኖረበት ያለው ርዕዮተ ዓለም ያስተማረውና ያሳመነው እርሶ መገበርን ነው፡፡ በመሆኑም በራሱ የስራ ባህሪ ውስጥ የሌሎቹን ጎራ “የት ሆኖላቸው” እያለ ይጠቁማል፡፡ ባላቸው ማንነት መሳፍንቱና ባላገሩ ማዶ ለማዶ የሚተያዩ ሰዎች ናቸው፡፡ ህይወታቸውና የሚኖሩበት መንገድ ለየቅል ነው፡፡ የአንዱ ባህሪ የሌላኛውን መደብ ባህሪ በቅርበት አይገልፀውም፡፡

በወይዘሮ ዘርፈሽዋል ህይወት ውስጥ የመሳፍንቱን ጎራ ማንነት እንደተረዳነው ሁሉ፤ ባላገሩም የራሱ ማንነት እንዳለው መገንዘብ ይቻላል፡፡ ባላገሩም ሆነ መሳፍንቱ የራሳቸውን ማንነት የሚያፀኑበትና ሀሳባቸውን በራሳቸው ጎራ ውስጥ የሚከቱበት መንገድ ዓላቸው፡፡ ይህ መንገድ በዘፈቀደ የተከሰተ ሳይሆን ከሚኖሩበት ህይወት የተቀዳ ነው፡፡

ህይወታቸውን የሰራው ደግሞ እየኖሩበት ያለው ርዕዮተ ዓለም ነው፡፡ ባላገሩም ሆነ ባላባቱ በራሳቸው ማንነት ውስጥ ሌሎቹን ይገልፃሉ፡፡ ገበሬው እንደ ገበሬ በማሰብ መሳፍንቱን ከራሱ ህይወት ውጪ ይመለከታል፡፡ በዚህ ሂደት ሁለቱም ጎራዎች በሚኖሩበት ህይወት ውስጥ ላለ ጉዳይ ብቻ ራሳቸውን *subject* ያደርጋሉ፡፡

የማህበረሰቡ የ*subject* ጣጣ በዘርና ሙያ ላይ ይመሰረታል፡፡ የወይዘሮ ዘርፈሽዋል የዘር እሳቤ የመሳፍንቱ አስተሳሰብ አምሳያ ነው፡፡ ባላገሩ ለመሬት ያለው ፍቅር (ለማሳረስ ሳይሆን አርሶ ለመኖር) በራስ ጎራ ውስጥ ሚተረጎም ነው፡፡ ምክንያቱም መሬት ለገበሬው የጉሮሮው መድሐኒት እንዲሁም የ'እትብት' (ዘር) ምሳሌው ነው፡፡ ሁለቱም በሚኖሩበት አቅጣጫ አንዳቸውን ካንዳቸው በመለየት የ'ራስ ወገን' መስራቾች ናቸው፡፡ በራስ ወገን የማጎልበት ሂደት ውስጥ አግዝፈው የሚመለከቱት "ማንነት"ን ነው፡፡ ይህ ማንነት አንዱን ካንዱ ለማንፀር ያገለግላል፡፡ ማንነትን የማጎልበት ሂደትን በግለሰብ ደረጃም ማየት ይቻላል፡፡

3.2.2. የ"ካሳሁን" አዲስ ማንነት ፍለጋ

ማንነትን በመገንባትና በማጎልበት አዲስ እውነታን ተገንዝቦ በርዕዮተ ዓለም አማካኝነት ወደ ሌላ አዲስ ማንነት መሻገር ይቻላል፡፡ ቀደም ሲል በኖረበት ህይወት ውስጥ ያልተመለከታቸውን ጉዳዮች በሂደት መረዳት ሲጀምር ለተረዳው ጉዳይ *subject* መሆን በግለሰቦች ውስጥ የተለመደ ባህሪ ነው፡፡ በድርሰቶቹ ውስጥ የምናስተውለው "ካሳሁን" የተባለው ገፀ-ባህርይ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ሊሆን ይችላል፡፡ ካሳሁን ወደ አዲስ አበባ ከመጣ በኋላ ካገኛቸው ተማሪዎች ጋር የሚለዋወጣቸው ሃሳቦች ለሌላ አዲስ ማንነት ሲያበቁት እናያለን፡፡ ይህ ማንነት በሂደት ከተማሪዎቹ በቀሰማቸው ሃሳቦች የሚገነባ ነው፡፡ ካሳሁን አዲስ ማንነቱን የሚገነባውና ለተረዳው ጉዳይ *subject* መሆን የሚጀምረው ደጋግሞ በመጠየቅና በመረዳት ነው፡፡

"'ምን አደረጉ?' ሰላማዊ ሰልፍ ማለት እናንተ በአንድነት ተሰብስባችሁ ለአቤቱታ እንደምታቀርቡት ሁሉ፤ በአንድነት ሆኖ የአቤቱታ ድምፅ ማሰማት ማለት ነው" *(ዋዜማ፣* 190)፡፡ ካሳሁን ከዚህ በፊት በነበረበት ህይወት ውስጥ ሰምቶት የማያውቀውን ቃል ጠይቆ ይረዳል፡፡ በ"ሠላማዊ ሰልፍ" ሃሳብ ውስጥ የሚረዳው ቁም ነገር፤ ወደ ፊት ለሚረዳው ርዕዮተ ዓለም መነሻ ስፍራ ነው፡፡ አንድም የአእምሮውን በር ማንኳኳት የጀመረ ሃሳብ

ነው፡፡ አንድም የወደፊቱን ርዕይ ገልጦለታል፡፡ አንድም በቀጣይ ህይወቱ ውስጥ ጠይቆ የመረዳት መንፈሱን አጠንክሮለታል፡፡ በርግጥ መሰብሰብ የሚለውን ቃል ቀደም ሲል ያውቀዋል (ገሮማ ላይ የተደረገውን ትዕይንት [ዋዜማ፣ 179] ይመለከቷል)፡፡ ነገር ግን ይሄኛው የ"ሰላማዊ ሰልፍ" ዕውቀቱ በመሰብሰብ ውስጥ ሌላ ፋይዳ እንዳለ ያስገነዘበው ነጥብ ነው፡፡

ከዚህ ቀደም ያደረጋቸው ስብሰባዎች የማህበረሰቡ ፍላጎት ድምር ውጤት አይደለም፡፡ "ና ውጣ!" በሚል ግዳጅ የተፈፀመ ነው፡፡ በህብረት ባንድ ድምፅ "ሆ ብሎ" አቤቱታ ማሰማት በካሳሁን ቀደምት ህይወት ውስጥ የተለመደ አይደለም፡፡ የተረዳው የሰላማዊው ሰልፍ እሳቤ የህይወቱ አዲስ ርዕይ መክፈቻ ነው፡፡ ካሳሁን ነገሮችን ለመረዳት ያለው ፍላጎት በዚህ አያበቃም፡፡ ይቀጥላል፡፡

"መሬት ላራሹ አላችሁ? እሷ ጥሩ ነገር ትመስላለች፡፡ እስቲ አብራሯት' ይላል . . . ሌላው ሳይወጣ ሳይወርድ ከእልፍኝ አዳራሹ ተቀምጦ እህል የሚያስጭንበት የጭሰኛ ስርዓት ይቅር ማለት ነው ሲሉ ያስረዱታል" (ዋዜማ፣ 198)፡፡ በዚህ ውስጥ ካሳሁን ያደገበትን መደብ ትልቅ ጥያቄ ይረዳል፡፡ "በመሬት ላራሹ" ውስጥ የሱንም ሆነ የባላገሩን ሕይወት ያነባል፡፡ አንድም ማንነቱ ለመሬት ቅርብ ነው፡፡ አንድም እሱ ተወልዶ ባደገበት ማህበር ህይወት በመሬት ይተረጎማል፡፡ አንድም ዘር ያስቀጥላል፡፡ አንድም መሬት እንደ ወግ ማዕረግ መብቂያ ነው፡፡ በእድሜ ለማረስ የደረሰ ልጅ፤ በዘመኑ አንዳች ሽግግር እንዳደረገ ይቆጠራል፡፡

ለዚህ ነው ካሳሁን ልቡናውና አእምሮው ተቀናጅተው ለእዝኑ ያደረሱትን ሃሳብ ከህይወቱ አስታርቆ 'መሬት ላራሹ አላችሁ?' ሲል የሚጠይቀው፡፡ ጥያቄው ተራ የመረዳት ስሜት የወለደው አይደለም፡፡ ከልብ በመነጨ ስሜት የቀረበ ነው፡፡ ውይይታቸው የቀደመውን ህይወቱን ቢጭርበት፣ ያለፈበትን መንገድ ቢያስታውሰው፣ ያደገበትን መደብ ቢጠቁመው ወዘተ. የሰነዘረው ጥያቄ ነው፡፡ በዚህ ጥያቄ ውስጥ ያደገበት ማህበር ምስል ገፅ በገፅ ይታያል፡፡ ምክንያቱም ጥያቄው ማዕከል ያደረገው መሬትን ነው፡፡ አዳሩ መሬት ምግቡ ከመሬት ለሆነው እንደ ካሳሁን ላለ የገበሬ ልጅ ከዚህ በላይ ጆሮ ሊያነቃ የሚችል ሃሳብ ሊያገኝ አይችልም፡፡ "እሷ ጥሩ ነገር ትመስላለች" ማለቱ የዚህ አመለካከቱ ማሳያ ነው፡፡ በነዚህ ጥያቄዎች ውስጥ ካሳሁን ቀስ በቀስ አዲስ ማንነት ወደሚያጎናፅፈው ሌላ ሃሳብ ይሸጋገራል፡፡

“. . . መንግስት በሲዳሞ፣ በባሌ፣ በጎጃም የጨፈጨፋቸውን ገበሬዎች ታሪክ ሲነግሩት የዓመፅ አስፈላጊነት በአእምሮው ውስጥ ቅርፅ እየያዘ ሄደ” (*ዋዜማ*፣ 202)፡፡ የርዕዮተ ዓለም ዋንኛ ግብ የሰውን ልጅ አእምሮ መገንባት [ቅርፅ ማስያዝ] ነው (እዚህ ጋር ለካሳሁን መረጃ የሚያቃብሉት ከግንዛቤ ተቋማት የተገኙ ተማሪዎች መሆናቸው እንዳይዘነጋ)፡፡ በዚህ አውድ ቅርፅ ብዙ ትርጓሜ ዓለው፡፡ አንድም ቀደም ሲል ስለ “መሬት ላራሹ” እና ስለ “ሰላማዊ ሰልፍ” ያስረዱት ሃሳብ ቅርፅ የመያዙ ሚስጢር ነው፡፡

አንድም “ቅርፅ” የርዕዮተ ዓለሙ መታገጊያ ክፍል ነው፡፡ አንድም “ቅርፅ” የማንነት ለውጡ ማህደር ነው፡፡ አንድም የጥንት ህይወቱን ክዶ ሌላ የመመኘቱ ወኪል ነው፡፡ “ቅርፅ መያዝ” በአዲስ ማንነት ውስጥ መግባት ነው፡፡ አንድም አመፅ የቀድሞውን ስርዓት ለመሻር መነሳት ነው፡፡ አንድም አመፅ የአዲሱ ርዕዮተ ዓለም ጅምር ነው፡፡ አንድም አመፅ በነበረው ህይወት አለመርካት ነው፡፡ አንድም አመፅ የአዲስ ህይወት ጥያቄ ነው፡፡ ካሳሁን ቀደም ሲል በሰበሰባቸው አዳዲስ አመለካከቶች የነበረውን ለማፍረስ ይተባበራል፡፡ ይህ ስሜቱ ባንድ ጀንበር የመጣ አይደለም፡፡ በሂደት በአእምሮና ልቡናው ውስጥ የዳበረ ነው፡፡ ከዛም ካሳሁን በሂደት እውቀት ስለማካበቱና የአዲስ ርእይ ባለቤት ስለመሆኑ በራሱ እንደበት ሲናገር ይስተዋላል፡፡

“. . . እኔ ስንኳ በዚህ በአጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ አወቅሁ፡፡ ወዳጅንም ጠላቴንም፡፡ እናንተም እንደምትሉት ውጤትንም-ምህኛትንም” (*መባቻ*፣ 183)፡፡ በአመለካከቱና በህይወቱ ውስጥ ለውጥ ስለ ማምጣቱ ይናገራል፡፡ ይህ ለውጥ አካላዊ አይደለም፡፡ ይልቁንም አመክንዮን የተላበሰ አእምሯዊ ለውጥ ነው፡፡ ካሳሁን ለውጡን ያዳበረው በጊዜ ሂደት ነው፡፡ ይበልጥ ያካበተውም “ውጤትንም-ምህኛትን”ም ነው፡፡ አንድም ነገሮችን ከየአቅጣጫው አጢኖ የመረዳትን መንገድ ማለቱ ነው፡፡ አንድም የከዚህ ቀደሙን ህይወት መቀየሩ ነው፡፡ ይህን በመረዳት ሂደት ውስጥ የሚያዳብረው በአዲስ መልክ የሚገነባውን ማንነት ነው፡፡ የድሮ ባህሪና ማንነቱን ሽሮ የተለየ ማንነት ይቀዳጃል፡፡ ይህ ስኬት በሽመታቸው ልዩ ልዩ አስተሳሰቦች የተፀነሰ ነው፡፡ የድሮውን ማንነት አዲስ ባገኘው አመለካከት ይገነባል፡፡ *Subject*ቱም አሁን ላካበተው አስተሳሰብ ነው፡፡ ምክንያቱም ከዚህ በኋላ አስተሳሰቡ የማንነቱ መገለጫ መሆን ይጀምራል፡፡ ካሳሁን አእምሮው በአዲስ ርዕዮተ ዓለም ከተገነባ በኋላ የቀድሞ ማንነቱን ወዳወረሰው ቀዬ ይጓዛል፡፡ ጉዞው የነበረውን ሊያፀና አይደለም፡፡ ይልቁንም ያመነበትንና የተቀላቀለውን ርዕዮተ ዓለም ሊገነባ ነው፡፡ ይህ

ርዕዮተዓለም «ሶሻሊዝም» ነው፡፡ ሶሻሊዝምና የካሳሁን ባዲስ ማንነት መወለድ ተቀራራቢ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ሶሻሊዝም ካሳሁን ባካበተው አስተሳሰብ ይገለፃል፡፡ ስለዚህ በህይወቱ ውስጥ የሚነበብ ሽግግር አለ፡፡

"ካሳሁን የቆሬ ገበሬ ቀበሌ ማህበር ሊቀመንበር በመሆኑ፤ ተስፋ የቆረጠውን ማፅናናት መበርገግ የቃጣውን ማረጋጋት ነበረበት" (ማግሰት፣75)፡፡ በዚህ ሃሳብ ውስጥ የካሳሁን ማህበራዊ ደረጃ ከፍ ሲል እናያለን፡፡ ይህ ከፊታ በደመነፍስ ያገኘው አይደለም፡፡ በህይወቱ ውስጥ ከተጋባው ርዕዮተ ዓለም የተገኘ ነው፡፡ "ሊቀመንበርነቱ" ብቻውን የብዙ ነገሮች መገለጫ ነው፡፡ አንድም ለተተከለው ርዕዮተ ዓለም *subject* ነው፡፡ አንድም የአዲስ ማንነቱ ማሳያ ነው፡፡ አንድም የህይወቱ "ውላጤ" ማደርያ ነው፡፡ በዚህ የሹመት አጋጣሚ ውስጥም ያካበተው እውነታና አመለካከት ይገለጣል፡፡ ወገንተኛነቱ፣ ጎራ መለየቱ፣ የተተከለው ይፅደቅ ወዘተ. ማለቱ ይረጋገጣል፡፡ ከተሰባኪ ግለሰብነት ወደ ሰባኪነት ተሸጋግሮ እናገኘዋለን፡፡

"ውሸት ነው! አድሃሪያን የሚባሉት የሚያሰወሩት ወሬ ብቻ ነው! አለ ካሳሁን ፍርጥም ብሎ" (ማግሰት፣77)፡፡ በዚህ ውስጥ ካሳሁን እንደበቱ የሶሻሊዝም ንድፍ ነው፡፡ አንድም "አድሃርያን" የርዕዮተ ዓለሙ ተከታይ ማህበር ቃል ነው፡፡ አንድም የተቃራኒውን *subject* የሚዘልፍ ነው፡፡ አንድም የወገንተኛነቱ ማሳያ ነው፡፡ በልሳኑ ውስጥ አእምሮው ይነበባል፡፡ የራሱን ጎራ ይክባል፡፡ የሌላውን ማንነት ይንዳል፡፡ አንድም የርዕዮተ ዓለማዊ ተቃርኖ እሳቤ ገብቶታል፡፡ አንድም የጥንቱ (የፊውዳሉ) ርዕዮተ-ዓለም ከናካቴው እንዲጠፋ ይፈልጋል፡፡ ስለዚህ የሌሎችን ተቃራኒ ሰዎች ሃሳብ ይሸራል (ውጤትንም-ምሕኛትንም መለየቱ አይዘነጋም)፡፡ ለካሳሁን መንስኤን ማጥፋት ከስሩ እንደሆነ ግልፅ ነው፡፡ በኔው ርእይ ካሳሁን ከተተከለውም ርዕዮተ ዓለም ባሻገር የተጓዘ ይመስለኛል፡፡

". . . አሁን ተጨማሪ አስተያየት ከሌለ በደንባችን መሰረት ይፍረስ ወይም አይፍረስ የሚለውን በድምፅ ብልጫ እንወስናለን" (ማግሰት፣87)፡፡ ካሳሁን በዚህ ውስጥ "የዲሞክራሲ እሳቤን" ሲያራምድ ይታያል፡፡ አንድም "በድምፅ ብልጫ" ማመኑ፡፡ አንድም የውይይት መንፈሱ መጎልበቱ፡፡ አንድም የመናገር ሃሳብ አለመንፈጉ የአስተሳሰቡን ከፍታ ያሳያል፡፡ ካሳሁን በርዕዮተ ዓለም ውስጥ ያሳለፈው ጊዜ ራሱን የቻለ የህይወት ሁደት ዓለው፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ ብዙ ነገሮቹን ሲያዳብር ይስተዋላል፡፡ የህይወት ፍልስፍናውም ጠይቆ

መረዳት ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም ነገሮችን ለማወቅ ያለው ጉጉት ከፍተኛ ነው፡፡ በዚህ ፍላጉቱ ውስጥም አዲስ ማንነቱን ያጠናክራል፡፡

አንድም ባጎለበተው ህይወት ውስጥ ገብቶ ይንቦራጨቃል፡፡ አንድም የርዕየተ ዓለሙ ባለቤት የሆነ ያህል ይሰማዋል፡፡ ካሳሁን ማንነቱ አሁን የድሮው አይደለም፡፡ ጠይቆ ተምሮበት፤ አንዳንዴም ግራ ተጋብቶበት አንቅሮ ተፍቶታል፤ ወደጥንቱ አይመለስም (እሱ ብቻ ሳይሆን የሚኖረበትም ማህበራዊ መደብ)፡፡ አሁን ያለፈውን ህይወት በዘመን መነፅር ብቻ ነው ሚያስተውለው፡፡ በነበር ዓለም ውስጥ የኖረበትን መንገድ ማስታወስ አይፈልግም፡፡ የድሮው ካሳሁን የአሁኑን አይወክለውም፡፡ በአስተሳሰብም በተግባርም ተለውጧል፡፡ በ*ማዕበል የአብዮት ዋዜማ*፣ በ*ማዕበል የአብዮት መባቻ* እና በ*ማዕበል የአብዮት ማግስት* ውስጥ "የድምፅ ብልጫ እሳቤ" ከአንደበቱ የሚወጣው ከካሳሁን ነው (ከታችኛው መደብ ፍሬ)፡፡ ይህ የለውጡ ጥልቀት አንድ ነፀብራቅ ሊሆን ይችላል፡፡

በርዕዮተ ዓለም አማካኝነት ማንነት ይገነባል፡፡ ማንነትን የመገንባት ሂደት ከግለሰብ ወደ ማህበር የሚሻገር ነው፡፡ ምክንያቱም በአንድ ጊዜ ማህበሩ አመለካከቱ አይቀየርም፡፡ ጊዜና መታሸትን ይፈልጋል፡፡ በካሳሁን ህይወት ውስጥም ሙሉ በሙሉ የምንረዳው ይህንኑ ነው፡፡ ከጥሬ ወደ ብስልነት (በአስተሳሰብ አንፃር) የተሻገረ ግለሰብ አርገን ልንስለው እንችላለን፡፡ በዚህ አጋጣሚ ለራሱ ሚያወርሰው አዲስ ማንነትን ነው፡፡ 'በመሬት ላራሹ' ዓመለካከት ውስጥ የሶሻሊዝም ርዕዮተ ዓለም አቀንቃኝ ሆኗል፡፡ Subjectነቱ አንድም ለርዕዮተ ዓለሙ ሲሆን፤ አንድም ለአቀንቃኙ ማህበር ነው፡፡

## 3.3. የቁጥጥር ተቋማት ተፅእኖና ጭቆና

ተቋማት ርዕዮተ ዓለምን በማስጠበቅ ሂደት ውስጥ የየራሳቸው ሚና ዓላቸው፡፡ የቁጥጥር ተቋማት የመጨረሻ ግብ ሁልጊዜም በመጨቆን የሚገኝ ነው፡፡ ይህ ጭቆና በአንድ ማህረበረሰብ ውስጥ የአካልና የዓመለካከት ተፅእኖ ይፈጥራል፡፡ የዚህ ተፅእኖ መነሻ ደግሞ ባብዛኛው ጠመንጃ አንጋቹ ነው፡፡ ምክንያቱም ያሻውን ቢፈፅም (ቢገል፣ ቢያቆስል) ጠያቂ የለውም፡፡

### 3.3.1. አካላዊ ጭቆና

ይህ ጭቆና የሚፈፀመው አንድም በማረሚያ ቤት፣ አንድም በወታደሩ ገደብ አልባ መብት ነው፡፡ አካላዊ ጭቆና በተለያየ መንገድ ይፈፀማል፡፡ ዋና ዓላማውም የወቅቱን ርዕዮተ ዓለም ማስጠበቅ ነው፡፡ ስለዚህ የቁጥጥር ተቋማቱ ለርዕዮተ ዓለሙ እንቅፋት መስሎ የታያቸውን ሁሉ ያጠቁበታል፣ተስፋ ያስቆርጡበታል፡፡ መሰረታዊ የመፍትሔ አቅጣጫቸውም ስቃይና ግርፋት ናቸው፡፡

> *ሁለት እጁን በጭኑ ውስጥ አሳልፈው እንደገና በእግሩ ቅልጥሞች በግራና በቀኝ አውጥተው ከፊት በኩል የፍጢኝ አሰሩት፡፡ ከዚያም በጉልበቶቹ መጋጠሚያና በጭኖቹ መካከል ባለፉት እጆቹ መካከል ፈልቅቀው ዘነዘናውን ብረት አስገቡበት፡፡ . . . ጧ! ጧ! ጧ! ጧ! ተናገር! አውጣ!. . . "እሄሄ! ኮረት ድንጋይ የሆነ እግሩ አሁን ምን ይሰማዋል ብለህ ነው፡፡ ሌላውን ብትሞክር አይሻልም?" . . . የሚቃጠለውን ሻማ ከብልቱ ላይ አንጠባጠቡበት፡፡ . . .ካሳሁን ከአካል ስቃዩ ሌላ ለአጭር ጊዜ በህሊና ጭንቀት ተወጠረ፡፡ (ዋዜማ፣ 194)*

ይህ ሁሉ በካሳሁን ላይ የሚፈፀመው ተሰዶ የመጣውን ባላገር አሳምፆታል ብለው ስላሰቡ ብቻ ነው፡፡ አንድም በማሰቃየት ርዕዮተ-ዓለሙን እናስጠብቃለን ብለው ስለሚያምኑ ነው፡፡ አንድም የፊውዳል ስርዓቱ የፀና ስለነበር አንድ ባላገር የስቃይ ገፈት ቀማሽ ቢሆን ለነሱ ተራ ነገር ነው፡፡ ምክንያቱም እንኳን የአንድ ባላገር ስቃይ የእልፍ ባላገር ስደትና ረሃብ አላሳሰባቸውም፡፡ በርዕዮተ ዓለሙ እሳቤ ባላገር ሁሌም ተደራጊ *(Object)* ነው፡፡ የሚባለውን ብቻ ሚሰማ፣ የተሰጠውን ብቻ ሚቀበል፡፡ የተደራጊነቱ ምስጢር ደግሞ ይበልጥ "ኮረት ድንጋይ የሆነ እግሩ" በሚለው ውስጥ ይጎላል፡፡

የካሳሁንን እግር እንደ "ኮረት ድንጋይ" ያደደረው ህይወቱ ነው፡፡ አንድም የረሃብን ገፈት ቀምሷል፡፡ አንድም በባዶ እግሩ ሲያርስ ኑሯል፡፡ አንድም ለባላገሩም ሆነ ለገፀ-ባህሪው መጓጓዣው እግሩ ነው (መኪና አያውቅም)፡፡ ኮረቱ፣ ድንጋዩና እግሩ ትይዩ ናቸው፡፡ ባንዳቸው ውስጥ አንዱ ይነበባል፡፡ አንድም ድንጋይ ጠንካራ ነው፡፡ አንድም ባላገሩ ብዙ ፈተናን ተጋፍጦ ማለፉ የጥንካሬው ምንጭ ነው፡፡ አንድም ድንጋይ ይወረወራል፡፡ አንድም ባለገሩ እጣ ፈንታው ቢጎድል ከወዲያ ወዲህ ይጥሉታል፣ ያዞሩታልም፡፡ በካሳሁን የግርፋት ስቃይ ውስጥ በተዘዋዋሪ የሚታየው የባላገሩ ሙሉ ህይወት ነው፡፡ ወጥተው የወረዱት ፈተና በካሳሁን ስቃይ ውስጥ ገዘፍ ነስቶ ይታያል፡፡ ለዚህ ሁነኛ ማስረጃ የሚሆነው የስቃይ ሂደቱ እስከ "ብልቱ" ድረስ መሻገሩ ነው፡፡ አንድም ብልት ትውልድ ነው፡፡ አንድም ብልት

ሃሴት ነው፡፡ አንድም ብልት ድብቅ ነው (በግላጭ አይታይም)፡፡ አንድም ብልት ህይወት ነው፡፡ በካሳሁን ብልት ላይ የደረሰው ስቃይ የመላው ባላገር ስቃይ ነው፡፡ አንድም ተደብቆ የኖረው ባላገር በረሃብና ቸነፈር ምክንያት ወደ ከተማ እንዲወጣ ተገዷል፡፡ አንድም ባላገሩ ደስታና ሃሴቱን ካጣ ሰንብቷል፡፡ አንድም የስቃዩ አካል የሆነው ባላገር ባንድ ዘመን ትውልድ ይፈረጃል፡፡ ስለዚህ የካሳሁን "ብልት"ና የባላገሩ ማህበር ገፅ በገፅ ይናበባሉ፡፡

የካሳሁን ስቃይ በቀጥታ የሚሻገረው ወደ አእምሮ ነው፡፡ ይህን ሽግግርም "በህሊና ጭንቀት ተወጠረ" በሚለው ሃሳብ ውስጥ እናገኘዋለን፡፡ አንድም የአካል ስቃይ ከአእምሮ ጋር ዝምድና መፍጠሩ ተፈጥሯዊ ነው፡፡ አንድም በዚህ ወቅት ጎሚ ይጠነሳሳል (ቀደም ሲል በነበረው ርዕስ ስር ካሳሁን ስለ "ዓመፅ" ያለው አመለካከት በአእምሮው ቅርፅ የመያዙ ምስጢር ይኸው ነው)፡፡ ይህ ስፍራ በአዲስ ማንነት ጉዞው ውስጥ ራሱን የቻለ አስተዋፆ ነበረው ብዬ አምናለሁ፡፡ ምክንያቱም የደረሰበት ስቃይና ተፅእኖ ሌሎች ተያያዥ ሃሳቦችን መገንዘብ እዲችል መንገድ ከፍቶለታል፡፡

ይህ ካሳሁን ላይ የሚካሄደው ጭቆና የመፈፀሚያ ስፍራው "እስር ቤት" ነው፡፡ እስር ቤት ደግሞ የቁጥጥር ተቋማት አንድ አካል ነው፡፡ በተለይም ደግሞ በወቅቱ ላለው ርዕዮተ ዓለም አደጋ ናቸው ተብለው የሚታሰቡ ሰዎች ሁሉ መታጎሪያቸው ይኸው ስፍራ ነው፡፡ እስር ቤት በድርሰቶቹ ውስጥ አንድም አካላዊ ጥቃት ማድረሻ ሲሆን፣ አንድም ደግሞ ለሰው ባህሪ ያልተመቸ ቦታዎች መገኛም ነው፡፡

"ከትውከት እስከ ዓይነ ምድር ያለው ቆሻሻ፣ በዚያ ላይ አዲስ የገቡት ሰካራሞች ሆድቃቸው ተገልብጦ የሚወጣ እስኪመስል ድረስ ቧ! እያደረጉ የሚለቁት ሁሉ ተጨምሮ ማስረሻ ከአንድ ትልቅ የመፀዳጃ ጉድጓድ ውስጥ የተዘፈቀ መሰለው" (*ማግስት*፣ 208)፡፡ ስፍራው "ከሰብአዊነት" ባህርይ ጋር አይጣጣምም፡፡ ለአካላዊ ተፅእኖና ለመንፈስ መታወክ ይዳረጋል፡፡በመሆኑም እስር ቤት ስልተ-ብዙ ነው፡፡ ማስረሻ ተገዶ ለገባበት ርዕዮተ ዓለም ያሳየው ለዘብተኛ አቋም ለእስር ዳርጎታል፡፡ እስሩ አንድም ማስተማሪያ (ጠያቂ እንደሌላቸው ማሳያ) ነው፡፡ አንድም የራስ ማድረጊያ ነው፡፡

ዓላማው ይህ በመሆኑም በማስረሻ ላይ የከፋ አካላዊ ጭቆና አናስተውልም፡፡ ነገር ግን ስፍራው በራሱ አካላዊ ጨቋኝ ነው፡፡ ለርእዮተ ዓለሙ ማስፈፀሚያነት መዋል ያልቻለ ሰው የግድ ሰብአዊነቱን ያጣል፡፡ ሰብዓዊነቱን በመንፈግ ለራስ ዓላማ ያውሉታል፡፡ ርዕዮተ

ዓለሙንም በዚህ መልኩ ያስጠብቁበታል፡፡ ጭቆናው አንድም በሰው አንድም ምቹ ባልሆነ ስፍራ ይቀነባበራል፡፡ የቅንብሩ ውጤት የተዘረጋውን ስርዓት ማስጠበቅ ነው፡፡ "ትውከት"፣ "አይነ ምድር" ወዘተ. ምንም እንኳ የሰው ልጅ ስጋዊ ውጤቶች ቢሆኑም፤ በባህሪ ደረጃ ግን ከሰው ጋር ተቃቅፎ ኗሪ አይደሉም፡፡ አቅርበን ብንይዛቸው ሰውነትን ያስረሳሉ፡፡ አንድም ከህይወታችን አርቀን ልንጥላቸው የግድ ነው፡፡ አንድም ሰው ክቡር ነው፡፡ ነገር ግን በርዕዮተ ዓለም ጣጣ ውስጥ (በቁጥጥር ተቋማት አማካይነት) ይህ ሁሉ ይጣሳል፡፡ ከሰው በላይ የሚታየው የተዘረጋው ርዕዮተ ዓለም ነው፡፡ ሁሉም የስርዓቱ ኗሪዎች ከስርዓቱ በታች ሊሰፍሩ የግድ ነው፡፡ ያለበለዚያ ርዕዮተ ዓለሙ ሊቀጥል አይችልም፡፡

እንዲያውም ርዕዮተ ዓለም በፈተና ውስጥ  የሚዘልቅ ፅንሰ ሃሳብ ነው፡፡ ነገር ግን ፈተናውን በቁጥጥር ተቋማቱ አማካይነት ይጋፈጠዋል፡፡ በዚህ  ሂደት ውስጥ በአንድም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ርዕዮተ ዓለሙ ነፍስ ይዘራል፡፡ አንዳንዴም በፈተናው ብዛት ይለወጣል፡፡ አንዳንዴም በአጣብቂኝ ውስጥ ይቀጥላል፡፡

> *. . .  ከሰፈር ውጭ ታፍነው ገፈርሳ፣ ሾላና የካ ጫካ ድረስ እየተወሰዱ ህይወታቸው እንደሸረሪት በቀጠነ ድር ተንጠልጥላ እስክትተርፍ ድረስ ተወቅተው፣ ታሽተው ተቀጥቅጠው የተጣሉ ወጣቶች ብዙ ናቸው፡፡ እንደምንም ከሰፈራቸው ተመልሰው ቁስላቸውንና ጥቃታቸውን እየጠገኑ ሲያገግሙ በቀላቸውን አብረው ያረግዛሉ፡፡ ከቤታቸው እንደ ወጡ ሳይመለሱ የቀሩም አሉ፡፡ (ማግስት፣ 49)*

ይህ የማህበረሰባዊነት ርዕዮተ ዓለምን ለማስቀጠል ሲባል ይወሰድ የነበረ እርምጃ ነው፡፡ እርምጃው እጅጉን አካላዊ ነው፡፡ ጠመንጃ አንጋቹ የርዕዮተ ዓለሙ አስጠባቂ ነው፡፡ የሚያስጠብቀው በምክርና ግሳፄ አይደለም፡፡ ይልቁንም ስቃይ አዘል በሆነ አካላዊ ጥቃት ነው፡፡ በፅንሰ ሃሳብም ሆነ በገቢር ርዕዮተ ዓለሙ ከሰው በላይ ነው፡፡ "ተወቅተው"፤ "ታሽተው"፣ "ተቀጥቅጠው" የሚሉት ቃላት የስቃይ ማድርያዎች ናቸው፡፡ አንድም የሃይል ውጤቶች ናቸው፡፡ አንድም ኢ-ሰብአዊ ናቸው፡፡ አንድም "የነብር ጣት" በሆነው ትውልድ ላይ ያረፉ ናቸው፡፡ አንድም ከመኖር ወዳለመኖር ያዛውራሉ፡፡ በመኖርና ባለመኖር ውስጥ የሚፋጠጠው "ሰው" ና "ርዕዮተ ዓለሙ" ነው፡፡ የፍጥጫው መጨረሻ  አንድም "ሞት" ("እንደወጡ የቀሩ አሉ")፤ አንድም "ለውጥ" ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ውጤቱ ምንም ይሁን ምን የቁጥጥር ተቋማቱ ሚና ርዕዮተ ዓለሙን ማስጠበቅ ነው፡፡

የቁጥጥር ተቋማትን በማንኛውም ርዕዮተ ዓለም ውስጥ ከ"ሃይል" ነጥሎ ማየት አይቻልም፡፡ አንድም ሃይሉ "ጠመንጃ" ነው፡፡ አንድም ፈፃሚው "ጠመንጃ አንጋቹ" ነው፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ ሁልጊዜ ማህበሩ ከላይ ወደ ታች ይታያል፡፡ አንድም ርዕዮተ ዓለም ማደርያው ራስ (አእምሮ) ነው፡፡ ከራስ ተወልዶ ሌላውን ይቀጣል፣ ያርማል እንዲሁም ይገላል፡፡ በዚህ ሂደት ማህበረሰቡ ከታች ወደ ላይ አንጋጣጭ ነው፡፡ ማንጋጠጡ አንድም የተባለውን ሊቀበል ነው፡፡ አንድም የሚሰራውን ሊታዘብ ነው፡፡ አንድም ባየው አምፆ፣ ባየው ሊቀጣ ነው፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ ጭቆና የግድ ይኖራል፡፡ ጭቆናው አንድም የርዕዮተ ዓለሙን የበላይነት ማስጠበቂያ ነው፡፡ አንድም በማህበሩ ውስጥ የአመፅ መፀነሻ ("ሲያገግሙ በቀላቸውን አብረው ያረግዛሉ") ነው፡፡ በርዕዮተ ዓለሙ አስጠባቂ (በቁጥጥር ተቋሙ) እና በማህበረሰቡ መካከል ህይወት አንድም በፍራቻ፣ አንድም በመጋፈጥ ይቀጥላል፡፡ የቁጥጥር ተቋማት ሃይል አንድም የበላይነትን መጎናፀፊያ ነው፡፡ አንድም በተቃራኒው የማህበሩን የበታችነት ማሳያ ነው፡፡ ለምሳሌ፣ ከዚህ አኳያ የፊውዳሉን ዘመን የባላገር ህይወት ከቁጥጥር ተቋማቱ አንፃር ማጤን ይቻላል፡፡

> *"የንጉስ ትዕዛዝ ትጥሳለህ?"*
> *"በስመአብ ወልደመንፈስ ቅዱስ፣ ከንጉስ ጋር ማን ይጣላል? ከብረት በሬ ጋር ማን ይጋጫል?" (ዋዜማ፣ 13)፡፡*

በዚህ ውስጥ የቁጥጥር ተቋሙ የበላይ ሲሆን፣ የባላገሩ ማህበረሰብ ደግሞ የበታች ነው፡፡ ምክንያቱም የሃይል ሚዛን ልዩነት በመሃከላቸው አለ ("በኛ አቅም ከመንግስት ጋር ታግለን አንወጣውም" [ዋዜማ፣ 179] የሚለውን የካሳሁንን ንግግር ይመለከቷል)፡፡ የበላይነቱን ሚዘረጋው አንድም ርዕዮተ ዓለሙ ነው፡፡ አንድም ተቀብሎ ሚያስፈፅመው የቁጥጥር ተቋሙ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ጉዳይ በማህበረ-ባህሉና በማህበረ-ፖለቲካው የፀና ነው፡፡ በባላገሩ ንግግር ውስጥ ግን ይህ ገናን ጉዳይ አገላለፁ ረቂቅና ስልታዊ ነው፡፡ ባላገሩ ሊያስተላልፍ የፈለገውን መልዕክት በ "በሬ"ና "ብረት" ውስጥ ደብቆ ገልፆታል፡፡ አንድም በሬ ቀንበርና ሞፈር ጭነው ይነዱታል፡፡ አንድም በሬ ቀንዱ ይዋጋል፡፡ በዚህ የበሬ ፅንሰ ሃሳብ ውስጥ "ብረት" ከፊቱ ቀድሟል፡፡ በበሬ ውስጥ ወታደሩ፣ በወታደሩ ውስጥ በሬው ፅንሰ ሃሳባዊ ዝምድና ዓላቸው፡፡ አንድም በሬው ወታደሩ ነው፡፡ አንድም ብረቱ ጠመንጃ ነው፡፡ የሁለቱ ድምር ውጤት ጠመንጃ አንጋቹ ነው፡፡ ታዲያ ባላገሩ እንዴት ይህን ደፍሮ

ይጋፈጣል? አንድም እንስሳ አእምሮና ልቡና የለውም እንደፈቱት ተጓዥ እንዳሰሩት አዳሪ ነው፡፡ በራሱ ሚፈፅመው አንዳችም ነገር የለውም፡፡

የቁጥጥር ተቋሙ አንድ አካል የሆነው ጠመንጃ አንጋችም ከዚህ ውጪ አይደለም፡፡ እንደታዘዘው ኗሪ ነው፡፡ ከዚህ ልቡናና አሳቢ አእምሮውን ከተነፈገ አካል የሚገነባው ሀይል እጅጉን አስፈሪ ነው፡፡አንድም ገፍቶ ቢመጣ አይመልሱትም፡፡ አንድም ከዚህ "በሬ" ጋር መጋጨት አደጋው የከፋ ነው፡፡ መጀመርያ በቀረበው "የንጉስ ትዕዛዝ ትጥሳለህ!?" በሚለው ጥያቄ ውስጥ በቀጥታ የሚታየው የንጉሱ ወንበር አይደለም፡፡ ይልቁንም የስርዓቱ ርዕዮተ ዓለማዊ ግዝፈት ነው፡፡

የቁጥጥር ተቋሙ የርዕዮተ ዓለሙን ገናንነት ያስረዳናል፡፡ አንድም በማስፈራራት፣ አንድም አካላዊ ጭቆና በማድረስ የሚዛኑን ክብደት ያፀናል፡፡ ስለዚህ "ሃይል" የርዕዮተ ዓለሙ ግልባጭ ሆኖ የተሳለው የቁጥጥር ተቋሙ (የጠመንጃ አንጋቹ) መለያ ነው፡፡ በጥቅሉ በልቦለዶቹ ውስጥ የቁጥጥር ተቋሙ ሚና  በማስፈራራትና በመጨቆን የገዥውን ስርዓት ማህበር ርዕዮተ ዓለም ማስጠበቅ ነው፡፡ ጭቆናው በህዝቡ ላይ የሚያሳድረው አንዳች ስጋት ስላለ ሙሉ በሙሉ ወደ አመለካከት መጨቆን ይሸጋገራል፡፡ አንድም ያለውን ጉዳይ እንዳለ ለመቀበል ይገደዳል፡፡ አንድም የግል አስተያየቱን እንዳይናገር ይሆናል፡፡

### 3.3.2. የአመለካከት ጭቆና

ማህበረሰቡ በተለያየ መንገድ በቁጥጥር ተቋማቱ ይጨቆናል፡፡ ጭቆናው አንድም በአካል፣ አንድም በአመለካከት ነው፡፡ በተለይ ይህ የአመለካከት ጭቆና ማስረሻ በተባለው ገፀ-ባህርይ ላይ ጎልቶ ይታያል፡፡ ደፍሮ በመናገርና የግል ርዕይን በመግለጥ የሚመጣ ጣጣ እንዳለ የገባው ይመስላል፡፡

> *የእግዜር ውሃ የጠማውና ሻምፓኝ የሚፈልገው የሁለቱም ፍላጎት አልረካም ተብሎ እኩል መታየት አለበት? ወይስ አንዱ የሚተዳደርበትን ማሳዬን ተብሎ እኩል መታየት አለበት? ወይስ አንዱ የሚተዳደርበትን ማሳዬን ተብሎ ... ከሃምሳ ጋሻ ጋር ሊቀላቅላት ቢሞክር ሁለቱም አልለቅም ሲል ሌላው ከሃምሳ ጋሻ ጋር ሊቀላቅላት ቢሞክር ሁለቱም በመብታቸው እኩል አልረኩም ሊባል ነው? ብሎ አለቃውን ሊጠይቅ ከጀለ፡፡ ነገር ግን እንደዚህ አይነት መናፍቃዊ አስተያየት ስንኳ ከአለቃ ጋር የትም ቦታ ቢሰነዝሩት አደገኛ መሆኑን ስለሚያውቅ ስሜቱን ገታ አረገና "እሱማ ነው" አለ፡፡ (ዋዜማ፣ 153)*

በጊዜው መናገር ብዙ ጣጣ ዓለው፡፡ ያለ ጊዜ ሞትን፣ ስቃይን ወዘተ. እንደመጥራት ይቆጠራል፡፡ የማስረሻ ግላዊ ርእይ በሆድ አድሮ ከህሊና ጋር በሚደረግ የሃሳብ ልውውጥ የሚጠናቀቅ ነው፡፡ አመለካከቱ ወደ ግለሰብ አይሸጋገርም፡፡ ምንም እንኳ አመለካከቱ መልካምና ሚዛን ደፊ ቢሆንም ከውስጣዊ መብሰልሰሉ ውጪ ለሌላው አይነገርም፡፡ ሃሳቡ አንድም (ከባላገር በመወለዱ) የገበሬው ጭቆና ሲያንገበግበው የተፀነሰ ነው፡፡ አንድም ሰብአዊነትን ከግምት ውስጥ በመከተቱ ነው፡፡ ይሁን እንጂ እንዲህ አይነቱ አመለካከት ለገዥው መደብ እንቅፋት የመሆን ያህል ይቆጠራል፡፡ ግልፅ ቢወጣ መዘዙ ብዙ ነው፡፡ ማስረሻ ስሜቱን ራሱ ለራሱ አካፍሎ ያበቃል (ማን ከብረት በሬ ጋር ይጋጫል!? የሚለውን ይመለከቷል)፡፡ የቁጥጥር ተቋሙ ግዙፍ ነው፡፡ እንዲህ አይነቱ የማሰረሻ እምነት ደግሞ ከጠላትነት ያስፈርጃል፡፡

አንድም የፊውዳሉን ስርዓት ለመናድ እንደመሞከር ይቆጠራል፡፡ ዘመኑ በራሱ ለእንዲህ አይነቱ አመለካከት ቦታ የለውም፡፡ እንደ "መናፍቅ" ያስቆጥራል፡፡ ከዛም ባለፈ የጭቆና ቋት ውስጥ ራስን እንደመከተት ይወሰዳል፡፡ "አደገኛ"ም ነው፡፡ አደገኛነቱ አንድም የሞት ጣጣ አለበት፡፡ አንድም ራስን ለስቃይ መዳረግ ነው፡፡ አንድም ከማይቋቋሙት "ሃይል" ከጠመንጃ አንጋቹ ጋር መጋፈጥ ነው፡፡ በአመለካከት ጠንክሮና ጎልብቶ እዲስ ርዕይ መፍጠር የዘመኑ ርዕዮተ ዓለም ክፉ በሽታ ተደርጎም ይታያል፡፡ ስለዚህ ከራስ ማውራቱ፣ ከራስ ጋር መወያየቱ "ከመሞት መሰንበት" እንዲሉ የተሻለው አማራጭ ነው፡፡

ከአንድ ግለሰብ የመነጨ ተቃራኒ አመለካከት ብቻውን ጦር መዞ የቁጥጥር ተቋሙን ሊመክተው ወይም ሊጋፈጠው አይችልም፡፡ ማስረሻ ይህ የገባው ይመስላል ሁሌም ጥልቅ የሆነ ሃሳቡን የሚያጋራው (የሚያወያየው) ለራሱ ብቻ ነው፡፡ ለሌላው አሻግሮ አያቃብለውም፡፡ በራሱ ውስጥ ደብቆ ለራሱ ብቻ ይገልፅለታል፡፡ ራሱ ይታዘባል፣ ራሱ ይገረማል፡፡ ውይይቱ አንድም ከ"አለቃ" ጋር የተደረገ ነው፡፡ አንድም አለቃ የሃይል አምሳያ ነው፡፡ አንድም አለቃ የገዥውን መደብ ርዕዮተ ዓለም ማስፈፀሚያ ቱቦ ነው፡፡ አንድም አለቃነቱ ለስርዓቱ ባለው ቅርበት ነው፡፡ በቅርበቱ ውስጥ እምነት፣ ዓመለካከት ወዘተ. ሁሉ የሚፈሰው ከላይኛው መዋቅር ነው፡፡ ያለቅነቱ ፅንሰ ሃሳብ ከላይም ሆነ ከታች የተቀበለውን ማስተጋባት ነው፡፡ ስለዚህ የማስረሻ አመለካከት ከሆድ ቢያልፍ ውጤቱ የመረረ ነው፡፡ በመሆኑም ማስረሻ ከራስ ተጋብቶ መኖርን የመረጠ ገፀ-ባህርይ ነው፡፡

*. . . ንዴት እንደማነቅ ዓለው፡፡ አይኑን ወደ ወይዘሮ ዘርፊሸዋል ቀና ሲያደርግ የሚለውን ለመስማት በመጠባበቅ ትክ ብለው ሲመለከቱት አገኙ፡፡ አስተያየታቸውና ግዝፈታቸው ገንፍሎ ሊወጣ የቃጣው ኃይለ ቃሉን ሟሸሸ አደረገው ተራራ የሚያክሉ ናቸው፡፡ ከተራራ ጋር ሰው እንዴት ይጋተራል? (ዋዜማ፣ 113)፡፡*

የማስረሻ ስሜት መነሻና የስሜት መግቻ በሌላ ግለሰብ የመታገዝ አጋጣሚ የለውም፡፡ ይልቁንም አጋዥና አራሚው ልቡናና አእምሮው ነው፡፡ "ግዝፈታቸው" አንድም አካላዊ አንድም ፅንሰ ሃሳባዊ ነው (በመደብ ልዩነት ውስጥ ቀደም ሲል ያብራራሁትን ሃሳብ ይመለከቷል)፡፡ ለማስረሻ ወይዘሮ ዘርፊሸዋል "ተራራ የሚያክሉ ናቸው"፡፡ ተራራነታቸው አንድም ለገዥው መደብ ባላቸው ቅርበት ይገለፃል፡፡ ተራራነታቸው አንድም ርዕዮተ ዓለሙ በተከለው የቁጥጥር ተቋም አንፃርም ይታያል፡፡

ተራራነታቸው አንድም የላይኛው መደብ ምሳሌነታቸው ነው፡፡ ለማስረሻ የፊውዳሉ ስርዓት፣ ርዕዮተ ዓለሙ፣ በርዕዮተ ዓለሙ ጥላ ስር የሚገኙ ሰዎች ወዘተ. ሁሉ "ተራራ" ናቸው፡፡ ሃይል ዓላቸው፡፡ ታዲያ ይህን "ሃይል" እንዴት ንቆ መጋፈጥ ይቻላል? ስለሆነም ማስረሻ ስሜቱ በግላጭ አይወጣም፡፡ ሃሳብና ዓመለካከቱ ሁሉ በሆዱ ተፀንሶ፣ በሆዱ አብቦ በሆዱ የሚኮላሽ ነው፡፡ ከራሱ ድንበር አያልፍም፡፡ "ከተራራ ጋር ሰው እንዴት ይጋተራል?" ሰው በአካል ተራራን አይጎዳኘውም፡፡ በመጠንም በባህሪም ለየቅል ናቸው፡፡ ነገርግን በተራራው ውስጥ የገዥው መደብ ርዕዮተ ዓለም፣ የላይኛው መደብ ወገንተኞችና የቁጥጥር ተቋሙ ገፅ በገፅ ይነበባሉ፡፡

ተራራውን ከስር ወደ ሽቅብ የሚያየው የባላገሩ ማህበርና የሱ ርዝራዦች (የማስረሻ ቢጤዎች) ናቸው፡፡ የሚያስቡት ሚፈፀምላቸው ሳይሆኑ፤ የታሰበላቸው ሚተገበርላቸው ማህበር ናቸው፡፡ ከሽቅብ ቁልቁል የሚታዩ "ኢምንቶች" ናቸው፡፡ ማስረሻ የዚሁ ማህበር ውጤት ነው፡፡ ቁልቁል እንደሚታይ ያውቀዋል፡፡ ስሜቱን በግልፅ አያስተጋባም፡፡ በአካል እየታየ በልቡናው ፎሪ የሆነ ሰው ነው፡፡ ምንም ያህል የቁጣና የ"ሃይለቃል" ስሜት ቢጠናወተው የቆመበትን ስፍራ ስለሚያውቀው ራሱን ይገታል፡፡

"እሱ ሳይፈልግ በወይዘሮ ዘርፊሸዋል ውሳኔ ተዳረ፡፡ እሱ ሳይፈልግ በወይዘሮ ዘርፊሸዋል ውሳኔ ሰርጉ ደሴ ከተማ ሆነ. . ." (*መባቻ*፣ 20)፡፡ በዚህ ውስጥ ማስረሻን ተንቀሳቃሽ "እቃ" ሆኖ ነው የምናገኘው፡፡ "ሳይፈልግ" በሚለው ቃል ውስጥ የዓመለካከቱ ገደብ በግልፅ ይታያል፡፡ ማስረሻ አድራጊ ሳይሆን ተደራጊ ነው፡፡ በተቀደደለት ቦይ መፍሰሱ የግድ

ነው፡፡ እንዳደረጉት ይሆናል እንጂ፤ 'እምቢ ባይነት'ን አልታደለም፡፡ እንዲያውም ልቦናውና አእምሮው ተገደው በቀመሩት ንድፍ ውስጥ የሚኖር ጭቁን ሰው ነው፡፡ በራሱ እድል ላይ ራሱ እንዲወስን አልታደለም፡፡ በራስ ተነሳሽነት በሚፈፀም አስተውሎትና ንግግር ውስጥ የሚቀርብ ተቃውሞ መዘዙ ብዙ ነው፡፡ በመሆኑም የተባለውን ለመቀበል ተገዷል፡፡ አንድም በተባለው ብቻ እንዲኖር የሃይል ሚዛኑ ያስገድደዋል፡፡ አንድም መናገርንና መሞገትን በለመደ ማህበር አላደገም፡፡ አንድም እንደፈለጉ መናገርን ርዕዮተ ዓለሙ አይፈቅደውም፡፡ አንድም ያሳደገው ማህበር ያስለመደውን ተደራጊነት "እሱ" ብቻውን ሊለውጠው አይቻለውም፡፡ በተለመደው ብቻ መቀጠሉ የግድ ነው፡፡ መጋፈጥን አይሻም ("ታፈሱ" የተባለችው ገፀ-ባህርይ "ህሊናህ በጣም ለስላሳ በመሆኑ . . . እንዳይቧጨርብህ አትጋጭም፣ አትፋጭም፡፡ አትፋጠጥም፡፡ ራስክን ትቀብራለህ ወይም ትሸፍናለህ" [*ማግስት*፣117] ያለችውን ይመለከቷል)፡፡ ማስረሻ ሙሉ ህይወቱ ከዚህ ውጪ አይደለም፡፡ "ታፈሱ" የህይወቱን ትርጓሜ እንደመስታወት የገለጠችው ይመስለኛል፡፡

> *'ማይ ፋት ዲሞክራሲያዊ' አለ ማስረሻ በሆዱ ከብሽቀቱ የተነሳ አስተሳሰቡን የእንግሊዘኛ ቋንቋ ወስዶበት እንዲህ አርጎም ዲሞክራሲ የለ! በዲሞክራሲያዊ መንገድ ፈቃዴ ምርጫዬ ተጠይቄ ነው ከዚህ ጣጣ የገባሁት በቃል ግን ትንፋሽ አልወጣውም፡፡ ደረበን ቀና ብሎም አላየውም፡፡ (ማግስት፣ 110)*

ማስረሻ በውስጡ የሚያብሰለስላቸው ሃሳቦች ጥልቅ ናቸው፡፡ ነገር ግን በግልፅ አይቀርቡም፡፡ ማደርያና መኖርያቸው ሆዱ ነው፡፡ ይህ የዓመለካከት ጭቆናው ከፊውዳሉ ርዕዮተ ዓለም ወደ ሶሻሊዝም በተደረገው ለውጥም ይቀጥላል፤ አይቋረጥም፡፡ ለማስረሻ "ሆዱ" ውክልናው ለምግብ ብቻ አይደለም፡፡ ይልቁንም በውስጡ ለሚያብሰለስላቸው ሃሳቦች ነው፡፡ አንድም ማስረሻ መኖር የሚሻው በራሱ ዓለም ነው፡፡ አንድም ማስረሻ ሰብአዊነትን ይሻል፡፡ አንድም የሚዘረጋው ርዕዮተ ዓለም ከሱ በተቃራኒ ነው፡፡ አንድም ፍርሃት ጋር መቆራኘቱ ነው፡፡ ፍርሃትና ውስጣዊ መብሰልሰሉ ከርዕዮተ ዓለሙና ከቁጥጥር ተቋሙ ይመነጫል፡፡

በ "ዲሞክራሲ" አለመኖር ውስጥ የማስረሻ ነፃነት ማጣት በግልፅ ይታያል፡፡ ባሻው መንገድ መጓዝ፣ ባሻው ምርጫ ማድር፣ እንዳሻው አስቦ እንደ ልብ መናገር ወዘተ. የርዕዮተ ዓለሙ ፅንፈኝነት መሳያዎች ናቸው፡፡ የነዚህ ነገሮች መከሰት የቁጥጥር ተቋሙን ነክቶ እንደመቀስቀስ ይቆጠራል፡፡ ስለዚህ ማስረሻ አንዳቸውንም ማድረግ አይሻም፡፡ ከራሱ ጋር ውሎ ከራሱ ጋር ያድራል፡፡ "በቃል ግን ትንፋሽ አልወጣውም" መተቸትን ርዕዮተ ዓለሙ

አይፈቅድለትም፡፡ ያልተፈቀደን መጣስ ወደ አካላዊ ጭቆና ያሻግራል፡፡ ይህም በእስር ወይም በድብደባ ሊገለፅ ይችላል፡፡ ስለዚህ ሁሌም ሽሽቱ ከንዲህ አይነቱ አጋጣሚ ነው፡፡ ሞጋች ሳይሆን አድማጭና ታዛዥ ይሆናል፡፡ የስቃይ ገፈት ቀማሽ መሆንን አይሻም፡፡ አመለካከቱን ደብቆ ይኖራል፡፡ አመለካከቱን መደበቁ አንድም ጠመንጃ አንጋቹን ሽሽት ነው፡፡ አንድም በሱ ርዕይ ርዕዮተ ዓለሙ ፍሬ ፈርስኪ ነው፡፡ ነገር ግን ፊት ለፊት አይጋፈጠውም፡፡ አካላዊ ጭቆናውን በጣም ይፈራል፡፡ በራሱ ዓመለካከት ውስጥ ራሱን ይቀብራል፡፡ በጥቅሉ የማስረሻ የአመለካከት መጨቆን የቁጥጥር ተቋሙን ከመፍራት የሚመነጭ ነው፡፡ በመሆኑም መናገርና ሃሳቡን መግለፅ አይችልም፡፡ ችሎና ውጦ ማሳለፍ ባህሪው ነው፡፡ በጥቅሉ የቁጥጥር ተቋማት ጨቋኝ ናቸው ሲባል፣ አንድም በአካል አንድም በአመለካከት ነው፡፡

## 3.4. የግንዛቤ ተቋማትና ርዕዮተ-ዓለማዊ ተቃርኖ

በማዕበል የአብዮት ዋዜማ፣ በማዕበል የአብዮት መባቻ እና በማዕበል የአብዩት ማግስት ውስጥ የግንዛቤ ተቋማት ተመሳሳይ ተግባር የላቸውም፡፡ በተለይም ደግሞ የ "መገናኛ ብዙሃን"ና "ትምህርት ቤቶች" እንዳቸው ካንዳቸው የተቃርኖ ስሜት ይነበብባቸዋል፡፡

### 3.4.1. የመገናኛ ብዙሃን እንደፕሮፖጋንዳ ማስፈፀሚያ

በሁለቱም (በፊውዳሉም ሆነ በሶሻሊዝሙ) ስርዓቶች የመገናኛ ብዙሃን ሚና ተመሳሳይ ነው፡ ፡ በተለይም የዘመኑን ርዕዮተ ዓለም ደጋፊዎችና ሰባኪዎች ናቸው፡፡ አንድም ለተተከለው ስርአት ያደላሉ፡፡ አንድም የታዘዙትን ያስተጋባሉ፡፡

> *የዘንድሮው ሰብል በማናቸውም ስፍራ ቢሆን ከዳር እስከዳር በመያዙ እህሉን ምን አይነት ጎተራ ይችለዋል? ተብሎ የሚያጠግብ የተስፋ ትንቢት ተነግሮለታል፡፡ . . . ባውድማው ላይ የተንጣለለውን እህል ወቅቶ ለማግባት ትጋትን የሚጠይቅ ሆኗል፡፡ (ዋዜማ፣ 96)*

ይህ ሃሳብ በድርሰቱ ውስጥ አዲስዘመን ጋዜጣ ያሰፈረው ነው፡፡ ሃሳቡም ሙሉ ለሙሉ ለፊውዳሉ ስርዓት ያደላ ነው፡፡ የጊዜውን ርሃብ፣ ችግርና ሰቆቃ የረሳና "በሬ ወለደ" አይነት መልዕክት ነው፡፡ አንድም ጋዜጣው ቅርበቱ ከህዝቡ ይልቅ ለጊዜው ርዕዮተ ዓለም ነው፡፡ አንድም የመጨረሻ ግቡ ለገገር መደቡ ስርዓትና ስኬት መጣር ነው፡፡ ስለሆነም የዘመኑን

እውነታ በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ ይክዳል፡፡ መንፈሱ በጠቅላላ የገኘው መደብ ነው፡፡ ህዝቡ ላይ በዘመኑ የደረሰው ስቃይና ስደት ጋር ተናቦ የቀረበ ሚዛናዊ መረጃ አይደለም፡፡

አንድም ህዝቡ ለመገናኛ ብዙሃኑ አሻንጉሊት ነው፡፡ አንድም የህዝቡ ፍላጎትና ስሜት ለመገናኛ ብዙሃኑ ፍሬ ፈርስኪ ነው፡፡ ይልቁንም የሚያሳስባቸው የገገር ስርዓቱ ህልውና መጠበቅ ነው፡፡ ስለሆነም "እህሉን ምን አይነት ጎተራ ይችለዋል?" በሚል ሃሳብ የህዝቡን ያልጠገበ ሆድ ይሸሩታል፡፡ አንድም የመገናኛ ብዙሃኑ ምግብነቱ ለአእምሮ ነው፡፡ አንድም ግብና ዓላማው የተራበውን ወገን ባልተራበው ልቡና ውስጥ ማስረሳት ነው፡፡ በዚህ ሂደት ደግሞ የሚጠበቀው በገገር መደቡ የተዘረጋው ስርዓት ነው፡፡ በህዝቡ አይን የመገናኛ ብዙሃኑ ሃሳብ ውሸትና ምናብ ሰራሽ ነው፡፡ የተገለፀበት መንገድ ከሚኖሩበት ሁነት ጋር ፈፅሞ አይናበብም፡፡ አንድም እጦትና ብክነታቸው በመምነሽነሽ ተስፋ ተተክቷል፡፡ አንድም እየኖሩ ያሉት ህይወት ባልኖሩበት መንገድ ተገልጿል፡፡ "የተንጣለለውን እህል" በማለት የተገለፀው ሃሳብ ከህዝቡ አኗኗር ሁኔታ የራቀ ነው፡፡ ይህ ለነሱ ምኞትና ተስፋቸው ነው፡፡ በአካልና በተግባር የተቆራኙት ሁነት አይደለም፡፡ ህይወታቸው ከላይ ከሰፈረው ሃሳብ በተቃራኒ የሚገኝ ነው፡፡

"ቡቃያው ሁሉ ገና ቅጠል ሳያዘረዝር በዚያው ክችው ብሎ ሲቀር ከሞቃቱ ነፋስ ጋር አብሮ የተፈለፈለ ካንቻ የተባለ ተባይ ከስሩ መድምዶ ጨረሰው፡፡ እሸት ቀርቶ የጎመን ቅጠል ጠፋ" (*ዎዜማ*፣ 90)፡፡ ባላገሩ የሚኖረው ህይወት ጋዜጣው ካስተጋባው ሃሳብ ለየቅል ነው፡፡ የባላገሩ ህይወት ትግልና ስቃይ የተሞላበት ነው፡፡ አንድም ከተፈጥሮ አንድም ከስርዓቱ ጋር የሚታገል ማህበር ነው፡፡ አንድም ለፍቶ መና በመሆን አባዜ ተጠምዷል፡፡

የመገናኛ ብዙሃኑ መንፈስ ከባላገሩ አንፃር የማይግባቡ፣ የማይረዳዱ ወዘተ. ፅንፍ ለፅንፍ የቆሙ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ባላገሩ መገናኛ ብዙሃኑን አያውቀውም፡፡ መገናኛ ብዙሃኑም ስለባላገሩ ሁኔታ ቢረዳ እንኳን ለስርዓቱ ማድላትና የርዕዮተ ዓለሙን የበላይነት ማስፈፀም ግዴታው ነው፡፡ ዋሽቶ ለማሳመን ይፍጨረጨራል፡፡ የመገናኛ ብዙሃኑ ጥረት ሁል ጊዜ የገገር መደቡን ሃሳብ ማስተጋባት ነው፡፡ ከህዝቡ ፍላጎትና እሳቤ ጋር ፈፅሞ አይጎዳኝም፡፡ ደሪነቱ የተባለውን እንደ "ገደል ማሚቱ" ለመድገም ነው፡፡

"‥ አንዳንድ ሰዎች ለአንዳንድ ሁኔታዎች ትክክል ያልሆነ ትርጉም በመስጠት ህዝቡን የሚያሸብር ሃሰተኛ ወሬ በመንዛት የከተማውን ፀጥታ እያወኩ በህዝብ ንብረት ላይ ጥፋት

አድርሰዋል፡፡. . .” (*መባቻ፣* 3)፡፡ ይህ የቴሌቪዥንን መግለጫ ወገንተኝነቱ ለገዢው ስርዓት-መደብ ነው፡፡ አድሏዊነቱም በጥቅሱ ውስጥ ይስተዋላል፡፡ መገናኛ ብዙሃኑ የገዥው መደብ ገመና ደባቂዎች ናቸው፡፡ የህዝቡን ፍላጎትና የጥያቄ ተገቢነት ባልሆነ መንገድ ያፈርሱታል፡፡ የመላውን ህዝብ አመፃ “አንዳንድ ሰዎች በአንዳንድ ሁኔታዎች” በሚል ተራ ስሜት ይተኩታል፡፡ የምር የሆነውን ርዕዮተ ዓለማዊ ተቃርኖ ፍዝ አድርገው ይስሉታል፡፡ ነገር ግን “አንዳንድ” በሚለው ቃል ውስጥ የተወሸቀው ሃሳብ የእውነታ ገላጭነታቸው ሳይሆን፤ የድብቅነታቸው ምንጭ ነው፡፡ ምክንያቱም “አንዳንድ” በሚለው ቃል የተሸፈነ እውነታ አለ፡፡ መገናኛ ብዙሃኑ ስራው ህዝብን በጥቂቶች ወካይነት በመኮነን የገዥ መደቡን ምስል ማግዘፍ ነው፡፡

“ሐሰተኛ ወሬ” በሚል የስርዓቱን ስህተት ይሸፍናሉ፡፡ መገናኛ ብዙሃን የገዥው መደብ ድምፆች ናቸው፡፡ አንድም እውነት ለነሱ የስርዓቱ መንፈስ ብቻ ነው፡፡ አንድም ለነሱ ህዝቡ ጠያቂ ሳይሆን ተገዥ ነው ብለው ያምናሉ፡፡ አንድም መገናኛ ብዙሃኑ በሌሎች የበላይነት የሚንቀሳቀስ “ማሽን” ነው፡፡ በፍቃዱ ሚፈፅመው አንዳችም ነገር የለውም፡፡ አንድም የገዥ መደቡ ስርዓት- ማህበር ጥገኞች ናቸው፡፡ 'ራስ በቅ' አይደሉም፡፡

“. . . ኢ.ህ.አ.ፓዎች ተራማጁና ሳይንሳዊ ሶሻሊዝምን የሙጥኝ ብለው በተማፀኑ ቃላት ይሸፋፍኑ እንጂ በኢትዮጵያ አብዮት ላይ በወሰዱቸው አቋሞች በሙሉ ከመሳፍንቱና ከኢምፔሪያሊስት አሳዳሪዎች አንድ ናቸው . . . ፡፡” *(ማግስት፣* 59) የመገናኛ ብዙሃኑ ስርዓቱን የሚሞግቱ ቡድኖችን ማውገዝ ስራቸው ነው፡፡ የተተከለው ስርዓት እንዲፈርስ ፊፅሞ አይፈለግም፡፡ ከገዥው መደብ በተቃራኒ የቆመ ሁሉ ይወገዛል፡፡ የመገናኛ ብዙሃኑ ለፊውዳሉ ስርዓት ተሚጋች እንደነበር ሁሉ፤ ከርዕዮተ ዓለም መቀየር ጋር ተያይዞ የተተካውን የደርግ ስርዓት መምሰልም ግዴታው ነው፡፡ የመገናኛ ብዙሃን ሁልጊዜ ከወቅቱ ርዕዮተ ዓለም ጋር ይቆራኛሉ፡፡ ስርዓቱ ሲፈርስ አብረው ይፈርሳሉ፡፡ ሲተካ አብረው በአዲስ ማንነት ይተካሉ፡፡ ለገገር መደቡ ተቃራኒ የሆነ ሁሉ፤ የመገናኛ ብዙሃኑም ተቃራኒ ነው፡፡ ይህ ዑደት ሁል ጊዜ በተዘረጋው ስርዓት የበላይነት ይቀጥላል፡፡ የተቃራኒውን ወገን ማጥላላት የተለመደ ነው፡፡ አንድም የተዘረጋው ስርዓት ባጭር መቀጨትን አይሻም፡፡ በአንድ ማህበር ውስጥ ስር ሰዶ የመኖር ፍላጎት የየትኛውም ርዕዮተ ዓለም ፍላጎት ነው፡፡ በመሆኑም መገናኛ ብዙሃኑ የኢ.ህ.አ.ፓ.ዎችን አስተሳሰብ "ከመሳፍንቱና ከኢ.ምፔሪያሊስት

አሳዳሪዎች አንድ ናቸው" ሲሉ ይተቻሉ፡፡ ለተዘረጋው ስርዓት ያላቸውን አብሮነት ያፀናሉ፡፡

> *. . .በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ውስጥ ለኢ.ህ.አ.ፓና ለኢ.ዲ.ዩ በውስጥ አርበኝነት አብዮቱን ለመቀልበስ ተራማጅ የደርግ አባላትንና የህዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ፅህፈት ቤት ታጋዮችን ለማፈን ሲያሴሩ በተያዙት በሚከተሉት የውስጥ አርበኞች ላይ በዛሬው እለት አብዮታዊ እርምጃዎች ተወስዶባቸዋል፡፡ (ማግስት፣ 222)*

በየትኛውም መንገድ መገናኛ ብዙሃኑ የገዢ መደቡ አጋር ናቸው፡፡ ስርዓቱ የተቃወመውን ይቃወማሉ፤ የደገፈውን ይደግፋሉ፡፡ አንዳቸው ካንዳቸው ተነጥለው ሊጓዙ አይችሉም፡፡ "ኢ.ህ.አ.ፓ"ና "ኢ.ዲ.ዩ" የስርዓቱ ተሟጋቾች ናቸው፡፡ ስለሆነም በገዥው መደብ ይወገዛሉ፡፡ በተወጋገዙ ወገን ላይ የተወሰደው እርምጃ፣ ያለነቀፌታ በመገናኛ ብዙሃኑ ይነገራል፤ ይተቻል፡፡ የ "አብዮቱ ቀልባሾች" ለመገናኛ ብዙሃኑና ለገዢው መደብ ያላቸው ምስል ተመሳሳይ ነው፡፡ አንድም የገዢ መደቡን ተግባር መናገርያ መስመሮች ናቸው፡፡ አንድም የስርዓቱ ስሜት የነሱም ስሜት ነው፡፡ አንድም ያለመገናኛ ብዙሃኑ ስርዓቱ ህልው አይሆንም፡፡ አንድም ያለገዢ መደቡ በጎ ፈቃድ መገናኛ ብዙሃኑ አይመሰረቱም፡፡ ምክንያቱም አብዛኛውን ጊዜ የስርዓቱ ፍላጎት ማስፈፀሚያዎች ናቸው፡፡ ስለሆኑም "አብዮታዊ እርምጃዎች ተወስዶባቸዋል" እያሉ የስርዓቱን ድምፅ ሲያስተጋቡ ይስተዋላል፡፡ በማዕበል የአብዮት ዋዜማ፣ በማዕበል የአብዮት መባቻ እና በማዕበል የአብዮት ማግስት ውስጥ የመገናኛ ብዙሃኑን ሚና ከገዢ መደቦቹ ፍላጎት ውጪ ነጥሎ ማየት አይቻልም፡፡ ተወራራሽ የሆነ ባህሪ ይታይባቸዋል፡፡ ከስርዓቱ ስሜት ውጭ አይጓዙም፡፡

በጥቅሉ የገዢ መደቡ ፕሮፓጋንዳ ማስፈፀሚያዎች ናቸው፡፡ ራሳቸውን ችለው የሚያስተጋቡት አንዳችም ሃሳብ የላቸውም፡፡ የየስርዓቱ ጥገኞች ናቸው፡፡ ከገዥ መደቦቹ ጋር አብረው ይሰለፋሉ፡፡ ሲሻሩ አብረው ይሻራሉ፡፡ አዲስ ስርዓት ሲተካ በተተካው ስርዓት ውስጥ በአዲስ ማንነት ይወለዳሉ፡፡ ሚናቸው እንደየርዕዮተ-ዓለሙ ባህሪ ይወሰናል፡፡ ከመገናኛ ብዙሃኑ በተለየ መልኩ ትምህርት ቤቶች ደግሞ የተዘረጋው ርዕዮተ ዓለም ማጎልበቻ ስፍራዎች ሳይሆኑ፣ የተቃውሞ ድምፅ ስፍራዎች ናቸው፡፡ የተቃርኖ ሃሳብ መገለጫዎች ናቸው፡፡

### 3.4.2 ትምህርት ቤት እንደ ተቃውሞ ድምፅ

ትምህርት ቤቶች የግንዛቤ ተቋማት አንድ አካል ናቸው፡፡ አንድም የተዘረጋውን ርዕዮተ ዓለም የማስፈፀም አቅም አላቸው፡፡ አንድም የተቃውሞ መድረክ ሆኖ የመከሰት አጋጣሚያቸውም ከፍ ያለ ነው፡፡ በድርሰቶቹ ውስጥ ትምህርት ቤቶች ባብዛኛው የተቃውሞ ድምፅ ስፍራዎች ናቸው፡፡ በህዝቡ መነሻነት ያልተመቻቸውን ይነቅፋሉ፡፡ ይቃወማሉ፡፡

"የወሎንና የትግሬን ህዝብ ለረሃብ የዳረገው የኃይለስላሴ ፋሽስታዊ አገዛዝ ይወድማል!! የኃይለስላሴ ፋሽስታዊ አገዛዝ ተባባሪዎችና ቡችሎች ሁሉ የህዝብ ቅጣት ይጠብቃቸዋል፡፡ በኢትዮጵያ የግፍ አገዛዝ ዕድሜው አብቅቷል፡፡ ተነሡ!" *(ዋዜማ፣* 161)፡፡ ይህ ሃሳብ ማስረሻ የተባለው ገፀ-ባህርይ ስደተኛ ባላገሮቹን ፍለጋ በወጣበት ጊዜ በተማሪዎች ተፅፎ (ተበትኖ) ያገኘው ወረቀት ነው፡፡ ንቃተ ህሊናው በትምህርት የዳበረው ተማሪ ወገንተኝነቱ ለህዝቡ ነው፡፡ አንድም ተማሪው ከህዝብ አብራክ የተገኘ ማህበር ነው፡፡ አንድም የህዝቡ ጉዳት የተማሪውም ጭምር ነው፡፡ አንድም የሸመተው እውቀት ብዙ ጥያቄዎችን እንዲያነሳ ይገፋዋል፡፡ በመሆኑም አንድም በወረቀት፣ አንድም በግላጭ ይቃወማሉ፡፡ "ፋሽስታዊ አገዛዝ" ና የ"ግፍ አገዛዝ" በሚሉት ቃላት ውስጥ የስርዓቱ የጭቆና መንፈስ በግልፅ ይታያል፡፡ ይህን ጭቆና ደግሞ ተማሪው ፈፅሞ አይሻውም፡፡ አንድም የሰብአዊነት ፅንሰ ሃሳብ ከልቡናው ተጋብቷል፡፡ አንድም በአዳዲስ ርዕዮተ ዓለም አእምሮው መቃኘት ጀምሯል፡፡ ስለዚህ የተሻለውን ፍለጋ ይቃወማል፣ ይጠይቃል፡፡ የተማሪው ተቃውሞ ግልብና ተራ አይደለም፡፡ በምክንያት ከዳበረ ውስጣዊ ስሜት የመነጨ ነው፡፡ ለዛም ይመስላል "ተነሱ" የሚል ቅስቀሳ ሚሰነዝሩት፡፡

"ተነሱ" የሚለው ቃል አንድም የስርዓቱ መቋጫ ጊዜው መዳረሱን ይጠቁማል፡፡ አንድም በባላገሩ ህይወት ውስጥ ተቀብሮ የኖረውን ድብቅ ስሜት ይቆሰቁሳል፡፡ አንድም አዲስ ርዕይን በማህበረሰቡ ውስጥ ያመላክታል፡፡ አንድም የአመፅ መንደርደሪያ ነው፡፡ የዚህ የተቃውሞ ድምፅ መጠንሰሻ ቦታ ትምህርት ቤቱ ነው፡፡ ትምህርት ቤት የህዝቡ መሰረታዊ ጥያቄ ማደሪያ ነው፡፡ ምክንያቱም ተማሪው በዘመናዊ እውቀት ሰበብ የሰረጸው አዳዲስ ምልከታዎች አሉት፡፡ ምልከታዎቹ ደግሞ የአዲስ ማንነት ፍለጋ መንገዶች ናቸው፡፡

*አራት ኪሎን ይዞ የዩኒቨርሲቲና የምኒልክ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የኃይለስላሴን መንግስት በማውገዝ፤ ህዝቡ የደረሰበትን በደል በመዘርዘር መፈክሩንና መዝሙሩን ያቀልጡታል፡፡ . . . የእሳት አደጋ ውሃ የጋዝ ጭስ ጥይት በአንድነት ሲወርድበት እንደደነበረ መንጋ ለቅፅበት ከተበጠበጠ በኋላ መልሶ ሰብሰብ ገታ ይልና ያደፍጣል፡፡ (መባቻ፣ 5-6)*

ለህዝቡ የጭቆና ጥያቄ ቀስቃሽና ተንኳሹ ትምህርት ቤቶች ናቸው፡፡ አንድም ከተራው ህዝብ ይልቅ የገገርውን መደብ ስራና ተግባር በቅርበት ያውቁታል፡፡ አንድም ተማሪና ትምህርት ቤት የ "ለውጥ" ሃዋሪያ ናቸው፡፡ ለውጡ አንድም በአመለካከት፤ አንድም በናፈቁት አዲስ ስርዓት ሊገለፅ ይችላል፡፡ "ማውገዝ"ና "በደል መዘርዘር" የገዥውን መደብ ኢ-ፍትሐዊነት ማሳያ ነው፡፡ የማህበረሰቡን ጭቆናና ረገጣ መጠቆሚያ ነው፡፡

በዚህ የተቃውሞ ድምፅ ውስጥ ተማሪው ለውጥ ፈላጊ ነው፡፡ ደምና እምባውን ገብሮ ያረጀና ያፈጀውን ስርዓት ይጋፈጣል፡፡ ለህዝብ አዲስ ኑሮ ቦይ ይቀዳል፡፡ አንድም የፊውዳሉ ስርዓት በተማሪው ርዕይ ተራ ነው፡፡ አንድም ባባቶቻቸው ገፅ ላይ ያስተዋሉት አሻራ ጥሩ አይደለም፡፡ አንድም የበዝባዥና የተበዝባዥ መስተጋብሩ የረሃብ ውጤትን አስከትሏል፡፡ ስለዚህ ይህ ሁኔታ ለተማሪው አይዋጥለትም፡፡ በግላጭ ከገገር መደቡ ጋር ይፋጠጣል፡፡ "የጋዝ ጭስ" ና "ጥይት" የአመፃው ምላሾች ናቸው፡፡ አመጹ በስርዓቱና በተማሪው ተቃውሞ አማካይነት የተከሰተ ነው፡፡ ተቃውሟቸው አሮጌውን ንቆ አዲሱን በመመኘት ምክንያት የሚፈጠር ነው፡፡ ቀደምት አባቶቻቸው የኖሩበት ህይወት ትርጉም ቢያጣባቸው የሚጋፈጡት ሁነት ነው፡፡ የአሁኑን ንቀው የወደፊቱን ህይወት በሌላ መንገድ ይመኛሉ፡፡ ይህ ምኞት በአንድ ጀንበር የሚጨበጥ እውነት አይደለም፡፡ በጊዜ ሂደትና ትግል የሚቀዳጁት ድል ነው፡፡ ድሉ በስምምነትና በመተሳሰብ የሚፈጠር ሳይሆን፤ ህይወታቸውን ሰጥተው (ገብረው) የሚጎናፀፉት ነው፡፡ ህይወት ሰጥተው ወደ አዲስ ህይወት ይሻገራሉ፡፡ ያለፈውን ንቀው በሚመጣው ይደሰታሉ፡፡ ዓመፅና ለውጥ ሁሌም በዚህ ንፍቀ ክበብ ውስጥ ናቸው፡፡ ስለሆነም አዝነው ይደሰቱበታል፡፡

"ዘመቻ አቋርጦ የተመለሰው ተማሪና መምህር ከተማውን በቁጥጥር ስር አውሎ ሣር ቅጠሉ ድንጋይ አፈሩ ሁሉ 'ኢ.ህ.አ.ፓ' የሚል ቃል የሚተፉ ይመስላል" (ማግስት፣ 37)፡፡ የፊውዳሉ ስርዓት ተሽሮ የሶሻሊዝም ስርዓት ቢተካም ትምህርት ቤቶች የተቃውሞ ድምፅ ማደርያዎች ናቸው፡፡ አቋማቸው ስህተትና ድክመትን መንቀስና ባመኑበት ቡድን ውስጥ ራሳቸውን ከተው ወገንተኝነታቸውን ማሳየት ነው፡፡ አንድም ተቃውሞና አመፅ ከተራው

ህዝብ በተሻለ መልኩ የተማሪው መገለጫ ነው፡፡ አንድም የተሻለውን መንገድ ለመምረጥ ልቦናና አእምሯቸው ፈጣን ነው፡፡ በመሆኑም ስርዓቱ የዘረጋላቸውን ርዕዮተ ዓለም በራሳቸው ርዕይ ይቃወማሉ፡፡ በሶሻሊዝሙ ስርዓት ደግሞ ቡድናዊነቱ ከ"ተማሪ" ወደ "መምህሩ"ም ይሻገራል፡፡

በዚህኛው ስርዓት ውስጥ የተማሪውና የመምህሩ ትብብር እጅግ ይጎላል፡፡ በአብሮነት ስሜት ውስጥ የ"ኢ.ህ.አ.ፓ"ን የፖለቲካ ቡድን ይቀላቀላሉ (በ"አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በለተይ በተማሪውና በመምህራኑ አካባቢ ከፍተኛ የመከፋፈል ሁናቴ የፈጠረው የእድገት በህብረት ዘመቻ ነበር" [መባቻ፡ 181] የሚለውን ይመለከቷል)፡፡ በዚህ ውስጥ የሚታየው መሰረታዊ ጉዳይ ትምህርት ቤት (ተማሪና መምህር) የተቃውሞ ድምፅ መድረክ መሆኑን ነው፡፡ ቀለም ገቡ ማህበር አይታገስም፡፡ አመፃውን የሚያሳየው ያልተስማማውን በመሸሽ የሚፈልገውን በመደገፍ ነው፡፡ አንድም ለተማሪውና ለመምህሩ ርዕዮተ ዓለም የምርጫ ጉዳይ ነው፡፡ አንድም ያለ አመጽ ለውጥ እንደማይመጣ ያውቁታል፡፡

ትምህርት ቤትን ከእውቀት ነጥሎ ማየት አይቻልም፡፡ የአዲስ አመለካከትና እይታዎች መፅነሻ ስፍራ ነው፡፡ አንድም ትምህርት ቤቶች ሀገርን የሚያዩበት መነፅር አላቸው፡፡ አንድም ትምህርት ቤቶች ዘመናዊነት ከስልጣኔ ተጋብቶ የሚወለድባቸው መድረኮች ናቸው፡፡ በመሆኑም የተሻለውን መርጠው ቡድናዊ መሆን ባህሪያቸው ነው፡፡ በፊውዳሉ ስርዓትም ሆነ በደርግ ስርዓት ውስጥ ትምህርት ቤቶች ለተተከለው ርዕዮተ ዓለም ተገዢ ከመሆን ይልቅ፤ ጉድፍ ነቃሽና የተቃውሞ ድምፅ ማሰሚያ ተቋሞች ናቸው፡፡ አንድም በሃሳብ፤ አንድም በድርጊት ይቃወማሉ፡፡ ዘመናቸውን ሙሉ በለውጥ መንፈስ ውስጥ ይኖራሉ፡፡

ተቋሙና የተቋሙ ፍሬ የሆኑት ተማሪና መምህራን ከ"ለውጥ" ተለይተው ሊገለፁ አይችሉም፡፡ አንድም በእውቀት ይዳብራሉ፤ ይለወጣሉ፡፡ አንድም በርዕዮተ ዓለም አማካኝነት ቅርፅ ይዘው ነባሩን ይሞግታሉ፡፡

## 3.5. ማህበረሰባዊ ውስብስብ የምክንያትና ውጤት ቁርኝት

በአንድ ሃገር ውስጥ "መሰረት" ና "ላዕላይ መዋቅር" የሚገናኙት በኢኮኖሚ ጉዳይ ብቻ አይደለም፡፡ ሌሎች ተያያዥ የሆኑ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ትስስርም ዓላቸው፡፡ በማዕበል

የአብዮት ዋዜማ፣ በማዕበል የአብዮት መባቻ እና በማዕበል የአብዮት ማግስት ውስጥ የባላገሩ ወደ መደብ ትግል መግባት ምክንያቱ ኢኮኖሚውና የብዝበዛ ሂደቱ ብቻ አይደለም፡፡ ይልቁንም ሌሎች ተያያዥ ውስብስብ መንስኤዎች ዓሉበት፡፡ አንድም በፖለቲካ ስርዓቱ ውስጥ የተሰገሰጉት ባለስልጣናት ራስ ወዳድ መሆን፤ የባላገሩን ህይወት አጨልሞታል፡፡

> *. . . ግዴለም ተወው፡፡ እንብቤዋለሁ፡፡ ብዙም ነገር የለበትም በቂ ዝናም ስላልጣለ ህዝቡ ሊቸገር ይችላል ነው የሚለው፡፡ አቃቢ ሹሙ ትንሽ እንደማሰብ አለ፡፡ አሎር! አሎር መንግስት ዝናም ሊሆን አይችልም፡፡ ይህ ግልፅ ነው፡፡. . . እንዳልኩት ዋናው ነጥብ ፖለቲካውና ፕሮፓጋንዳው ነው፡፡ (ዋዜማ፣ 98)*

በጥቅሱ ውስጥ የባለስልጣናቱ ራስ ወዳድነት የትየለሌ ነው፡፡ ከህዝቡ ይልቅ የዘረጉት ስርዓት እንዲከበር ብቻ ይሻሉ፡፡ "ከራስ በላይ ንፋስ" የሚል ብሂል የተጠናወታቸው ይመስላሉ፡፡ አንድም ለነሱ "ዋናው ነጥብ ፖለቲካውና ፕሮፓጋንዳው" ነው፡፡ አንድም የስርዓቱ መጠበቅ ለራስ ወዳድነታቸው መጎልበት የራሱን ሚና ይጫወታል፡፡ 'ሰው' በባለስልጣናቱ ርዕይ ተራ ነው፡፡ ችግራቸው እንደ ችግር የሚታይ ሳይሆን እንደ ጥፋት ሚቆጠር ነው፡፡ ባላገሩ መዘለፍያም መጠቀሚያም ነው፡፡ ርዕዮተ ዓለሙንና ስርዓቱን ለማስጠበቅ የሚሞክሩበት መንገድ እጅግ የተሳሳተ ነው፡፡ "መንግስት ዝናብ መሆን አይችልም" የሚለው ሃሳብና "ዋናው ነጥብ ፕሮፓጋንዳው ነው" የሚለው ጉዳይ አንዳቸው ባንዳቸው ውስጥ ይጣረሳሉ ፡፡ ለህዝቡ (ለባላገሩ) የመደብ ትግልና አመፅ ምክንያት ነው፡፡ በባለስልጣኑ አስተሳሰብ ህዝቡ ጓዳ እንደተረሳ እቃ ነው፡፡ ሲፈልጉት ብቻ ይጠቀሙበታል፤ ሲጎዳ ደግሞ አርቀው ይጥሉታል፡፡ የፖለቲካ አስተዳደሩ ለራሱ የተለየ ዓለም የፈጠረና በዛ ዓለም የሚኩራራ ማህበር ነው፡፡ የባላገሩን መሰረትነት ክዷል፡፡ ፖለቲካዊ አካሄዳቸውና ህዝቡ ሆድና ጀርባ በመሆናቸው፤ በመካከላቸው ያለው ግንኙነት ሻክሯል፡፡ ለዚህ ደግሞ መንስኤው የባለስልጣኖቹ ራስ ወዳድነትና ለህዝቡ ያሳዩት ንቀት ነው፡፡

አንድም ሰብአዊነት የጎደላቸው በመሆናቸው የህዝቡን ጥያቄ ንቀው አልፈውታል ("ሰዎቹ እየከሱ ሲሄዱ ፋይሉ ግን በአንድ ጊዜ ደለበ" [*ዋዜማ፣* 151] የሚለውን የ'ማስረሻ' ንግግር ይመለከቷል)፡፡ በተጨማሪ በከተማው ህዝብ ላይ ይፈፀም የነበረውን ኢ-ሰብአዊ ድርጊት የማህበረሰቡን ተዋረዳዊ ዝምድና ያፋለሰ ጉዳይ ነው፡፡ የዚህ ተግባር ፈፃሚዎችም ባለ ስልጣናት ናቸው፡፡

*ቆሻሻ ሰው አብሮ የተጠረገበት ቀልጣፋ የፅዳት ዘመቻ ነበር፡፡ . . . የከተማው አስተዳደር የፈለገውን ለማድረግ "የኮሌራ አስቸኳይ ጊዜ" ስልጣን ተሰጥቶት ነበር፡፡ . . .የትም ይድረሱ የራሳቸው ጉዳይ ነው፡፡ ኮሌራ ከሚያዛምቱ በብርድ ማለቃቸው ይሻላል፡፡ (ዋዜማ፣ 97)*

በፊውዳሉ ስርዓት ባላገሩም ሆነ ደሃው የከተማ ሰው ክብር ያጣበትና ከሰብአዊነት ደረጃው የተጓደለበት ዘመን ነው፡፡ ሰው ከ"ቆሻሻ" ተደምሮ የተቆጠረበት ዘመን ነው፡፡ አንድም ተጠርጎ ይጣል ዘንድ ይፈረድበታል፡፡ አንድም በነሱ ምልከታ ደሃው ሰው ከበሽታ እኩል የሚቆጠር ነው፡፡ ከተጠናወታቸው ህመም የሚድኑበት መንገድ ሳይሆን የሚፈለገው፤ አብረው (ከበሽታው ጋር ተደምረው) የሚጣሉበት መፍትሄ ነው ሚመቻቸው፡፡ አንድም ደሃው ሰው በባለስልጣኑ ርእይ ትርጉምና ብያኔ የለውም፡፡ አንድም ለላይኛው መደብ እንቅፋት የሆነ ያህል ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ደሃው ልቦናና አእምሮ የተቸረው ፍጡር መሆኑን ይዘነጉታል፡፡

ባለስልጣኑ ለነዚህ ሰዎች ያለው አስተሳሰብ "የትም ይድረሱ የራሳቸው ጉዳይ" በሚል የንቀትና ሰብአዊነትን አጉዳይ በሆነ ንግግር ነው የሚገለፀው፡፡ አንድም ለባለስልጣኑ ደሃው መነሻም መድረሻም የለውም፡፡ ንፋስ አባሮ እንዳመጣው "ቆሻሻ" ይቆጠራል፡፡ አንድም የስርዓቱን ምስል የሚያጎድፍ በሽታ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ የሰው ልጅ የሰብአዊነት እሳቤ በዘቀጠ አመለካከት የተሞላበት ስርዓት ነው፡፡ ጥቂቶች ርዕዮተ ዓለሙ ባጎናፀፋቸው መብትና አጋጣሚ የሚዘባነኑበት፤ እንዲሁም ደሃና ተራው ባላገር የጨለማ ህይወት የሚገፋበት ዘመን ነው፡፡ የሰው ልጅ አይነት ተበጅቶለት የሚጣልና የሚነሳ ግዑዝ አካል ተደርጎ ተወስዷል፡፡ ይህ ደግሞ ማህበሩን የተሻለ ህይወት እንዲመኝ ያደርገዋል (ለስርዓቱ መፍረስ እንደ አንድ ሰበብ ነው)፡፡ በተጓዳኝ የባላገሩ ጩኸትና ድምፅ ሰሚ ጆሮ በማጣቱ፤ ወደ ከፋ የሰብዓዊነት መንጠፍ ውስጥ ሲገባ ይታያል፡፡

"ቀን ቀን ዋናው የጊዜ ማሳለፊያ ተባይ መልቀም ነው፡፡ . . . ምድረ ቅማል፣ ምድረ ትኋን፣ ምድረ ቁንጫ ችግር ባደረቀው ገላ ላይ ዘምቶ ሲያንገበግበው የደከመና የሰለለ እጅም የደረቀ ቆዳ ሲፎክት ያድራል፡፡" (*መባቻ፣* 78)፡፡ ተፈጥሮ ፊቷን ያዞረችበት ይህ ችግረኛ ባላገር የስቃይና ችግር አዘቅት ይውጠዋል፡፡ የደሃው ደረጃ ከሰብአዊነት ይልቅ የእንስሳን ባህሪ የተላበሰ ነው፡፡ ለምለም ከሆነ አዝመራው ጋር ተቃቅፎ እንዳልኖረ ሁሉ፤ በዚህ ጥቅስ ውስጥ ግን ባላገሩ የሰቀቀን ገፊት ቀማሽ ነው፡፡ አንድም 'ትኋን'፣ 'ቅማል'ና 'ቁንጫ' የፊውዳሉ ስርዓት ርዝርዝራዥ የሆኑት ባለስልጣናት ወኪሎች ናቸው፡፡ አንድም

በውክልናቸው ውስጥ የጨቋኝነታቸው መንፈስ ይነበባል፡፡ ባላገሩ እንደሰው ኗሪ አይደለም፡፡

በህይወቱ ውስጥ አንዳች የጎደለ ነገር አለ፡፡ አንድም ቀደም ሲል የነበረው ኑሮ ርቆታል፡፡ አንድም ማጀቱ ሙሉ እንዳልነበረ ተመዕዋች ሆኗል፡፡ ማህበረ-ፖለቲካው ራስ ወዳድ በመሆኑ የነፈገው ምላሽ ለተዋረደ ኑሮው ዋንኛ ምክንያት ነው፡፡ 'ትኋን'፣ 'ቅማል' ና 'ቁንጫ' ቅርበታቸው ከሰው ይልቅ ለእንስሳ ነው፡፡ ነገር ግን ባላገሩ ረሃብ ያጎሳቆለው በመሆኑ፤ ስብአዊነቱን ሽሮ የእንስሳትን ህይወት ይጋራል፡፡ አንድም ባላገሩ አስታዋሽ ያጣ ማህበር ነው፡፡ አንድም ውለታው የተረሳ ግዑዝ ነው፡፡ አንድም በስርዓቱ እምነት እንደ መገልገያ ቁስ ይታያል፡፡ በዚህ የሰብአዊነት መንጠፍ ውስጥ ባላገሩ ማህበረ-ባህሉንም ጭምር ይተቻል፡፡

"ሰው ክቡር ነው ይላሉ ቄሶችም ሰዎችም፡፡ ታዲያ ሰው እንዴት ከውሻ የባሰ ይዋረዳል?" (መባቻ፣ 79)፡፡ ባላገሩ እየኖረ ያለው ህይወት ቢያስመርረው፣ ሰብአዊነቱ ቢያጠራጥረው ወዘተ. ሙግት አዘል ጥያቄውን ሚሰነዝረው ለኖረበት ማህበረ-ባህል ነው፡፡ የ"ሰው ክቡርነት" ምንጩ የኖሩበት ማህበረ ባህል ነው፡፡ ነገር ግን ፅንሰ ሃሳቡ ተፋልሶ ሲያገኙትና ከሰውነት ይልቅ የእንስሳዊነት ባህሪያቸው ሲጎላባቸው 'እንዴት?' የሚል ጥያቄ ይሰነዝራሉ፡፡ ለዚህ ምክንያታዊ ጥያቄ ግን ምላሽ አያገኙም፡፡ በውስጣቸው እንደተድበሰበሰ ይቀራል፡፡ በመሆኑም ለባላገሩ ትርጉም ያጣበት ማህበረ-ፖለቲካው ብቻ አይደለም፡፡ ማህበረ-ባህሉም ከንቱ ሁኖበታል፡፡ በ "ቄስ" ውስጥ የምንረዳው የቤተ-ክህነቱን ርዕዮተ ዓለማዊ ጣጣ ነው፡፡ አንድም ባላገሩ በዚህ ተቋም ተፅእኖ ውስጥ የኖረ ነው፡፡ አንድም የሰብአዊነቱን ጥግ ያወቀው በዚሁ ተቋም ነው፡፡ አንድም ተቋሙ ለኖረበት ህይወት ህግና ደንብ ሲያበጅለት ዘልቋል፡፡ ይሁን እንጂ አሁን ለባላገሩ ይህ ሁሉ ፋይዳ ቢስ ሆኖበታል፡፡ በመሆኑም ያለፈበትን ማህበረ-ባህል ዋጋ ቢስ ሆኖ ያገኘዋል፡፡ የባላገሩ መሰረታዊ ጥያቄ "ሰው እንዴት ከውሻ የባሰ ይዋረዳል?" የሚለው ነው፡፡ በዚህ ውስጥ ጎልቶ ሚታየው የሰብዓዊነት መንጠፍ ነው፡፡ የሚገፉት ህይወት ከእንስሳ ጋር እንኳን አይስተካከልም፡፡ ሕይወታቸው እጅጉን የዘቀጠና የተዋረደ ነው፡፡ እንደዚህ ባለው አጋጣሚ ውስጥ የምር ሰው ነኝ ብሎ ማሰብ አይቻልም፡፡

ማህበረ-ባህሉ ያስተማረው የ"ሰው" ፅንሰ ሃሳብ ይህ አይደለም፡፡ "ክብር" በሚል ተቀፅላ ገዝፎ የተሳለ ነው፡፡ ስለሆነም ባላገሩ እያሳለፈ ካለው ህይወት ጋር ይጋጫል፡፡ ለዚህ ሁኔታ

ደግሞ ተወቃሹ የፊውዳሉ ስርዓት ነው፡፡ ስርዓቱም ሰብአዊነታቸውን እንዲክዱ አድርጓቸዋል፡፡ ይህ ሁሉ ነገር ለገገር መደቡ መንገዳገድና መውደቅ መንስኤዎች ናቸው፡፡ መሰረቱ (ባላገሩ) ከላእላይ መዋቅሩ (ከባላባቱ፣ መሳፍንቱ፣ መኳንንቱ ወዘተ.) ጋር ያለው ዝምድና ኢኮኖሚያዊ ብቻ አይደለም፡፡ ይልቁንም ውስብብ ባህላዊ፣ ፖለቲካዊ ወዘተ. ቁርኝትም ጭምር ነው፡፡ በጥቅሉ በመሃላቸው ያለው መስተጋብር የመገበርና የማስገበር ኢኮኖሚያዊ ጣጣ ብቻ አይደለም፡፡ በህይወታቸው ውስጥ በተለያየ አንፃር የሚታኝ ዝምድና አለ፡፡ ይህ ዝምድና ተራና የአንድ ለአንድ ቁርኝት ተደርጎ በተናጥል የሚታይ ሳይሆን፤ ውስብስብ በሆነ መንገድ ከኑሯቸው ጋር ሚተሳሰር ነው፡፡ በጥቅሉ ውስብስብነቱ አንድም በተፈጥሮ(ረሃብ)፣ አንድም በፖለቲካዊ ራስ ወዳድነት፣ አንድም በማህበረ-ባህሉ እሳቤ ወዘተ. ሊታይ ይችላል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## 4. መደምደሚያ

ይህ ጥናት የመደብ ልዩነትና ርዕዮተ ዓለማዊ ተቃርኖ በ*ማዕበል የአብዮት ዋዜማ፣ በማዕበል የአብዮት መባቻ* እና በ*ማዕበል የአብዮት ማግስት*፤ ከልዊ አልኢዩሴ ማርክሳዊ ንድፈ ሃሳብ አንጻር በሚል ርዕስ የቀረበ ነው፡፡ ጥናቱ ነገረ-ፍካሬን በዘዴነት እንዲሁም የዲስኩር ትንተናን በስልትነት ተጠቅሟል፡፡ የጥናቱ ትኩረት በድርሰቶቹ መነሻነት የማህበረሰቡን የመደብ ልዩነትና ርዕዮተ ዓለማዊ ተቃርኖን በተመረጠው ንድፈ-ሃሳብ መታገዚያት መፈከር ነው፡፡ በጥናቱ የሰፈሩትን ዓላማዎች ለማሳካትም፤ በድርሰቶቹ ውስጥ የማህበርሰቡን ርዕዮተ ዓለማዊ እሳቤ መነሻን ለመመርመር ተሞክሯል፡፡

አንድም ማንነትን የማፅናትና የማጎልበትን ጣጣ በባላገሩና በመሳፍንቱ ማንፀርያነት ተፈትሿል፡፡ በዚህ ሂደትም ማህበረሰቡ እንዴት የመደብ ልዩነትን እንደሚያስተናግድ ተፈክሯል፡፡ ርዕዮተ ዓለም በግለሰብ ላይ የሚያስከትለው የማንነት ለውጥ በ ካሳሁን ማሳያነት ተተንትኗል፡፡ ከማህበረሰቡ ጋር በተያያዘ የቁጥጥር ተቋማት የጭቆና አካሄዳቸውም በሁለት ጠገግ እንደሚታይ ተገልጿል፡፡ አንድም በአካል፤ አንድም በአመለካከት እንደሚጨቁኑ ተዘርዝሯል፡፡

በጥናቱ ውስጥ የግንዛቤ ተቋማት የርዕዮተ ዓለማዊ ተቃርኖ መጠንሰሻ ስፍራዎች መሆናቸውም ተገልጿል፡፡ በተለይ መገናኛ ብዙሃን አብዛኛውን ጊዜ የገዥ መደቡ ፕሮፓጋንዳ ማስፈፀሚያዎች ሲሆኑ፤ ትምህርት ቤቶች ደግሞ በተቃራኒው የተቃውሞ ድምፅ ልሳኖች እንደነበሩ ተብራርቷል፡፡ ማህበረሰባዊ ውስብስብ የአመክንዮና ውጤት ትስስርን በተመለከተም፤ በ "መሰረት"ና በ "ላዕላይ መዋቅር" መካከል ያለው ቁርኝት ኢኮኖሚያዊ ብቻ እንዳልሆነና ከባህላዊ ፖለቲካዊ ወዘተ. አስተሳሰቦች ጋር ረቂቅ ጥምረት እንዳለው ተገልጿል፡፡ በንድፈ-ሃሳቡ መታገዚያነት አመጽ፣ ትግል፣ ለውጥ እንዲሁም አዲስ ማንነትና ወገንተኝነት ጥቅል የጥናቱ ግኝቶች ናቸው፡፡ በጥናቱ የትንተና ሂደት ውስጥ የጥናቱ ዋንኛ የማጠንጠኛ ሃሳብ በድርሰቶቹ ውስጥ የማህበረሰቡ አእምሮ የሚገነባው (ቅርፅ የሚይዘው) በርዕዮተ ዓለም አማካኝነት ነው የሚል ነው፡፡

በጥቅሉ ይህ ጥናት ከተመሰረበት ማርክሳዊ ንድፈ ሃሳብ ባሻገር *ማዕበል የአብዮት ዋዜማ፣ ማዕበል የአብዮት መባቻ* እና *ማዕበል የአብዮት ማግስት* ራሱን ችሎ ከ "ሌላነት"

(*Otherness*) ፅንሰ ሃሳብ አንፃር መጠናት የሚችል ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም ገፀ-ባህርያቱ በራሳቸው ማንነት ውስጥ ሌላውን ለመንካት ይሞክራሉ (ለምሳሌ፤ ወይዘሮ ዘርፈሽዋል)፡፡ በተጨማሪም የ "ዘለቃ" ባህሪ በፌሚኒዚም ንድፈ ሐሳብ ውስጥ ከ "አይን ማረፊያ መሆን" (*the idea of gaze*) ፅንሰ ሃሳብ አንፃር መጠናት ይቻላል ብዬ አስባለሁ፡፡ አንድም "ፍትወት" ለዘለቃ ፍልስፍናዊ መሳሪያዋ ነው፡፡ በመሆኑም አብዛኛው ሰው ሲሻት ይታያል፡፡ ይህ ደግሞ በሌላው አይን ተደራጊ (*object*) እንድትሆን አድርጓታል ብዬ አስባለሁ፡፡

# ዋቢ ጽሑፎች


ቀዳማይ የመረጃ ምንጮች

ብርሃኑ ዘሪሁን፡፡ *ማዕበል የአብዮት ዋዜማ፡፡* አዲስ አበባ፤ የኢትዮጵያ መጻሕፍት ድርጅት፣ 1975፡፡

________ ፡፡ *ማዕበል የአብዮት መባቻ፡፡* አዲስ አበባ፤ የኢትዮጵያ መጻሕፍት ድርጅት፣ 1975፡፡

________ ፡፡ *ማዕበል የአብዮት ማግስት፡፡* አዲስ አበባ፤ የኢትዮጵያ መጻሕፍት ድርጅት ፤ 1975፡፡

ካልዓይ የመረጃ ምንጮች

ብርሃኑ ገበየሁ፡፡ ‹‹ልቦለድ እንደ ርዕዮተአለም መገለጫ››፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፤ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም፤ ለሀዲስ 90ኛ የልደት በአል የቀረበ መጣጥፍ፣ የአዲስ አበባ የምርምርና ህትመት ቢሮ (ቁ. 10፣ ገጽ 43-76)፣ 1992፡፡

ቴዎድሮስ ገብሬ፡፡ *በይነ-ዲሲፕሊናዊ የሥነ-ጽሑፍ ንባብ፡፡* አዲስ አበባ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕሬስ፣ 2001፡፡

ደጀኔ ተሰማ፡፡ ‹‹የጀንሶቶንቤን *ዘግሬፕስ ኦቭራቭ* እና የብርሃኑ ዘሪሁን *ማዕበል የአብዮት ዋዜማ* ንፅፅራዊ ጥናት››፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል (ዲማጽ)፣ 1982፡፡

ገነት ለማ፡፡ *‹የ ማዕበል የአብዮት ዋዜማና መባቻ የቋንቋ ይዞታ››፡፡* አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል (ዲማጽ)፣ 1975፡፡

ይልማ ደምሰው፡፡ ‹‹የጉዲካሳ፣ የአደፍርስና የካሳሁን ማህበራዊ እይታ››፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል (ዲማጽ)፣ 1986፡፡

ጥሩዬ ዓለሙ፡፡ ‹‹በብርሃኑ ዘሪሁን ልቦለዶች ላይ የታዩ አንዳንድ ለውጦች››፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል (ዲማጽ)፣ 1979

አርጋው ቦጋለ፡፡ ‹‹የደራሲው ሚና በሶሻሊስት አብዮት ወቅት››፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል (ዲማጽ)፣ 1974::

አብርሃም ታደሰ፡፡ ‹‹የሶሻሊስት እውነታዊነት ፍንጮች በድህረ አብዮት የአማርኛ ልቦለዶች ውስጥ››፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል (ዲማጽ)፣ 1978፡፡

አፀደ ተፈራ፡፡ ‹‹በማዕበልና በወንጀለኛው ዳኛ ውስጥ በቋንቋ አማካኝነት የሚደረግ የገፀ-ባህርይ አቀራረፅ››:: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል (ዲማጽ)፣ 1979፡፡

Althusser, Louis. *For Marx: Radical Thinkers.* Paris: François Maspero Inc, 2005.

____________ *Lenin Philosophy and Other Essays.* London: Rutledge, 1971.

Althusser, Louis and others. *Philosophy of the Encounter Later Writings, 1978-87.* Paris: François Matheron Ltd, 2006.

Bekele Geleta. "Political Socialization in Ethiopia." Addis Ababa University: Journal of the Political Science Association (V3, n1), 1968.

Berbes, Khaled. *Rehabilitating Literary Theory: A Practical Guide for the Critical and Semiotic Analysis of Poetry and Drama.* Florida: Brown Walker Press, 2011.

Bertram and others. *Intentions and Intentionality: Foundation of Social Cognition.* Massachusets: the MIT Press, 2001.

Brian, Paltridge. Discourse Analysis: An Introduction. London: Routledge Ltd, 2006.

Cavallaro, Dani. *Critical and Cultural Theory.* London: the Athlone Press, 2007.

Eagleton, Terry. *Ideology: An Introduction.* London: Leaper and Gard Ltd, 1991.

Edgel, Stephen. *Class*. London: Taylor and Francis Ltd, 1993.

Ferretter, Luke. *Routledge Critical Thinkers: Louis Althusser*. New York: Antony Rowe Ltd, 2006.

Fikre Tolossa. "Realism and Amharic Literature (1908-1981)." Bremen: University of Bremen (Dissertation), 1983.

Goldstien, Philip. *The Politics of Literary Theory. An Introduction to Marxist Criticism*. Florida: Florida University Press, 1990.

Ilitsraya, Lenina. *ABC of Dialectical and Historical Materialism.* Moscow: Progress Publishers, 1978.

Jackson, L. Ronald and A. Michael, Dogg (eds). *Encyclopedia of Identity* (4th edition). London: Sage Publication Inc, 2010.

Levine, Andrew. *The General Will: Rousseau, Marx, Communism.* Cambridge: Cambridge University Press, 2003.

Lewis, S. William. *Louis Althusser and the Traditions of French Marxism.* New York: the Row Man and Little Field Publishing Group Inc, 2005.

Lopez, Joseph. *Society and Its Metaphor: Language, Social Theory and Social Structures*. London: Sage Publication Ltd, 2003.

Middendrop, C.P. "Progressiveness and Conservatism: The Fundamental Dimensions of Ideological Controversy and their Relationship to the Social Class". Jerusalem: New Babylon Studies in the Social Science (PP.1-43), 1978.

Michael Fiquremariam. "The Study of the Influence of Marxism on Bealu Girma's Three Novels: Haddis, Yekey Kokeb Tiri and Derasiw". Addis Ababa University: Department of Foreign Language and Literature (MA thesis), 2008.

Misraq Tarekegn. "Alienation in Three Amharic Novels: Fekir Iskemekabir, Adafris and Kadmas Bashager". Addis Ababa University: Department of Foreign Language and Literature (MA thesis), 2002.

Ransome, Paul. *Social Theory for Biggners*. Bristol: University of Bristol Press, 2010.

Robbins, Derek. *French Post-War Social Theory* (2nd Edition). London: Sage publication Ltd, 2012.

Sara Schatz and Javier Jesus Gutierrez-Rexach. "Conceptual Structure and Social Change: the Ideological Architecture of Democratization." New York University: Journal of Social Science (PP. 10-35), 2002.

Simpson, Malpas and Paul, Wake (eds). *The Routledge Companion to Critical Theory* (3rd edition). New York: Francis and Taylor group Ltd, 2006.

Stephen, A. Resnick and Richard, D.Wolff (eds). *New Departures in Marxian Theory* (4th edition). New York: Taylor and Francis Ltd, 2006.

Taylor, George R. *Integrating Quantitative and Qualitative Methods in Research*. New York: New York university press, 2005.

Thiselton, C. Antony. *Hermeneutics: An introduction*. Michigan: Eerdmans Publishing Ltd, 2009.

Valsiner, Jaan. *Cultural Psychology and Psycho-analysis: Path Ways to Synthesis*. New York: IAP-information Age Publication Inc, 2011.

Weedon, Chris. *Identity and Culture: Narratives of Difference and Belonging*. London: Open University Press, 2004.

## ማረጋገጫ

እኔ ዳዊት ብርሃኑ፣ይህ የጥናት ወረቀት ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያነት፣ በእኔ የተሰራ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ፊርማ_______________

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ


የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ- ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል


የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የመደብ ልዩነትና ርዕዮተ ዓለማዊ ተቃርኖ በማዕበል የአብዮት ዋዜማ፣ በማዕበል የአብዮት መባቻ እና በማዕበል የአብዮት ማግስት፤ ከልዊ አልኢዩሴ ማርክሳዊ ንድፈ-ሃሳብ አንጻር

በ


ዳዊት ብርሃኑ


የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሁፍና ፎክሎር መርሀ ግብር የኤም.ኤ ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉ ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት

ሰኔ 2005 ዓ.ም.

አዲስ አበባ